እስልምና ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ራእይ ጋር አይስማማም፤ አይቀበለውምም

ቀደም ብለን በገጽ 25 እንዳነበብነው የእስልምና ተሰፋ

> «ስለ ክርስቲያናዊ ንድፈ አሳብ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መባሉ፥ ስለ መሢሑ የመስቀል ዝክረ- ሐተታ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰው ልጅ ደኅንነት ስለ ማግኘቱ... ድጋፍና ነቀፋ ለመስጠት የሚረዱ እስላማዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ለይቼ ለማሰባሰብ» ነው።

ቢያንስ በሙስሊሞች መካከል፥ እስልምና ይህን በማድረግ ስኬታማ ሆኖ መሰንበቱን ስንገልጥ ኃዘን እየተሰማን ነው። የምናዝነውም ይህ በመለኮታዊ መረጃ በልጽጎ የተገለጠውን እውነት የማጥፋት ጥረት በመሆኑ ነው።

ከእስልምና ክሶች በተቃራኒ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ጊዜ ጣልቃ-ገብ ነገሮች እንዳልነበሩበትና የአዲስ ኪዳንም መጻሕፍት በአንድ ላይ ከተጠረዙበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ለውጥ እንዳልተደረገበት የታወቀ ነው። ይህ ሺህ ጊዜ ሊረጋገጥ የሚችል እውነት ነው። ደግሞም ቀደም ብሎ (ገጽ 54-55) ተመልክቷል። እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ውስጥ ያለችውን ቅዱስ እጅ ለማረጋገጥ ትንቢታዊ ገጽታዎችን ተመልክተናል (ከገጽ 59 ጀምሮ)። ምንም እንኳ ቃል በቃል እየተናገረ በማጻፍ ፈንታ፥ እግዚአብሔር በመልእክቱ አሳቦች ሰዎችን ለመሙላት ቢመርጥም፥ መልእክቱ አለ ጥርጥር ማጠናከሪያ እንዳገኘ አስቀምጠናል። አሁንም ወደ በኋላ ሌላ መረጃ ይቀርባል። በእስልምና የተተወውንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ዕቅድ በማጥናት፥ ምንም እንኳ ሁለት ኪዳኖችን ቢይዝ (ብሉይና አዲስ ኪዳኖች ሲሆኑ፥ አንዱ ከአይሁዶች ጋር የተደረገ ብሔራዊ ውል፥ ሌላው ለእግዚአብሔር የይቅርታ ስጦታ ራሳቸውን ለመስጠት ክሚፈቅዱ ሁሉ ጋር)፥ በ66 «መጻሕፍት» ቢጻፍና፥ በ1600 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ 40 በሚሆኑ ሰዎች ቢዘጋጅም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ፍጹም የሆነ የአሳብ መያያዝና ዕድገት እናገኛለን። ይህ መያያዝ አከራካሪነት ላይ በሚገኙት በእነዚህ ትምህርቶች አንፃር ሊብራራ ይችላል፦

1. ስርየት
2. ኢየሱስና የ«ሥላሴ» አንዱ አካል በመሆን መለኮታዊነቱ፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅነቱ
3. ስቅለት

አሁንም የመከራከሪያ ጥቅሶች የተወሰዱት በሚስተር ጁግል ከተዘጋጀው መጽሐፍ ነው።

በስርየት ትምህርት ላይ የእስልምና ተቃውሞ

ስርየት ምንድነው? ቃል ኪዳኑን ወይም ክስው ጋር የገባውን ውል በማፍረስ በእርሱ ላይ ካመፁ በኋላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ማለት ነው። ዓመፁንም ኃጢአት ብለን እንጠራዋለን። ለነገሩ ማንኛውም በአሳብ፥ በቃል፥ ወይም በተግባር ከቃሉ፥ ለሰው ካለው ሕጉና ዓላማው በተጻራሪ የተደረገ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው። ሁሉም ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ዓመፅን በማድረጉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አጥቷል። ይህም የሚያስከትለው ሞትን ለዚያውም መንፈሳዊን ሞት ነው። የዚህም ውጤት ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለዓለም መለያየት ነው፦

> «ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ክቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፦ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ» (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14-16)።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኃጢአት ከተሠራ በኋላ (በፍላጎት አይደለም ዘሌዋውያን 4፡2) ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ኃጢአተኛው ለኃጢአቶቹ ማስተስርያ ማቅረብ እንዳለበት አዝዟል። የአቀራረቡ ሥርዓትም በብዙ ዝርዝር ተነግሯል (ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1-7፥ 16፥ ወዘተ...)። ይህም መሥዋዕትን ማቅረብ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ

የእንስላ መሥዋዕትነት ለኃጢአተኛው ሲል በተሠቃየው በኢየሱስ ተተክቷል።

አንድ ሙስሊም የሚመለከተው መሠረታዊ ችግር በአግዚአብሔር የሰርየት ሥራ ውስጥ ንስሐ ለሚገባው ኃጢአተኛ በእርሱ ምትክ ሌላ የመሠዋቱ ጉዳይ ነው። በኃጢአተኛው ምትክ ይህ በአግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል፤ በምትኩም ላይ ትክክለኛ የሆነ ቅጣት ይፈጸምበታል። ሙስሊሞች በጥፋተኛው ምትክ ንጽሑን ሰው መቅጣት የአግዚአብሔርን የፍርድ ሚዛን ያዛባዋል ብለው ይከራከራሉ። ጥፋተኛው የመከራ ምላሽ ሊቀበል እንደሚገባው ሁሉ፥ ትክክለኛውም ሰው የመልካም ነገር ሽልማት ሊሰጠው ይገባል። ስለዚህ ትክክለኛውና ጻድቁ ኢየሱስ በእርግጥ መከራ ሊቀበል አይችልም፤ ይልቁንም እርሱን ለኃጢአተኞች እንዲሠቃይ ማድረግ ለአግዚአብሔር የማይቻል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ይህ ለአግዚአብሔር የጽድቅና ፍትሕ ጽንሰ-አሳብ ዕንቅፋት ይሆናል። ዳሩ ግን ይህ ክርክር ከቁርዓንም ጋር የሚቃረን ነው። በዚያ ውስጥ የጥንት ነቢያት መከራ እንደ ተቀበሉና እንደ ተገደሉ ይናገራል (ሱረቱ 3፡183)።

መሐመድ ራሱ በአንድ አጋጣሚ ለሞት እስኪያጣጥር ድረስ (ከዚህ የተነሣ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደ ተሠቃየ ሃዲስ ይናገራል) ከተደረገበት መርዝ የተነሣ ስለ ተሠቃየና በኡሑድ ጦርነትም የሽንፈትን ጽዋ በመጎንጨት መከራ ስለ ተቀበለ (እርሱ ራሱ ከፊቱ ላይ ቆሳስሏል፤ ሁለት የፊት ጥርሶቹም ረግፈዋል)፥ እዚህ ላይ ከሙስሊም የሃይማኖት መሪዎች ያጋጠመን ክርክር እንዲሁ ለመናገር ያህል የቀረበ ነው ብንል ከእውነት አንርቅም።

በተጨማሪም አላህ አል-ራህማን እና አል-ራህም (ጸጋን የተሞላና መሐሪ) ተብሎ የሚጠራበትን «ብስሚላሂ»ን መጥቀስ አለብን። ጸጋ የማይገባ ስጦታ ነው። በሕጋዊ አነጋገርም ይቅርታ ማለት ነው። ምሕረት ሰውየው መረዳት ይገባው ወይም አይገባው እንደ ሆነ የማይመለከት የርኅራኄ ተግባር ነው። ይህ በእርግጥ ግብታዊ የሆነ እርዳታ ነው።

ይቅርታ ወይም የሰርየት ተግባር የቃሉን ትርጉም በትክክል ከተጠቀሙበት ፍትሕ-አልባ ነው። ለተላላፊው አይገባውም። ዳሩ ግን የአግዚአብሔር ፍቅር (ጽድቁን ለማርካት) የኃጢአት ተግባር የሚቀጣበትንና

ኃጢአተኛው የሚመለስበትን መንገድ አስናድቷል። ስርየት ማለት እንግዲህ ይኸው ነው። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የሚከተለውን ቃል መቀበል መቻል አለብን፡-

> «አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና፥ ይላል እግዚአብሔር። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው» (ኢሳይያስ 55፡8-9)።

እግዚአብሔር የሚወዳቸውንና የሚወዱትን ለማዳን ዕቅድ በሚወጥንበት ጊዜ አንድም መቀበል፥ አሊያም መተው አለብን። እግዚአብሔርንና የተገለጸውን መንገዱን፡-

> «እግዚአብሔር እንዴት እንደዚያ ሳይሆን እንደዚህ አደረገ?»

ብለን በመከራከር ልንጠይቀው አንችልም። ለመሆኑ ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወይም ለመምከር እኛ ማን ነን? ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር ከእግዚአብሔር የተገለጹ እንደ ሆኑ እየተናገሩ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ያላቸውን በመመርመር እውነት በሆነው ነገር መኖር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ጻድቁን ለመከራ አሳልፎ እንደማይሰጥ የሚናገረው የእስልምና ጽንሰ-አሳብ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን የሰርየት ሥራ ዋጋ በማሳጣት የገዛ ጥቅማቸውን ለመጠበቅ የሚደረግ ክርክር እንደ ሆነ ለመገመት እንገደዳለን።

ሁል ጊዜም ሙስሊሞች በተሳሳተ መንገድ እንደሚከተለው ያስባሉ፡-

> «ይህ ትምህርት ለሰው ልጅ ላይገታ እንደ ልብ ኃጢአት ለመፈጸም ፈቃድ ይሰጣል። አንድ ሰው ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር ያለፈውና የወደፊቱ የሰው ልጆች ኃጢአቶች ታጥበው እንዲነጹ ባደረገው በኢየሱስ ደም ላይ ጭፍን እምነት መጣል ነው። ይህ ለመከተል እጅግ ምቹ፥ ተስማሚና ቀላል ትምህርት ነው። ከአማኙ የሚጠይቀው ምንም ጥብቅ ወይም ተግባራዊ የአምልኮ ዓይነት

የለም። ዝም ብሎ ማመን ብቻ ሊያስፈልገው፥ ደኅንነቱም በዚያው ይረጋገጥለታል» (ኤ.ኤስ.ኪ. ጁግል)።

በእነዚህ ቃላት ውስጥ የራስን ደኅንነት ለማስተዋወቅ የሚደረግ ጥረት አንመለከታለን። ይህ ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ነው። ምክንያቱም ይህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተፈጸመ ኃጢአት ነው። ሰው በራሱ ኃጢአቱን ለማስወገድ ብቁ የሆነ ይመስለዋል። ይህን ጭብጥ ወደ ትክክለኛ መደምደሚያው ስንወስደው፥ ሰው በራሱ «ደጋግ ሥራዎች» በማካካስ ወይም «ጥብቅ የአምልኮ ዓይነት» በማድረግ ለሠራቸው ኃጢአቶች መፍትሔ ለማግኘት ስለሚችል፥ ሰው እግዚአብሔርን አይፈልገውም ማለት ይሆናል። «የአምስቱ የእስልምና አእማድ» ዓላማ ይኸው እንደ ሆነ እናስባለን። ይሁንና ደግ ሥራ መሥራት ኃላፊነታችን ነው። ይህን በማድረግ ግን የሚመጣ ትርፍ የለም። ለኃጢአታችን ደግ ሥራ በመሥራት ለማካካስ የምንፈልግ ከሆነ፥ ጽድቅን ለራሳችን ያዘጋጀነው እኛው ነን ማለት ነው። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ «ጽድቃችን ሁሉ አንደ መርገም ጨርቅ ነው» (ኢሳይያስ 64፡6) ይላል።

ችሎት የቀረበ ወንጀለኛ ደግሞ ያንን ጥፋት አንደገና እንደማይፈጽም ወይም ለወደፊት «ደግ ሰው» ለመሆን ቃል በመግባቱ በነጻ ስለ መለቀቁ ሰምተህ ታውቃለህ?

ስውሩ ችግር ያለው ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ «ኃጢአት» ለሚለው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጽንሰ-አሳብ እጅግ የተለየ አመለካከት ከመያዛቸው ላይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአት የተመለከተው የሰውን ልጅ ሁሉ ባሪያ የሚያደርግ አና ሁሉንም ሰው ኃጢአትን ወደ መሥራት የሚገፋፋ መምሪያ ሆኖ ነው። እንደ መግደል ያለ «ትልቅ ኃጢአት» ወይም በንግድ ላይ ውሸትን እንደ መናገርና ከኩባንያ ውስጥ አንድን ነገር እንደ መስረቅ ያለ «ትንሽ ኃጢአት» ቢሆን፥ ኃጢአት የሰው ከጥገኝነት ነጻ የመሆን ዝንባሌ፥ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ግልጽ ዓመፅ ነው። ሁለቱም በሰው ፈቃድ አና ሕሊና ውስጥ ማዕከላዊው ስፍራ ለእግዚአብሔር እለመሆኑን ያስቀድማሉ። ምናልባት በርካታ ሃይማኖታዊ ግብሮችና መስጠት ቢኖረውም የአምላኪው ታማኝነት ባመዛኙ በሥራው ፍሬ-ከርስኪ ይሆናል። እነዚህን ኃጢአቶች ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ

በማሽከርከራችን እንደሚሰጠን የቅጣት ትኬት አድርገን ልንወሰዳቸው አንችልም፤ ኃጢአት እኛን ከእግዚአብሔር ይለየናል!

> «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አውን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቊጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን . . . ጸጋው በአምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከአናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌሶን 2፡1-5፥ 8-10)።

ሃያሲያን አያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ክርስቲያን እንደ ሆነና ንስሐ (ከኃጢአት መመለስ) አንድም እንደማያስፈልግ፥ አሲያም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አካል እንደ ሆነ ይገምታሉ። ስለ ሆነም ለማዳን ሥራው እግዚአብሔርን ማፍቀሩ አይከሰትም፤ ከዚህም የተነሣ አማኙ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት አይመራም። እንዲህ አይደለም! ኃጢአቱ ይቅር ስለ ተባለለት፥ ክርስቲያን ራሱን ስጥቶ በምስጋና ይመላለሳል። አንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ዳግም ኅብረት ለማድረግ በመቻሉና በደኅንነቱም ፍሬ ይደስታል። ይህም አለ ጥርጥር ቅድስና ነው፡-

> «ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» (ዕብራውያን 12፡14)።

ምንጩን ሳይጠቅሱ ሚስተር ጁግል ከስርየት የተነሣ አማኙ «እንደሚድን የተረጋገጠ ስለ ሆነ እስከ ፈለገው ድረስ ኃጢአት መፈጸም ይችላል» በማለት ዶክተር ማርቲን ሉተር እንደ ተናገሩ ይገልጻሉ። ይህ ዐረፍተ ነገር

ክሌላው የሉተር ትምህርትም ሆነ ከሥራው ጋር የማይዛመድ ስለ ሆነ፥ አንቀበለውም። ይህን ዐረፍተ ነገር ማርቲን ሉተር ተናግሮታል ከተባለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይስማማ ስለ ሆነ፥ ከተለየ ዓውድ የቀረበ ነው ማለት ነው። በሚስተር ጄማል አስተያየት የዚህ ትምህርት ውጤት ለሚከተለው ነገር መንስኤ ነው፡-

> «የአውሮፓና አሜሪካ ክርስቲያን ከፍለ ዓለማት ለሚዋጉበት የሞራል ውድቀትና የግብረ-ገዥነት መታጣት።»

እኛ ስለ ክርስቲያን ከፍለ ዓለም ወይም ክርስቲያን ጎብረተስብ የምናውቀው የለንም። የተሳሳተው አመለካከት የሚመነጨው ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ ከማስቡ ላይ ነው። ላይ ላዩን የሚመለከትም ሰው ከላይ እንደ ተጠቀሰው ወዳለ መደምደሚያ ይደርስ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይህ አውነት እንዳልሆነ አጥብቆ ይናገራል፡-

> «ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ፥ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው» (ራእይ 21፡8)።

> «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቊጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሚም አንዳልሁ፥ አንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። አንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከከፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ» (ገላትያ 5፡19-24)።

የዳንነው ከአንድ ነገር አና ለአንድ ነገር ስለ ሆነ፥ ይህን ከላይ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቸል ማለት ስለ ስርየት የተሳሳተ ነገር ማቅረብ

ማለት ነው። ስለ ሆነም «ከአንግዲህ ሕግን መከተል አያስፈልጋቸውም» ብሎ መደምደሙ ስሕተት ነው።

ከርስቲያኖች ከሕግ በታች አለመሆናቸው እውነት ነው።

> «በእውቀት አይቅኑ እንጂ (አይሁዶች) ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ከርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና። ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና» (ሮሜ 10፡2-5)።

> «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ አምነት አንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» (ገላትያ 2፡16)።

ስውን ጻድቅ ለማድረግ የሚችል ሕግ በዓለም ላይ የለም። ሕግ ትክክለኛ ወይም ስሕተት የሆነው የትኛው አንደ ሆነ ያሳያል እንጂ፥ ስውን ትክክል የማድረግ ብቃት የለውም። ፍርድ የሚሰጥበት መመዘኛ ብቻ ነው።

> «በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከአምነት የጽድቅን ተስፋ አንጠባበቃለንና። በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ አምነት አንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና» (ገላትያ 5፡4-6)።

> «አንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቊጠረለት። እንኪያስ ከአምነት የሆኑት አነዚህ የአብርሃም ልጆች አንደ ሆኑ አወቁ። መጽሐፍም አግዚአብሔር አሕዛብን በአምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። አንደዚህ ከአምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።

«ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው። ሕግም ከእምነት አይደለም ነገር ግን፡- የሚያደርገው ይኖርበታል ተብሏል። በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።

«ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። የሰው ስንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን ማንም አይንቅም ወይም አይጨምርበትም። ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፡- ለዘሮቹም እይልም፤ ስለ አንድ አንደሚነገር ግን፡- ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ። ይህንም እላለሁ ከእራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ እስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተሰፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርሰም። ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተሰፋ ቃል አይሆንም፤ በተሰፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ሰጥቶአል።

«እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተሰፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ። መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።

«እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም። ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተሰፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።

«እምነትም ላይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ እምነት ግን መጥቶአልና

ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም። በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና» (ገላትያ 3፡6-26)።

ዳሩ ግን ይህ ማለት አማኞች እንደ ፈለጋቸው ሥርዓት በሌለው አኳኋን ይኖራሉ ማለት አይደለም።

«የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም። ወይስ ጌታን እናስቀናውን? እኛስ ከእርሱ ይልቅ እንበረታለንን?

«ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ» (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡21-24)።

ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔርን እንዲወዱና እርስ በርሳቸውም እንዲዋደዱ በደንብ አስተምሮአቸዋል።

«ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐንስ 14፡15)።

«እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ» (ዮሐንስ 13፡34)። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐንስ 14፡23)።

በዚህም የብሉይ ኪዳን ትእዛዛት ሁሉ ተፈጽመዋል፡-

«ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ዝም እንዳስኛቸው በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ። ከእነርሱም አንድ ሕግ እዋቂ ሊፈትነው፡- መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸዱቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ

ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል» (ማቴዎስ 22፡34-40)።

ስርየትን በተመለከተ ተቺዎች የሚከተለውን ጥያቄ ይሰነዝራሉ፡-

> «ከእርሱ ጋር ሲወዳደሩ ዋጋ ለሌላቸው፥ ኃጢአተኛና ከስማና ለሆኑት ሰዎች ብሎ ስማያዊው አምላክ ራሱን ሰውቷል ብለን እንዴት ለማመን እንችላለን? የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ ከእስተውሎት የተቃረነና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነው።»

የተፈጥሮ ሕግ እዚህ ውስጥ እንዴት እንደሚገባ አይታየንም (ለምሳሌ ስለ እናቶች የመሥዋዕትነት ፍቅር አስብ)፤ ዳሩ ግን ምናልባት ግንዛቤአችን የተሟላ ላይሆን ቢችልም እንኳን፥ አንዳንዶቻችን ፍቅር ምን እንደ ሆነ ሰመረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፡8)። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ራሱን ስለ ገለጸና በቃሉም ራሱን ስለ አሰረ፥ ሰማያዊው አምላክ እንደ ቃሉ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ መስጠቱን ለማመን እንችላለን። ይህም ዋጋ ለሌላቸው ሳይሆን፥ ለወደዳቸው ሰዎች ነው። ፍቅር ካለ ዋጋ-ቢስነት ጓዙን ጠቅልሎ ይወጣል። በስብአዊ ደረጃ እንኳ አንድ «ዋጋ የሌለው» ሰው የፍቅር ተቀባይ ከሆነና ለዚያም ምላሹን ለመስጠት ከቻለ፥ ከፍተኛ ዋጋ ያሰው ሰው እንደሚሆን ልብ በል። በእርግጥ ይህ አላብ ከ«አስተውሎት» ጋር ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች፡-

> «ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስክ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደረሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌሶን 3፡19)

የሚል ማበረታቻ ተስጥቷቸዋል።

በቃሉ ውስጥ ራሱን ስለ ሰጠና ልንደገፍበትም ስለምንችል፥ የሰማዩ አባታችንን ለማመን እንችላለን።

> «ስለዚህም እግዚአብሔር፥ የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለ ፈቀደ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር (በተስፋ ቃልና በመሐላ)

> ... ለእኛ ብርቱ መጸናናት ይሆንልን ዘንድ፥ በመሐላ በመካከል ገባ» (ዕብራውያን 6፡17-18)።

ሌላው ከሃያሲያኖቻችን የሚቀርብብን ነቀፋ በክርስቶስ ያመኑት ስዎች እንደ ሌሎቹ ስዎች ሁሉ ስለሚሞቱ፥ ስርየት ምንም ዋጋ የለውም የሚል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀ ሰው ከዕርቁ የተነሣ በሥጋ እንደማይሞት አልተነገረንም። ይልቁንም፡-

> «ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ስውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈላችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ስውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል» (ሮሜ 8፡10-11)። (ይህ በመንፈላዊ ገጽታው አሁንም እውን ሲሆን የአማኙንም ትንሣኤ ይመለከታል።)

በሌላ ምንባብ ውስጥ ደግሞ የሚከተለውን እናነባለን፡-

> «በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ክክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን» (ኤፌሶን 2፡5)።

የስርየት ዋጋ ሥጋዊ ላይሆን መንፈሳዊ ነው። ምንም እንኳ በሥጋ ብንሞትም፥ እንደ ሌላው ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ በመጨረሻው ቀን ደግሞ እንነሣለን። ዳሩ ግን ፍርድና ኩነኔ አያጋጥመንም፤ ይህ በኢየሱስ ላይ አስቀድሞ ተፈጽሞአል።

ሙስሊሞች ክርስቶስ ሕይወቱን በፈቃዱ ቤዛ አድርጎ አልስጠም ባዮች ናቸው፡-

> «በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፡- አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ክእኔ ትለፍ» (ማቴዎስ 26፡39)።

አሁንም ሃያሲያኖቻችን ዓውደ ንባቡን ቸል ይላሉ። ከመያዙ ትንሽ ቀደም ብሎ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ሲጸልይ ነበር። ከላይ የተጠቀሱት ቃላትም የጸሎቱ ከፍሎች ነበሩ። እንዲሁም የሚከተለውን ብሏል፡-

«ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች።»

ይሁን እንጂ ሰጸሎቱ ማሠሪያ ያበጀው፡-

«ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን»

በማለት ነበር።

ሌላው የወንጌል ዝክር ስለ ክርስቶስ የሚከተለውን ይዘግባል፡-

«በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ» (ሉቃስ 22፡44)።

የሕክምና ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ክርስቶስ በሰይጣን ከመፈተኑ የተነሣ በጌቴሴማኒ ወደ ሞት አዝምሞ እንደ ነበር («እስከ ሞት ድረስ እጅግ እንደ አዘነ») እንመለከታለን። ይህም አብዝቶ በማይከሰተውና በሕክምና መረጃ መሠረት በክፍተኛ ሥጋት ወይም ፍርሃት ላቢያ ወደ ሞት በሚመራ በደም ላብ የተንጸባረቀ ነው። ከፊቱ የተደቀነው ነገር «መለስተኛ ቅጣት» (ኤ.ኤስ.ኪ. ጁማል) እንዳልሆነና ዳሩ ግን እጅግ የከፋ ሥጋዊ ሥቃይ እንደ ሆነ ልብ ማለት አለብን። ክርስቶስን በተመለከተ ግን ያልረከሰውና ቅዱስ የሆነው እርሱ በዓለሙ ሁሉ ኃጢአት መቆሸሹ መንፈሳዊ ሥቃዩን ከዚህም የበለጠ ያደርገዋል።

በዕብራውያን 5፡7 የተጠቀሱትን አንዳንድ መግለጫዎች ማንበቡ ጠቃሚ ነው፡-

«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር (በጌቴሴማኒ) ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት» (ዕብራውያን 5፡7)።

ይህ ወደ መስቀሉ የሚያመለክት ከሆነ እልተሰማለትም፤ እዚያው ላይ ሞቷልና። ስለዚህ የ«ጽዋ ማለፍ» ከመስቀሉ ሞት ነጻ ለመሆን የተደረገ ጸሎት ሳይሆን፥ ይልቁንም ወደ መስቀሉ እንዳይሄድ ከሚያደናቅፈው ሞት ለማምለጥ የቀረበ ጸሎት እንደ ሆነ አድርገን መደምደም አለብን።

ጻድቅና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር እንዴት ይቅር ባይና መሐሪ ሊሆን ይችላል?

ለሚለው ትልቅ ጥያቄ እስልምና የማያገኘውን መፍትሔ ነው የስርየት ሥራ ያቀረበው። ኃጢአትን በመቅጣት ጽድቁን ሲያሳይ፥ ቅጣቱን ራሱ በመቀበል ምሕረቱን ይገልጻል። ክዚህ በስተቀር ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር መሐሪም የሚሆንበት መንገድ የለም። ይህን ነጥብ ከታሪክ ውስጥ የተወሰደው ክንዋኔ በይበልጥ ያብራራው ይሆናልና እነሆ፡-

ሳሙኤል ከ200 ዓመታት በፊት የነበረ የካውካሰያን መሰፍን ነበር። ሕዝቡ ጎረቤታቸው ከሆነችው ከቱርክ ጋር በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ነበሩ። አንድ ጊዜ የቱርክን ከተማ በወታደሮቹ ከበበ። እናቱም እንደ ተለመደው ከእርሱ ጋር በካምፑ ውስጥ ነበረች። አንድ ምሽት ድንገተኛ የሆነ ጥቃት ለማድረግ ዐቀደ። ዳሩ ግን ጠላት ነቅቶ ይጠብቀው ነበር። ምስጢራዊ ዕቅዶቹም ከሸፉ። ድሉም ታጣ። ሳሙኤልም ወሬ አቀባዩ ከተገኘ በመቶ የጅራፍ ግርፋቶች አንደሚቀጣ በቁጣ አስታወቀ። አሁንም በትልቅ ምሥጢር ሌላ ድንገተኛ ጥቃት ታቀደ። ውጤቱ ግን ያው ነበር። ዳሩ ግን ወሬ አቀባዩ ታወቀ፤ እርሷም የሳሙኤል እናት ነበረች።

ለሦስት ቀናትና ሌሊት ራሱን በድንኳን ውስጥ ሸሸገ። ምን ያድርግ? እናቱን ቢያተርፍ፥ ሁሉም ሰው ትክክል አንዳላደረገ ይናገራል። ቢቀጣት ደግሞ ሁሉም «ሳሙኤልን እዩት! ለእናቱ እንኳ ርኅራኄ የለውም» ማለታቸው አይቀርም። በመጨረሻም ከድንኳኑ ብቅ አለ። በናፍቆት ይጠባበቀው የነበረ ጦር ሠራዊቱም ሰብሰብ አለ። ኮስተር ብሎ ለሕዝቡ እየተናገረ፡- «ከወሬ ቅብብሎሹ የተነሣ ሁለት ድሎችን አጥተናል። ሰዎቻችንም ተገድለውብናል። ነገሩን የምናቃልልባቸው መንገዶች የሉም። ጥፋቱ ሰለ ተፈጸመ፥ አጥፊው ግለሰብ በሕጌ መሠረት በመቶ ጅራፍ መቀጣት አለበት! ጽድቅና ፍርድ መከበር አለባቸው» አለ።

እናቱም ወደ መግረፊያው ከበብ ተወሰደች። ፊቷ ገርጥቶ በፍርሃት ትንቀጠቀጥ ነበር። ገራፊው ጅራፉን አነሣ፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ጅራፍ ከማረፉ በፊት ሳሙኤል ጮኸ፡- «ቆየኝ! እርሷ እናቴ ነች። እኔም ከደምዋና ከሥጋዋ ነኝ። እኔ ለእርሷ ቅጣቱን እቀበልላታለሁ» አለ። ወደ ከበቡ በመግባት ልብሱን አውልቆ፡- «ገራፊ ሆይ፥ ከመጨረሻው ጥፋተኛ ባነስ ሁኔታ ለመግረፍ አታስብ። ኃላፊነትህን ተወጣ። በል ቀጥል!» አለ። ራሱን ሰቶ እስኪወድቅ ድረስ ግርፋት በግርፋት ላይ ቀጠለ። ከተጠበቀው በላይ ግን ሕይወቱ ተረፈ። ይህ ክስተት ምናልባትም በታሪክ ከተጠቀሱት

ሁሉ በላይ ክኢየሱሰ ሁኔታ ጋር ይዛመዳል። እርሱ ሥጋን የለበለ አምላክ ነበር። ጽድቅ ፍርድም መፍረድ ነበረበት። ነገር ግን በፍጹም ፍቅሩ የእኛን (የእኔን፥ ያንተን) ኃጢአት በራሱ ላይ በማድረግ፥ የዚህ ውጤት የሆነውን ሥቃይ በመስቀል ላይ ተሠቃየ። ይህም ከፉና ጭካኔ የተሞላበት ሥጋዊ ሥቃይ ብቻ ሳይሆን፥ ይልቁንም እጅግ ንጹሕና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ራሱ የኃጢአታችንን አሰቀያሚ ቆሻሻ በራሱ ላይ ማድረጉ እንደ ሆነ እናውቃለን።

ጽድቅና ፍቅር በኢየሱሰ መስቀል ላይ ተገናኙ።

> «እግዚአብሔር በክርሰቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን (በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የተሠራውን) አይቈጥርባቸውም ነበር» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)።

ይህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሆኗል። ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ለሰዎች ሁሉ በሁሉም ጊዜ ብቁ ነው። ይህ ለእኛ የማይገባን የእግዚአብሔር ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ይሁንና ስጦታው የእኔ ሊሆን የሚችለው ሰቀበለውና ስጠብቀው ብቻ ነው።

አንድ ቀራጭ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የሠራውን ትልቅ ሐውልት፥ ከዚያ በኋላ በወረቀት ላይ መልሶ ለማሰፈር ቢሞክር፥ ከባለ ሦስት-ደረጃ ቅርጽ (ወርድ፥ ስፋት፥ ርዝመት) ወደ ሁለት-ደረጃ ቅርጽ (ሰፋትና ርዝመት) መቀየር አለበት። እስኪ ሰውን በተፈጥሮአዊ ችሎታው፥ ሁለት-ደረጃዎችን ብቻ መረዳት ከሚችልና ለእርሱ የወርድ ደረጃ ሊገባው የሚችለው በመገለጥ ብቻ ከሆነ ፍጥረት ጋር አናመሳስለው። ለሰው ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንገዶቹ ከሰው የአመለካከት አንጻር ማብራራት ስንሞክር፥ ሁልጊዜም ከተሳሳተ መንደርደሪያ እንጀምራለን። በተለይም ሃያሰያኑ የኃጢአተኛን ቅጣት እንደ እርማትና እንደ አድሳት መንገድ አድርገው ሲጠቅሱት የሚፈጸመው ነገር ምንድነው? ሰለ ኃጢአት ምንነት ያለውን መለኮታዊ አመለካከት አልተረዱም። ይህን ወደ ጎን የምንተው ከሆነ፥ የሃይማኖት ሥነ- ሥርዓት መፈጸሙ «ለጥቃቅን ስሕተቶቻችን» ማካካሻ ይሆናሉ ወደሚለው ማጠቃለያ የግድ መድረሰ አለብን። ይሁን እንጂ ኃጢአት በሁሉም የተግባራዊ ሕይወት ገጽታዎች በራስ ፈቃድ መመላለስ ሲሆን፥ በሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ኃላፊነቶች የማካለሰ ነገር

መላምት ብቻ ነው። ኃጢአት በማስተዋል እና ባለማስተዋል በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዓመፅ መሆኑ፥ ኃጢአተኛውን ሙሉ በሙሉና ለዘላለም ከእግዚአብሔር ይለየዋል። ያለፈውን ኃጢአት በተመለከተ የሚደረግ ማንኛውም እርማት ቢሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ካልመጣ በቀር የማይታሰብ ነው። ለሰው አሰፈላጊ የሆነው ነገር ከአድሳት የጠለቀ ነው። የስውየው ሙሉ ተፈጥሮ መለወጥ አለበት፡-

> « እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ አርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12፡1-2)።

እኛ በራሳችን ይህን መለወጥ ልናመጣው አንችልም፥ ወይም በሃይማኖታዊ ተግባሮች ሊመጣ አይችልም። ይህ በጸጋው የሆነ የእግዚአብሔር የማዳን ውጤት ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ መመልከት የሚያሻን አንድ የመጨረሻ ነጥብ አለ። የእግዚአብሔር ቅጣት ዓላማ ኃጢአተኛውን ለማረም ከሆነ፥ ኃጢአተኞች ይህን ቅጣት በሚቀበሉበት በፍርዱ ቀን ምን ፋይዳ ሊኖረው ይችላል? የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ ብንተውና በስፍራውም ሃይማኖትን ብንተካ፥ ራሳችንን በማታለል ከእግዚአብሔር መለየትን እንመርጣለን። በዚህ ዓይነት ገሃነመ እሳት ቅጣት ሳይሆን፥ የራሳችን ምርጫ ነው። ከእርሱ ጋር የነበረውን ግንኙነት መታጣት መልሶ ለመመሥረት በእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛ አማራጭ ስርየት ነው። ይህ ሁሉንም የሕይወታችን ገጽታ የሚመለከትና የሕይወታችንን መለወጥና መቀየርን የሚያስከትል ነው። ስው በራሱ ችሎታ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደሚችል የተያዘው ምናብ፥ ቀደም ብለን እንደ ደረስንበት ብቸኛውና ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው። ይህ ኃጢአት ሲታወቅና ንሰሐ ሊገባበት አዲስ ሕይወት ይጀምራል። ብዙዎች ግን እጅግ ግራ ስለ ተጋቡና፥ በዚህ ጽንሰ አሳብ ላይ አሰከ መጨረሻው ድረስ ለማሰብ አንኳ ስለሚቸገሩ፥ ኢየሱስንና ሰርየቱን አይቀበሉም።

«ይህ የስርየት አሳብ የተጠነሰሰው ከጳውሎስ የፈጠራ ብልሃት የተነሣ» እንደ ሆነ ክርስቲያኑ ከሚስተር ጁማል በመደነቅ የሚሰማው ነገር ነው። ኢየሱስ በእርግጥ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ፥ ነገር ግን የሞተ እንደ መስለና ስለዚህም እንደ በድን በመቃብር ውስጥ እንደ ተደረገ ይተርካል። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በሱረቱ 4፡157

«አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም»

ከሚለው ከቁርዓን ጋርም በቀጥታ ይቃረናል። የሚስተር ጁማል ዐረፍተ ነገር በሚርዛ ጉላም አሕመድ የተዘጋጀው የአሕመዳውያን እምነት ነው።

የእርሱ አመለካከቶች በሱኒ ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የተነፈጋቸው ቢሆኑም፥ ብዙውን ጊዜ ለገዛ ጥቅማቸው ሲሉ የሚያሰራጯቸው ናቸው። ከዚያም ዘገባው ስለ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡-

> «ሕክምና ከተደረገላቸው በኋላ ቁስሎቹ ዳኑ። በዚህም ጊዜ ከመቃብሩ በመውጣት በምስጢር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተገናኘ። በሮም መንግሥት የሞት ፍርድ የተላለፈበት ስለ ሆነ፥ በሕይወት እንዳለ ቢታወቅ አደገኛ ይሆን ነበር። ማንነቱ ታውቆ ቢሆን ኖሮ፥ እንደገና ይታሠርና ለሁለተኛ ጊዜ ይፈረድበት ነበር። ደቀ መዛሙርቱስ ክርስቶስ እንዳልሞተና ዳሩ ግን ሕያው እንደ ሆነ እንዴት ይገልጻሉ? በሌላ በኩል አይሁዶች ኢየሱስ እንደ ሞተ በደስታ አውጀዋል። ምክንያቱም እርሱ የተረገመ አስመሳይ ስው ነበርና ነው። ‹በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር የተረገመ ነውና› ይላል ዘዳግም 21፡23።»

ይህ ግምት ስለ ኢየሱስ ሞት ብቸኛ ዝርዝር ስለሆነው ለአዲስ ኪዳን የዓይን ምስክሮች ዘገባ ሙሉ ለሙሉ እንግዳ ነው።

> «አይሁዳውያን ኢየሱስን ለመስቀል የፈለጉበት ዓላማ ሐሰተኛ መሆኑን ለማሳየትና በዚያውም የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት ለማረጋገጥ ነበር። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም ምን እንደሚያደርጉ ወይም እንደሚናገሩ አያውቁም ነበር። በማመንታት ላይ ነበሩ። በመስቀል ላይ እንደ ሞተ ማመኑ «በእግዚአብሔር የተረገመ ነው» የሚለውን እምነት ያጠናክረዋል። በሕይወት እንዳለ ማወጁ ደግሞ

> የባሰ አደገኛ ነበር ... እዚህ ላይ ነበር የጳውሎስ የፈጠራ ችሎታ መሥራት የጀመረውና ደቀ መዛሙርቱ ያልተቃወሙትን የብልሃት ዕቅድ የወጠነው። ያልተቃወሙትም ከነበሩበት ቀውጢ ሁኔታ የሚወጡበት ብቸኛው መንገድ ይኸው መስሎ ስለ ታያቸው ነው። ጳውሎስ ኢየሱስ ያለ ጥርጥር የተረገመ ሞት ሞቷል፥ ዳሩ ግን እርሱ ራሱ ንጹሕ ሆኖ ላለ የሰዎችን የኃጢአት መርገም በትከሻው ላይ ተሸከመ፤ ይህ ዝናውን የሚያጎድፍበት አይደለም ይልቁንም እጅግ የከበረ ሥራ ነው የሚል ጽንሰ-አሳብ አቀረበ። ስለ ሆነም ክርስቲያኖች ዛሬ ቢያንስ ለአይሁዶች የሚሰጡት መልስ አላቸው። ይህ ጽንሰ-አሳብ በመጀመሪያ ለአይሁዶች ምላሽ እንዲሆን የተዘጋጀ ይሁን እንጂ ቀስ በቀስ ዛሬ በክርስቲያን ሚስዮናውያን በመሰበክ ላይ ወዳለው የስርየት ትምህርት አድጓል።»

ስለ ሚስተር ጁማል የተለየ ዓይነት መልእክት ምንጮች በበለጠ ለማወቅ እንሻለን። በተጨማሪም በፕሮፌሰር ዶክተር አርኖልድ ሜየር ከተጻፈው «ኢየሱስ ወይስ ጳውሎስ» ከተሰኘው መጽሐፍ ይጠቅሳል፤ የሚከተለውንም ይነግረናል፡-

> «ፕሮፌሰሩ የኢየሱስ አምላክነትና ስርየት ምንጫቸው ከጳውሎስ ዘንድ የሆነ ጭፍን አምነቶች እንደ ሆኑ በማያጠራጥር መንገድ ያረጋግጣል። «ኢየሱስና ሐዋርያቱ» ይላሉ ፕሮፌሰሩ «ስለ እነዚህ ትምህርቶች የሚያውቁት አልነበራቸውም።» ሚያንደር «የቤተ ክርስቲያንና የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ» በተሰኘው መጽሐፉ፥ «የስርየት ትምህርት እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ዛሬ በክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እንደሚታመነው ባለው መልኩ ግልጽና ጉልህ ሆኖ አልተቀናበረም ነበር» ብሏል።
>
> «እንዲሁም በታልሙድም ሆነ በቶራ ውስጥ ስለ ስርየት የተጠቀሰ ምንም ነገር አናገኝም።»

የእነዚህን አባባሎች መሠረተ ቢስነት ቀጥለን ለማሳየት እንወዳለን።

1. እንደ ክርስቶስ ሕይወት በሚገባ በመረጃ የተደገፈ አንድም የጥንታዊ ከስተት የለም። የታሪክ ሰዎች የአዲስ ኪዳንን የመረጃ ተአማኒነት

የሚጠረጥሩበት ምንም ምክንያት የላቸውም (ከገጽ 145 ጀምሮ ተመልከት።)

2. ስለ ስቅለቱ ከውስጣዊ መረጃ በተጨማሪ በሌሎችም የዘመኑ ጽሑፎች ውጫዊ መረጃ አለ (ከላይ እንደተመለከተው)።

3. ከላይ የተጠቀሱትን መግለጫዎች የጻፈው ሰው ምሁር ብቻ መሆኑን ስለምናውቅ ሐቀኝነቱን ለመጠራጠር እንገደዳለን። ጳውሎስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቦማበር እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ለማቀናበር ሴራ አድርጓል ሲል ስጠቀሰው ምላሽ ለመስጠት፥ ጳውሎስ እስከ ተለወጠበት እስከ 36 ዓ.ም. አካባቢ ወይም ክርስቶስ ከሞተ ከ6 ዓመታት በኋላ የክርስቲያኖችን ቤተ ክርስቲያን ያሳድድ እንደ ነበር አንመለከታለን። ከዚያም በኋላ ብቻውን በአረቢያ አገር ውስጥ ለሦስት ዓመታት ተቀመጠ። ስለ ሆነም በትንሣኤ፥ ዕርገትና ጳውሎስ የማስተማር አገልግሎቱን በአንጾኪያ (በበርናባስ ተጠርቶ) በጀመረበት ጊዜ መካከል የአሥር ዓመታት ልዩነት ነበር። በመሆኑም «የብልሃት ዕቅዱ» ከታሪክ አንጻር ተቀባይነት አይኖረውም።

4. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ እኛ እርግማን በመቀበል «በእግዚአብሔር የተረገመ» ሆነ። «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላትያ 3፡13)።
የዓለሙ ኃጢአትና የኃጢአት መርገም በእርሱ ላይ ነበረ።

5. ሚስተር ጁማል ፕሮፌሰሮችንና የትርጓሜ አዘጋጆችን ሲመርጡ፥ በክርስቲያኖች ዘንድ ምንም ዋጋ የማይሰጣቸውንና ትምህርቶቻቸውንም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የማይመሠርቱትን ባለ ለዘብተኛ አቋሞቹን ነው። «እንደ የኢየሱስ አምላክነትና ስርየት ዓይነቶቹ ጭፍን እምነቶች ማረጋገጫዎች ምንጫቸው ጳውሎስ ነው» የሚለው ብሒል ፍጹም ትርጉም የማይሰጥ ነገር ነው። ይበልጥ ትርጉም የማይሰጠው ደግሞ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ስለ እነዚህ ትምህርቶች የሚያውቁት አልነበራቸውም የተባለው ነው። «ስርየት» የተባለው ቃል ከክርስቶስ ዘመን በፊት ወደ ሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ በቆየው ብሉይ ኪዳን ውስጥ 79 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ተጽፎአል።

እንደ አጋጣሚ «ስርየት» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የተጻፈው።
«አሁን መታረቁን (ስርየቱን) ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን» (ሮሜ 5፡11)።

የዘሌዋውያን መጽሐፍ (1500 ዓ.ዓ) 16ኛው ምዕራፍ በሙሉ ለ«ስርየት ቀን» የተሰጠ ሲሆን በ17፡11 ደግሞ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡-

«የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተስርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።»

የእስልምና ባህል ቁርባን የማቅረቡ ልማድ መሐመድ ከመዲና አይሁዶች ጋር ከሄጁራው በኋላ በመጀመሪያው ዓመት የፈጸመው ከዚህ ከስርየት ቀን እንደሚጀምር ይናገራል።

የዘጸአትና የዘሌዋውያን መጻሕፍት በተለይ በስርየት ዘገባዎችና ትምህርቶች ላይ የሚያተኩሩና በእግዚአብሔር ሕግ ላይ መተላለፍን ባደረገው አማኝ ምትክ በሚሆነው መሥዋዕት አስፈላጊነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ተላላፊው መሥዋዕቱን ወይም የኃጢአቱን ማስተስረያ ወደ መሠዊያው በማቅረብና በመሥዋዕቱ ራስ ላይ እጁን በመጫን መናዘዝ ነበረበት፥ ከዚያም መሥዋዕቱ ይታረዳል። ይህም የተላላፊው ጥፋቶች በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል አስከፊ እንደ ሆኑና ለዚሁም የሚገባው ቅጣት ብቻ መሆኑን ያሳየዋል። በእርግጥ «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነው» (ዕብራውያን 9፡9-19፤ 10፡1-4)። ዳሩ ግን እነዚህ መሥዋዕቶች በኢየሱስ ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት አስቀድመው በጥላነት አመልክተዋል።

የስርየት ትምህርት በማንኛውም ጊዜ በክርስቶስ በፍጹም አልተሰበከም ተብሎ የሚነገረውም እውነት አይደለም። የዚህ መንስኤው የሃያስያኑ መሐይምነት ይሁን ወይንም ቅጥፈት እርግጠኞች አይደለንም። ማቴዎስ 20፡28ን እንጠቅሳለን፡-

«እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።»

«ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የእዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» (ማቴዎስ 26:28)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3:16)። (እንዲሁም «የእግዚአብሔር ልጅ» በሚለው ርዕሰ ሥር ያለውን ማስታወሻ ተመልከት ገጽ 139።)

«ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ... እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» (ዮሐንስ 6:51)።

«መልካም እረኛ ነፍሱንም ስለ በጎቹ ያኖራል ... ነፍሴንም ስለ በጎች እኖራለሁ ... እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም» (ዮሐንስ 10:11፥ 15 ና 18)።

ወደ ብሉይ ኪዳን በመመለስ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የኢሳይያስ 53ን ትንቢት እናገኛለን፡-

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል ... እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን ... እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ... ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመታ ... እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ ... የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።»

በመጨረሻም ከሃያሊያኑ ዘንድ ስርየትን በተመለከተ ከተሰነዘሩት የመሚገቻ ጥያቄዎች ሁለቱን ለመመለስ እንወዳለን፡- «የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለክርስቲያኖች ያደረገላቸው ነገር በትክክል ምንድነው?»

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

«በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን

ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ» (ገላትያ 3:13-14)።

«አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና ... ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ...በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» (ኤፌሶን 2:13-16) (ጥሉ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መሆኑ ነው)።

«ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ ... የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ክዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል» (ቲቶ 2:11-14)።

ሌላው ጥያቄ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

«መሥዋዕቱ በክርስቶስ በሚያምኑና ሥጋ ወደሙን በሚካፈሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለኃጢአት የጥላቻ ስሜት አሳድሯል ወይስ ክፉትን ለማድረግ ያለውን ዝንባሌ ገድሏል?»

በማጠንከር የምንስጠው ምላሻችን መቼም እዎን ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ከዳነ በኋላ በኃጢአት ተዘፍቆ አይኖርም። እውነተኛ ክርስቲያን ማለቱ ነው (ክገጽ 193 ጀምሮ)። በሕይወታቸው ይህ የማይሆንባቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ግብዞች በማለት ይጠራቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም አዲስ ኪዳን በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ተግሣጾች እሉት፡-

«ከኃጢአት እርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ተገዛችሁ» «እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ»

«ኃጢአት አይገዛችሁምና» «ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት ንኖራለት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?» (ከሮሜ 6)።

«በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም» (ሮሜ 8፡8-9)።

«ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ ኣርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ» (ገላትያ 5፡13)።

«ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቊጠር» (ፊልጵስዩስ 2፡3)።

«እውነተኛ ... ጭምትነት ... ጽድቅ ... ንጹሕ ... ፍቅር ... መልካም ወሬ ... በጎነት ... ምስጋና ... እነዚህን አስቡ» (ፊልጵስዩስ 4፡8-9)።

«ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ... ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ... በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማስረያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» (ቈላስይስ 3፡12-14)።

ሌሎች ብዙ ክፍሎችንም መጥቀስ ይቻል ነበር።

ይህ ማለት ግን ክርስቶያኖች ኃጢአት አልባ ናቸው ማለት አይደለም። ዳሩ ግን በጣም አናሳ የሆኑትን ሳይቀር፥ ኃጢአትን ይጠላሉ፤ በኃጢአት የተሞላ ሕይወትም አይመሩም። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ቢረቱለትም እንኳ በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፡-

«ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1፡10)።

እንግዲህ የክርስትናን እምነት እየተከተለ የግብረ ገብነት ኑሮ ስለ ራቀውና የሞራል ውድቀት ስለ ተሚነው የምዕራቡ ዓለም ምን እንላለን? በርካታው

ሕዝብ የቤተ ክርስቲያን አባልነት ካርድ እንዳለው ከመናገሩ ወይም እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ እንዳለ ከማመኑ የተሻለ ነገር የለውም። ይህ የክርስትና እምነት አይደለም! እነርሱን ክርስቲያኖች ብሎ መጥራት የአዲስ ኪዳን ትርጉሙን ማሳጣት ማለት ነው። ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተሰጠና በቃሉም የሚኖር ነው።

በመደምደሚያም ስርየት ማለትም የእግዚአብሔርና የሰው መታረቅ ከመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ጀምሮ መሥዋዕቱ በመስቀል ላይ እስከ ተፈጸመበት ጊዜ ድረስ የእግዚአብሔር ጥሪ በመሆን በሥራ ላይ የዋለ መሆኑን በመግለጽ ለማጠቃለል እንችላለን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያን አማኞች ሁሉ በክርስቶስ በተሰጠው ስርየት በመጠቀም የክርስትና ሕይወታቸውን መኖር ጀምረዋል። ከዚያም ይህን በር የከፈተላቸውን ክርስቶስን ያገለግላሉ፡-

«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውንም አይቈጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17-21)።

የኢየሱስን አምላክነትና ልጅነት በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

የአክስፎርድ የሪፖን ሆል ኃላፊ የሆኑት ሬቨረንድ ኤች. ዲ. ኤ. ሜጀር በ1921 በኦክስፎርድ በተደረገው የሃይማኖት ጉባኤ ላይ የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡-

«የድንግል መውለድ ታሪክ እንደሚጠቁመው በሥጋዊ መንገድ፥ ወይም ደግሞ በኒቂያን ሥነ-መለኮት እንደሚጠበቀው በረቂቅ መንገድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በወንጌላት

ውስጥ አለመናገሩ ግልጽ ሆኖ ሊታወቅ ይገባል። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ሲል፥ የሰው ልጅ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነቱን በሚገልጽበት አኳኋን የአባትና የልጅነት እንዲሁም ግብረገባዊ ዝምድና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሁኔታና እግዚአብሔር በሚሠራባቸው በእነዚህ ግብረገባዊ መመሪያዎች ላይ ለመሥራት ችሎታ አንዳለው በሚገልጽ መንገድ ነው።»

«በዚህ ስብሰባ ላይ ክሊቀ መንበርነት የተቀመጡት፥ የካርላይል ዲን ዶክተር ራሽዳል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር አድርገው እንዲቀበሉ እንዳልፈቀደላቸው በመግለጽ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ አስደንጋጭ ዜና አስተላልፈዋል። ምሁሩ ዲን እንዳስቀመጡት፥ ኢየሱስ በሁሉም ሙሉ ለሙሉ ሰው እንጂ እግዚአብሔር እይደለም» («መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወይስ የሰው ቃል?» በኤ. ኤስ. ኪ. ጁግል)።

አሁንም «ባለ ለዘብተኛ አቋሞቹ» አመለካከታቸውን እንዲገልጹ ተጠርተዋል። ቃላቸው እንዴት ነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማው?

የኢየሱስ መለኮታዊነት የሮማ የጳጳሳት፥ የዲኖች፥ የጳጳሳት ወይም የቀሳውስት አስተሳሰብ አይደለም፤ አስተሳሰባቸው በምንም ዓይነት ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና የሬቨረንድ ኤች ሜጀር እና የዶክተር ራሽዳልም በአርግጥ እንዲሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ክርስቲያኖች መልእክቶችንና ትምህርቶችን በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይወስዳሉ እንጂ፥ አሳባዊ፥ ግላዊና ሰው እንዳሻው የሚተረጉማቸውን ነገሮች አይቀበሉም። ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና በቤተ ክርስቲያን ጭፍን እምነት መካከል ግልጽ ልዩነት ሊኖር እንደሚችል መመልከቱ አስፈላጊ እንደ ሆነ አያለሁ።

የሚያሳዝነው ሙስሊሞች «ሥላሴ»፥ «የእግዚአብሔር ልጅ» ወይም «የክርስቶስ መለኮታዊነት» የሚሉ ዓይነት ቃላት በሚሰሙበት ጊዜ በቁርዓን ውስጥ የሚገኙትን፦

«አላህ አልወለደም፤ አልተወለደምም» (ሱረቱ 112፡3)

የሚሉት ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች በተናጠል ትውስ ይሏቸዋል። እዚህ ላይ ሥላሴን የተረዱት እግዚአብሔር፥ ማርያምና ኢየሱስን (ሱረቱ 5፡116) የሚያጠቃልልና፥ ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ሥጋዊ ውህደት አድርገው ነው። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ነው፤ መሐመድም ሥጋዊ ውህደትን በመቃወሙ ትክክል ነው። እንዲህ ዓይነቱ «ሥላሴ» በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ከትምህርት ላይ አልዋለም፤ ምናልባት ማርያም በውሸት «የእግዚአብሔር እናት» ተብላ በተጠራችበት በመካከለኞቹ ዘመናት በተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ካልሆነ በስተቀር። መጽሐፍ ቅዱስን አለማወቅ ብዙውን ጊዜ ሙስሊሙን ወደ ተዛባ መደምደሚያ እንዲደርስ ያደርገዋል።

ቁርዓን እንኳ በተለየ የአገላለጽ ዘይቤው ለክርስቶስ ልጅነቱ መንገድ ይከፍታል። መልአኩ ለማርያም እንዲህ ሲል ተናገራት፦

«እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ፥ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት። (በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ኾኜ፥ አመንዝራም ሳልኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች። አላት፦ (ነገሩ) እንደዚህሽ ነው፤ ጌታሽ፦ አርሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ ለሰዎችም ታምር፥ ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው አለ፤ (ነፋባትም)» (ሱረቱ 19፡19-21)።

«ሰሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፥ በዚህ ዓለምና በመጪረሻውም ዓለም የተከበረ . . .» (ሱረቱ 3፡45)

በሱረቱ 19 ክኢየሱስ እናት ጋር ተዋውቀናል። «ይኼ ለእኔ ቀላል ነው» በሚለው ሐረግ እንደ ተመለከተው እግዚአብሔር የቅዱሱ ልጅ የአባት ምሳሌ ነው። ይህ በሥጋዊ ውህደት ስላለመፈጸሙ ዳሩ ግን በቅዱስ መንፈስ እንደ ሆነ እንስማማለን። የሰውን መንፈስ ከራሱ ክሰውየው ለይቶ ለማየት ስለማይቻል፥ የንጹሑ ጽንስ ተአምር ተፈጸመ፤ «ቅዱሱ ልጅ» ኢየሱስም ተወለደ።

ቁርዓን የኢየሱስ ክርስቶስን የተለየ መሆንና በምድር ላይ ከኖሩት ክሌሎች ሰዎች ሁሉ የሚወዳደረው ያለመኖሩን ሐቅ በምንም ዓይነት አያናንቅም።

1. ክድንግል ተወልዷል (ሱረቱ 19፡16-35)።

2. እርሱ መሲሕ ነበር (ሱረቱ 4፡171)። ቁርዓን መሢሕ ምን እንደ ሆነ አያብራራም። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሙ ተቀባይነት አግኝቷል ብለን እንገምታለን። አስቀድሞ የተነገረውና ተቀባይነት ያገኘው የመሢሑ ሥራ ነፃ የማውጣትና የማዳን ተግባር ነው።

3. እርሱ ከአግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መንፈስ ነው (ሱረቱ 4፡171)

4. እርሱ የአግዚአብሔር ቃል ነበር (ሱረቱ 4፡171)። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት ነው (ዮሐንስ 1፡1-14)።

5. አንከን አልነበረበትም (በማርማዱክ ፒክታል የተተረጎመ) ወይም እርሱ ቅዱስ ነበር (በዩሱፍ አሊ የተተረጎመ) (ሱረቱ 19፡19)። ይህ ከማንኛውም ሌላ ስው ወይም ነቢይ በተቃራኒ የተነገረ ነው፡-

አዳም ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 2፡36፤ 7፡22-23)።

አብርሃም ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 26፡82)።

ሙሴ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 28፡15-16)።

ዮናስ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 37፡142)።

ዳዊት ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 38፡24-25)።

መሐመድ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 47፡19፤ 48፡1-2፤ 33፡36-38)።

6. በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም የተከበረ ነው (ሱረቱ 3፡45)።

7. በአግዚአብሔር ወደ ስማይ ተወስዷል (ሱረቱ 4፡158)።

8. ለፍርድ አንደገና ወደ ዓለም ይመጣል (ሱረቱ 43፡61 በዩሱፍ አሊ የተተረጎመ እና ሚሽካት 4 ገጽ 78-80)።

ሌላ አመለካከት ከቁርዓን መውሰድ ይቻላል። እርሱም በትክክል እንደሚከተለው ይዘግባል፡-

«አላንተ ስዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ፤ ለርሱም አድምጡት፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት)፥ ዝምብን ፈጽሞ አይፈጥርም፤ ለርሱ (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳ፥

(አይችሉም)፤ አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም» (ሱረቱ 22፡73)።

ሕይወትን ለመፍጠር የሚችለው አግዚአብሔር ብቻ አንደ ሆነ ሁላችንም እንስማማለን። አስቲ አንግዲህ በዚህ አመካኝነት ወደ ኢየሱስ እንመልከት፡-

«እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ አንደ ወፍ ቅርጽ አፈጥራለሁ፤ በርሱም አተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፥ ለምጻኛንም፥ አድናለሁ፤ ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ የምታምኑ አንደኾናችሁ ለአናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት» (ሱረቱ 3፡49)።

ከምንባቡ ሕይወትን አና ጤንነትን የፈጠረው (በሞቱ ስዎችና በወፎች) ኢየሱስ አንደ ነበረ አንረዳለን። ከምንባቡ ላይ በአግዚአብሔር የመፍጠር ሥራ አንደ መሣሪያ ሆኖ አንዳላገለገለ ሳይሆን፥ ይልቁንም ራሱ ፈጣሪ አንደ ነበረ ግልጽ ነው።

በብዙ ቁጥሩ ውስጥ ስለ አግዚአብሔር አንድነት የተጠቀሰው ሌላ አስደሳች አሳብ በዶከተር ኤ. ሀቅ ቀርቧል፡-

አግዚአብሔር በራሱ ተፈጥሮም አንኳ ፍጹም አንድነት ካለው፥ የተፈጥሮውን ባሕርያት በተመለከተ ጥያቄ ይነሣል። እነዚህ ባሕርያት የአግዚአብሔርነቱ ባሕርያት አካል ናቸው፥ ወይስ ከአርሱ ውጭ ናቸው? እነዚህ በአሱነቱ ባሕርይ ውስጥ የሚጠቃለሉ ከሆኑ፥ አንግዲህ በዘጠና ዘጠኝ ደረጃዎች የሚገልጽ አንድ የአሱነቱ ባሕርይ አለን ማለት ነው (የአላህን ባሕርያት በተመለከተ)። የአግዚአብሔር ፍጹም ዘላለማዊ አንድነቱ በዚያው ውስጥ ለበርካታነቱ ለፍራ መስጠት አለበት። በሌላ በኩል፥ ደረጃዎቹ ከአግዚአብሔር ተፈጥሮ ውጭ ከሆኑ፥ መለኮታዊ አይሆኑም። በዚህ ረገድ ውቦቹን ስያሜዎችን ሁሉ ለአላህ መስጠቱ ተፈጣሪዎችን ከፈጣሪ ጋር ማስተካከል ይሆናል። ይህ በአስልምና አምነት መሠረት፥ በአግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ከሁሉም የከፋ ኃጢአት ነው። ስለዚህ

በአግዚአብሔር ውስጥ በብዙ ደረጃዎች ያለ አንድ ተፈጥሮ የሚለው የመጀመሪያ አማራጭ ሊረታ ይገባዋል።

ሌላው የአግዚአብሔርን ፍጹማዊ አንድነት በተመለከተ የሙስሊም የአስተሳሰብ ችግር የሚከሰትው፥ ከራእይ ወይም ከመገለጥ ዓውድ አንጻር ነው። ቁርዓን ስለ መገለጥ የሚናገረው በሰማይ እንደ ተዘገበና መልአኩ ገብርኤል ለነቢያት እንዳመጣላቸው አድርጎ ነው። ይህ ዘገባ ወይም በሰማይ ያለው የመጀመሪያው መጽሐፍ «የመጽሐፉ እናት» (13፡39) ተብሎ ይጠራል። ይህ የሰማዩ መጽሐፍ መገለጥን ሁሉ፥ እንዲሁም የነገሮችንና የክስተቶችን ዘገባ ሁሉ ያካትታል (57፡22፤ 17፡37፤ 6፡38)። የሙስሊም ሥነ-መለኮት ራሱ፥ «ይህ መጽሐፍ በሰማይ ለዘላለም የኖረ ነው ወይስ የተፈጠረ ነው?» የሚልን አሰቸጋሪ ጥያቄ ሰንዝሯል። ቁርዓን ራሱ በዚህ ነጥብ ላይ ምንም መረጃ አይሰጥም። ይሁንና የኋለኛው አርቶዶክስ ሥነ-መለኮት ስለ መጽሐፍ አናት ዘላለማዊነት ተናግሯል። አል-ጋዛሊ ይህን የአግዚአብሔር ዋንኛ ባሕርይ አካል አድርጎ አቅርቧል።

የመጽሐፉ አናት ዘላለማዊ ከሆነች፥ አንግዲህ በአግዚአብሔር ውስጥ ወይም አጠገብ መኖር አለባት። መጽሐፏ ከአግዚአብሔር ዘንድ ካለች፥ በሁለት አማልክት ማመንን የሚያመለክቱ ሁለት ዘላለማዊ ነገሮች አሉ ማለት ነው። አል-ጋዛሊ ይህን ችግር ሰለ ተገነዘበ፥ ሌላውን አማራጭ ወሰዷል። ይህም መጽሐፏ ከአግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ አንዳለች አድርጎ መቀበል ነው። አዚህ ላይ ክርስትና ከአባቱ ጋር አንድ አምላክነት ባለው በአግዚአብሔር ቃል፥ ወይም ልጅ (ሱረቱ 4፡171) ላይ ያለው የክርስትና አምነት፥ በአግዚአብሔር ዘንድ ካለው የተመዘገበ መጽሐፍ ያነሰ ትርጉም ይሰጠው አንደ ሆነ ሙስሊሙ ራሱ አንዲፈርድ ሊያበረታታው ይችላል። ለዝንጉነት አንደ ተጋለጡት የሰው ልጆች፥ አግዚአብሔር የራሱን መግለጫዎች መዝግቦ ማቆየት አያሰፈልገውም። ዳሩማን ነገሮች ሁሉ በቃሉ ተደግፈዋል (ዕብራውያን 1፡1-3)። ይኸው ቃል ወይም የአግዚአብሔር ልጅ የፍጥረት፥ የራእይና የደኅንነት ምንጭ ነው። እርሱም በተወሰነ የታሪክ ምዕራፍ ላይ «ሥጋ ሆነ ጸጋንና

እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ አንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን› (ዮሐንስ 1፡14)።

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ብርሃን፥ አንድ ሰው ኢየሱስ ተራ ሰው ወይም ነቢይ አንደ ሆነ ሊናገር ይችላልን? አንዲህ ያሉ ባሕርያትና ምግባሮች ያሉት ነቢይ የት አለ?

ሙስሊሞች የክርስቶስ ልጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ከአማኞች ወይም ከመናፍስት «ልጅነት» ጋር የሚምታታባቸው ይመስላል። ቅዱስ ዮሐንስ የጻፈው ወንጌል በ3፡16-18 ላይ ስለ አግዚአብሔር አንድያ ልጅ፥ ወይም ብቸኛ ልጅ ይናገራል፡-

> «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አንዲኖረው አንጂ አንዳይጠፋ አግዚአብሔር አንድያ ልጁን አሰኪሰጥ ድረስ ዓለሙን አንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ አንዲድን ነው አንጂ፥ በዓለም አንዲፈርድ አግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በአግዚአብሔር ልጅ ሰም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።»

«አንድያ» የሚለው ቃል ከ1611 ዓ.ም. ትርጉም የተወሰደ ሲሆን፥ ትርጉሙ ዛሬ በተለየ መንገድ ነው የሚገለጸው። አንድ ሕያው የሆነ ቋንቋ ይለወጣል። በመጀመሪያዎቹ የግሪክ መዛግብት ውስጥ ቃሉ «ሞኖጀኔስ» («ሞኖ» = አንድ፥ «ጀኔስ» = ተወለደ) ነው። የማሰረገዝን ድርጊት አይጠቁምም።

ከዚህ በተጨማሪ፥ ፍርድ ሁሉ ለልጁ አንደ ተሰጠ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንረዳለን፡-

> «አብ በራሱ ሕይወት አንዳለው አንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት አንዲኖረው ሰጥቶታልና። የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው። በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ» (ዮሐንስ 5፡26-29)። («የሰው ልጅ» የሚለው ሰያሜ በ500

ዓ.ዓ. በነቢዩ ዳንኤል የተነገረ ነው (ምዕራፍ 7፡13፤ 10፡16)። ይህ ማን ሊሆን እንደሚችል ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለም።)

ክርስቶስ በአይሁድ የመሰደዱ እውነተኛ ምክንያት ይኸው ነው፡-

> «እንግዲህ ስንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፡- እግዚአብሔር አባቱ ነው ስላለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር» (ዮሐንስ 5፡18)።

ሙስሊሞችንና ሂዩማኒስቶችን (የሰብአዊ ፍጡርን ክቡርነት የሚያነሳ ፍልስፍና ተከታዮች) የክርስቶስን እምላክነት እንዲክዱ በተደጋጋሚ የቀሰቀሱአቸው ምክንያቶች እሱ። ክርስቶስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ፡-

> «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» (ማቴዎስ 4፡10)

ብሎ እንደ መለሰ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይጠቅሳሉ። ይህ ዐረፍተ ነገር የክርስቶስን መለኮታዊ አለመሆን ያረጋግጣል ተብሎ ተገምቷል። ግና ክርስቶስ ሰይጣንን ማምለኩን አጥብቆ ስለ ተቃወመ ነጥባቸው የቱ ላይ እንደ ሆነ ለማየት ይሳነናል።

ከዚያም ኢየሱስ ለሚመረምረው አለቃ የሰጠው ምላሽ በሉቃስ 18፡19 ላይ እንደሚከተለው ተጽፎአል፡-

> «ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።»

በመጀመሪያ ዕይታ የተጠቀሱት ምንባቦች ኢየሱስ ክብርንና ማዕረግን ያልፈለገው የማይገቡት በመሆናቸው እንደ ሆነ ያስመስላሉ። ዳሩ በእርግጥ እውነቱ እንደዚህ ነውን?

> «የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ።»

ይህንንም ያደረገው ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሆኖ ላለ ነው (ፊልጵስዩስ 2፡6-7)። ይሁንና ሁኔታውን መመልከት የሚገባን በሚከተለው ዓውድ ሊሆን ይገባዋል። ጠያቂው ኢየሱስን «ቸር መምህር» (አስተማሪ፥ ሺኺ)

ብሎታል። ነገሩን ወደ ሌላ አቅጣጫ በማመልከት ኢየሱስ፡- «መምህር ቸር አይደለም። ቸር እግዚአብሔር ብቻ ነው። ቸር ብለህ እኔን መጥራትህ ማለፊያ ቢሆንም እንኳ፥ እኔ ከመምህር በላይ ነኝ» ማለቱ ነበር።

ሌላም በኢየሱስ ላይ የተደረገ ውስንነት አለ፡-

> «አብ ሊያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም ... እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» (ዮሐንስ 5፡19፥30)።

በግልጽ የሚታየው የክርስቶስ ሁሉን አለማወቅ ብዙ ሃያሲያንን ወደ እንድ መደምደሚያ መርቷቸዋል። እንዲህም ሲሉ ይጠቅሳሉ፡-

> «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም» (ማቴዎስ 24፡36)።

> «(እግዚአብሔር) ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና። ነገር ግን፡- ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡27-28)።

እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ከሠፈው የቅዱሳት መጻሕፍት ዐውድ አንጻር ቢታዩ፥ ሁሉ ነገር ተገቢ ቦታውን ይይዛል። ክርስቶስ በሰብአዊ አካል በነበረ ጊዜ ባመዛኙ በሰው ላለው ዓይነት ውስንነት ተዳርጓል። ለአብነትም፡-

በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ መወሰን ነበረበት። እንደ ሰዎች ስሜት፥ የእውቀትም ውስንነት ነበረው። ምንም እንኳ ከሰብአዊ ችሎታ በላይ የሆኑ ተአምራት ቢያደርግም፥ ሙሉ ለሙሉ ሰው ነበር።

እንግዲህ ክርስቶስን በተመለከተ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ባሕርይ ተመሳሳይ ከሚመስሉት ከሁለቱ አማቦች በስፋት እንደሚለይ እንመለከታለን። ሁለቱ አማቦችም፡-

1. «መናፍስት» (ኢዮብ 1:6፤ 2:1 እና ዘፍጥረት 6:2) እና

2. «የእግዚአብሔር ልጆች» እነዚህም ከእግዚአብሔር ዘንድ [illegible]ይቅርታውን ስጦታ የተቀበሉ ናቸው (ዮሐንስ 1:12፤ 3:8፤ ኤፌሶን 1:5፤ ሮሜ 8:14፤ ወዘተ.)።

የክርስቶስ [illegible]ላክነት በሁለቱም ኪዳኖች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እንደ ተቀመጠ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ሥላሴን በተመለከተ የብሉይ ኪዳንን መረጃ በሚከተለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን። አሁን ግን ወደ አዲስ ኪዳን መረጃ መመልከት አለብን፡-

«በመጀመሪያው ቃል (ሎጎስ) ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም አግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም . . . ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ለ[illegible]ም [illegible]ባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐንስ 1:1-5 እና 14)።

«በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐንስ 1:10-12)።

«እርስዋንም፡- ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል አላት። ከአርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው፡- ኃጢአትን እንኳ የሚያስተሰርይ ይህ ማን ነው? ይሉ ጀመር» (ሉቃስ 7:48-49)።

«እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር . . . ፈቅዶአልና። በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል» (ቈላስይስ 1:19 እና 16-17)።

«ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ . . .» (ዕብራውያን 1:2-3)።

«እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት አንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በስውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» (ፊልጵስዩስ 2:6-7)።

«እነርሱ አስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተሰፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ (መሢሕ) በሥጋ መጣ። አርሱም [ክርስቶስ] ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን» (ሮሜ 9:4-5)። (እዚህ ላይ ትርጉሙ የሚወሰነው በምንጠቀመው ሥርዓተ-ነጥብ ሲሆን፥ ይህም በመጀመሪያዎቹ መዛግብት ላይ አልነበረም።)

«ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው» (2ኛ ቆሮንቶስ 4:4)።

«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (የሐዋርያት ሥራ 20:28)።

«የእግዚአብሔርም ልጅ አንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» (1ኛ ዮሐንስ 5:20)።

«በዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ክዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥

መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል» (ቲቶ 2፡11-14)።

ምናልባት እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የራሱ የክርስቶስ ቀጥተኛ ቃላት አይደሉም የሚል ተቃውሞ ይነሣ ይሆናል። ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና ይህን ለማጠናከር የክርስቶስን ቃላት ቀጥለን እንጠቅሳለን፡-

«አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል» (ራእይ 21፡6-7)።

«ከዚያም በኋላ ቶማስን (ከትንሣኤ በኋላ)፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፡- ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው» (ዮሐንስ 20፡27-29)።

ቶማስ ያመነው ምን ነበር? ጌታው ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ አምኗል። ክርስቶስም እንዲያምን አበረታታው እንጂ፥ ይህን እውነት አልካደም። ቶማስን ወይም ደግሞ ዛሬ እኛን ለማታለል አልፈለገም።

«እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። ኢየሱስ፡- ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፡- ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም ስለ ስድብ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት» (ዮሐንስ 10፡30-33)።

ኢየሱስ ሰው ብቻ መሆኑን በመግለጽ ከድንጋይ መወገር ለማምለጥ አልሞከረም። ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ በእርግጥ ይህን ያደርግ ነበር። ይልቁንም የዚህን ተገላቢጦሽ ተናግሯል፡-

«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር።

ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው። ፊልጶስ፡- ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም አለው፡- አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ፡- አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» (ዮሐንስ 14፡6-10)።

ነቢያት ሁሉ እንደ ተራ ሰዎችና ኃጢአተኞች ሲታዩ፥ ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ማስቀመጡ ትልቅ ነገር ነው፡-

ኢየሱስ «ኃጢአት ያላወቀው» ነበር (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

ኢየሱስ «ኃጢአት አላደረገም» (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22)።

ኢየሱስ «ከኃጢአት በቀር... እንደ እኛ...ነው» (ዕብራውያን 4፡15)።

በኢየሱስ «ኃጢአት የለም» (1ኛ ዮሐንስ 3፡5)።

ይህም «ንጹሕ» የማርያም ልጅ በሚናገረው የቁርዓን ክፍል ተጠናክሯል (ሱረቱ 19፡19)።

የእነዚህን ሁሉ ዐረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚያዛባ «ማብራሪያ» የለም። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? የሚከተለው ምዕራፍ መልሱን ይሰጣል።

በሥላሴ ትምህርት ላይ የእስልምና ተቃውሞ

ከዚህ ምስጢር በላይ በተሳሳተ መልኩ ከግንዛቤ ላይ የዋለ ነገር የለም። ገና ከጅምሩ ሥላሴ የሚለው ቃል የሥነ-መለኮት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዳልሆነ ለመግለጽ እንፈልጋለን። እንደ ሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት ከመደንገግ ይልቅ ተጠቁሞ የሚታሰፍና ክሰብአዊ መረዳትም የላቀ ነገር ነው። በግልጽ መቀበል ያለብን ነገር ቢኖር፥ ሥላሴን ለመረዳት ሰው የሚያደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ፥ በማመሳሰል መንገድም እንኳ ቢሆን ከንቱ መሆናቸውን ነው። ለዚህም ቀላሉ ምክንያት የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመረዳት ስለማንችል ነው። ሰው ሊረዳው የሚችለውና ለደኅንነት

የሚያስፈልገው ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተቀምጧል። ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የምንችለው ሁሉ ተገልጿል። ነገር ግን በዚያ መገለጽ የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ገጽታ ለማወቅ እንችልም። ያ ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከአእምሮአችን ያነስ ይሆን ነበር። በዚህም መሠረት በሙስሊም «ሊቃውንት» የሚቀርቡትን እንደሚከተለው ያሉ ደካማ ክርክሮችን አንቀበልም፡-

«በሁሉም የስሌት ሕጎች ሦስት በአንድ ሲባዛ ሦስት ይሆናል። ነገር ግን በክርስትና ስሌት ሦስት በአንድ ሲባዛ አንድ ይሆናል ... እስተውሎታችንን እንዳንጠቀምና የቤተ ክርስቲያንን ጭፍን እምነት ለመረዳት እንዳንሞክር በካህናት ተነግሮናል። ስለዚህም ያ የክርከሩ ዐቢይ ነጥብ ነው። እንድናምን የተጠየቅነውን ነገር ለመረዳት ከአምላክ የተሰጠንን የእስተውሎት ኃይል እንድንጠቀም አልተፈቀደልንም። በእነዚህ ትምህርቶች ላይ ያለን እምነት ዕውር፥ የማይጠየቅ፥ ፍጹም መሆን አለበት! እነዚህን እምነቶች ለመረዳት ብሎ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው፥ በሙሉ ቅንነት ቢሆንም እንኳን ወደ ዘላለም ጥፋት ወረደ ማለት ነው።»

የጥቅሱ የመጀመሪያው ክፍል ደካማ ከሆነ፥ ሁለተኛው ክፍል መርዘኛ ቅጥፈት ነው። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትንሽ እንኳ የሚያውቅ ሰው የትምህርቱ ሁሉ ዓላማ ማሳወቅ እንደሆነ አይስትም፡-

> «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን ... ታውቁ ዘንድ ነው» (ኤፌሶን 1፡17 ና 18)።
>
> «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በአምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይሰጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ክፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌሶን 3፡16-19)።

ተመሳሳይ መልእክት ያላቸው ሌሎች በርካታ ምንባቦች ሊጠቀሱ ይችላሉ። አስተውሎታችንን እንድንጠቀምበት ብንበረታታም ከግንዛቤአችን በላይ የሆኑ ነገሮች ደግሞ አሉ። ሃያስያኑ እንደ ዘላለማዊነት፥ መንግሥተ ሰማያት፥ እግዚአብሔር፥ ወዘተ... የሚሉትን ይቅርና እንደ የትየለሌ ያሉትን ጽንሰ አሳቦች እንኳን እሳማኝ በሆነ ሁኔታ ማብራራቱ እንቆቅልሽ ይሆንባቸው ይሆናል።

እንድ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድቼ ነው ብሎ የሃይማኖት መጽሐፍ የሚጽፍ ከሆነ፥ እድማጮቹ ወይም አንባቢዎቹ ለመረዳት የማይችሉትን ነገር ክመጻፍ እንደሚቆጠብ ጥርጥር የለውም። ይህንንም የሚያደርገው በመጀመሪያ ደረጃ መልእክቱ ለመረዳት የማያዳግት እንዲሆን ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ግን ደራሲው ራሱ ለመረዳት የማይቻለውን ነገር ሊያስተውል ስለማይችል ነው! ሥላሴን ለመረዳት ያለመቻሉ ዋናው ምክንያት «ዝም ብሎ ሰው-ሠራሽ ንድፈ-አሳብ» በመሆኑ ነው የሚለው ወቀሳ ራሱ አሉባልታ ነው።

ብዙ ጊዜ «ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሆነ፥ በማርያም ማኅፀን በነበረ ጊዜ፥ በእራስነቱ ወይም በመቃብር ውስጥ በሆነ ጊዜ ዓለምን የሚያስተዳድረው ማን ነበር?» የሚል ጥያቄ እንሰማለን። እስኪ የሚከተለው ምሳሌ መልሱን ይስጠን፡- የውኃ መቅጃ ባልዲ ተሸክሜ ወደ ውቅያኖስ ወረድሁና ጨዋማውን ውኃ ሞላሁት። በውቂያኖሱ ውስጥ ያሉት ዓሦች ሁሉ ምን ይገጥማቸዋል? ምናልባት በትክክል፡- «ለምን? ይህ ከዓሣው ጋር ምን ግንኙነት አለው?» ትሉ ይሆናል። እኔም፡- «ዓሣ ካለ ውኃ ሊኖር አይችልም - ውኃውም አሁን በባልዲ ውስጥ ነው» ብዬ እመልሳለሁ።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ በነበረ ጊዜ፥ በሁሉም ስፍራ በመገኘት ችሎታው፥ በሌሎችም ስፍራዎች ሁሉ ነበረ።

አንድ ነገር ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። አግዚአብሔርን የሆነው ክርስቶስ አልነበረም። ይልቁንም እግዚአብሔር ክርስቶስን ሆነ። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በሌላ በየትኛውም ስፍራ እስክማይሆን ድረስ ነበር ማለት አይደለም። ያማ እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ውስን ማድረግ ነው። «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)።

ብዙ ጊዜ ግዴለሽነት የሚታይባቸው ዐረፍተ ነገሮች ተሠርተዋል፡-

> «ስለ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቸኛው ጥቅስ የሚገኘው በ 1ኛ ዮሐንስ 5፡7 ሲሆን፡- <የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው፥ ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ> ይላል።»

ሃያስያን እንደሚናገሩት ይህ በጣም ዘመናዊ በሆኑ ቅጂዎች ውስጥ በኢታሊክስ የጽሑፍ አጣጣል ስልት የተጻፈው ጥቅስ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገባ እስክ ተደረገበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ለማስተማር ከምትጠቀምባቸው መካከል አልነበረም። ይህ የሚያመለክተው ክርስቲያኖች በራሳቸው ፈቃድ ጣልቃ እንዳስገቡት ነው። በቀጥተኛ አነጋገር የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ «የክርስትናው አካል የተደረጉት በኒቅያው ጉባኤ» ላይ ነበር። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የትኞቹ መጻሕፍት በሐዋርያት የተጻፉና የትኞቹ ደግሞ ምናብ ወለድና አፈ-ታሪክ ሆነው የተጨመሩ እንደ ሆኑ በከፊል የመረመሩት በዚህ ጉባኤ ላይ ነበር። ይሁንና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከሞላ ጎደል ጠቅላላዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በየትም ሰፍራ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደ ነበሩ መታወቅ አለበት።

ይህ በእስያ፥ በአፍሪካና በአውሮፓ በመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በርካታ ጽሑፎች መረጃ ተደግፎአል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሥላሴ የሚናገረው አንድ ጥቅስ ብቻ እንደ ሆነ የሚናገረው ሂስ ትክክል ነው ወይስ አይደለም?

የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ገጽ በመግለጥ የሚከተለውን እንባለሁ፡-

> «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።»

«እግዚአብሔር» የሚለው ቃልና ጠቅላላው ምንባብ በዕብራይስጥ ስለ ተጻፈና «እግዚአብሔር» የሚለውም የአማርኛ ቃል ስለ ሆነ፥ በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምናገኘው «ኤሎሂም» የሚለውን ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ማለት ኤል ወይም ኤላህ መሆኑ ነው። «ኤሎሂም» ማለት እንግዲህ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት

«እግዚአብሔሮች» ማለት ነው። ትንሽ ፈቀቅ ብለን በቁጥር 26፡- «ኤሎሂም አለ፡- ሰውን . . . እንፍጠር»

> የሚል እናነባለን። እንደገናም በምዕራፍ 11፡7 የሚከተለውን እናገኛለን፡- «ኑ፥ እንውረድ . . . ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው»።

«እኛ» የሚለው ማንን የሚወክል ነው?

መልስ፡- «ኤሎሂም።» ይህን እንዴት እንረዳለን? ይህ የነገሥታቱ ዓይነት የብዙ ቁጥር አጠቃቀም ስልት ነውን? አይደለም፤ እንዲህ ያለ አጠቃቀም በዕብራይስጥ አይታወቅም ነበርና። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ደረጃ በደረጃ ስለሚገልጽ፥ በትምህርቱ ላይ የበለጠ ብርሃን ያረፈው በኋላ ነው። ከዘዳግም 6፡4 ጀምሮ የሚከተለውን እናገኛለን፡-

> «እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።»

ወይም፡-

> «አንተም ያህዌን የአንተን ኤሎሂምን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።»

ይሁንና የሚበልጠውን ብርሃን የሚፈነጥቀው የሚከተለው አጭር ዐረፍተ ነገር ነው፡-

> «አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።»

በዕብራይስጥ እንደሚከተለው ሊነበብ ይችላል፡-

> «ያህዌ ኤሎሄኑ ያህዌ ኢቻድ።»

ቃል በቃል ቢተረጎም ይህን ትርጉም ይሰጣል፡- «ጌታ አግዚአብሔሮቻችን፥ ጌታ አንድ ነው።»

«ኢቻድ» የሚለው ይኸው ቃል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው በኋላ ስለ አዳምና ሔዋን በሚናገርበት ክፍልም ውስጥ አገልግሏል፡-

«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ (ኢቻድ) ሥጋ ይሆናሉ» (ዘፍጥረት 2፡24)።

ያገቡ ሰዎች አንድ ግለሰብ ሳይሆኑ፥ ሁለቱ በአንድነት የተጣመሩ እንደ ሆነ መቼም እንረዳለን። እንደገና በኢሳይያስም በዚህ ትምህርት ላይ የበለጠ ብርሃን ተንጸባርቆበታል። የዚህ ምሥጢር ሙሉ መረዳት ለስውሊገባ በሚችል መልኩ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

«የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም» (ኢሳይያስ 44፡6)።

በተጨማሪም ይህን እናነባለን፡-

«የያህዌን ... ትልቅ በጎነት አሳስባለሁ። እርሱም (ለእስራኤል)፡- በእውነት ሕዝቤ፥ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው አለ ጀሹዋም (ኢየሱስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ዘመን የነበረው ስም ሲሆን፥ ወደ ቋንቋችንም ኢየሱስ በመባል ተተርጉሞአል) ሆነላቸው። በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው... እነርሱ ግን ዓመፁ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው» (ኢሳይያስ 63፡7-10)።

ለጊዜያዊ ጥቅሙ በማሰብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት መጠየቅን እምቢ ላለው ለንጉሥ አካዝ ነቢዩ እንዲህ በማለት ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል፡-

«ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳይያስ 7፡14)።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳይያስ 9፡6)።

አንዳንድ ጊዜ «የኃያሉ አምላክ ድንቅ መካር» ተብሎ መነበብ እንዳለበት ይነገረናል። ይህ እውነት አይደለም! በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መዛግብት ውስጥ «ሼል» ወይ «የ» የሚል ነገር የለም።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 8፡58 መሠረት የሚከተለውን እንግዳ ዐረፍተ ነገር በግልጽ ተናግሯል፡-

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ (ነኝ) አላቸው።» ከዚያም አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ።

ለምን? ምክንያቱም «እኔ ነኝ» የሚለው «ያህዌ» ማለት ስለ ሆነ፥ ከአብርሃም በፊት እኔ ነኝ የሚለው ሰዋሰው የክርስቶስን ዘላለማዊ ሕልውና ያመለክታልና ነው።

ይህ ከብሉይ ኪዳን ጋር ፍጹም የሆነ ኅብረት ስላለው፥ እኛም እንደዚሁ እንቀበለዋለን። በዚህም ሆነ በሌሎች ለፍራዎች በኢየሱስና ስለ ኢየሱስ የሚናገሩትን ዐረፍተ ነገሮች ለመረዳትና በትክክልም ለመገምገም የምንችለው በብሉይ ኪዳን የመገለጽ ብርሃን ብቻ ነው፡-

«አኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐንስ 10፡30)።

«አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው» (ዮሐንስ 10፡33)።

«እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐንስ 14፡9)።

«ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ የእግዚአብሔር አካል እንደ ሆነ ለመናገር ምንም ሥልጣን የላትም» ይላሉ ሚሰተር ጁማል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት መልስ ይሰጣል፡-

«አሕዛብ ለምን ያጕረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፡- ማሰርያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል። በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል። በዚያን ጊዜም በቍጣው ይናገራቸዋል፥በመዓቱም ያውካቸዋል። እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን

ላይ። ትእዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። ለምንኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ። በብረት ብትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ» (መዝሙር 2፡1-9)።

ምንም እንኳ የትኛውም ዓይነት ማመሳሰያ ብቃት የሌለው ምስል ብቻ ቢሆንም፥ የሚከተለው ቀላል ገለጻ ሥላሴን ከአንድ እንጻር ብቻ አንድንመለከተው ያደርገናል፡-

አንድ ጠብታ ውኃ ወደ አንድ ኬሚስት (ተማራማሪ) ውስድና የማምገማ ውጤቱን እንዲያሳውቅህ ጠይቀው። የሁለት እጅ ሃይድሮጂንና የአንድ እጅ አክስጂን ውህድ መሆኑን ይነግርሃል። ይህንኑ የውኃ ጠብታ ለፊዚክስ አዋቂ ብትወስድለት፥ ፈሳሽ ነገር እንደ ሆነ ይነግርሃል። አሁንም ጥቂት በረዶ ውሰድና እንዲሁ ጠይቅ። ኬሚስቱ እንደ መጀመሪያው ሊመልስ፥ ፊዚስቱ ጠጣር ነገር ነው ይልሃል። አሊያም የሙከራ ቱቦ ውስጥ የሞላ እንፉሎት በመውሰድ ከኬሚስቱ ተመሳሳይ ውጤት፥ ከፊዚስቱ ግን የተለየ ውጤት እናገኛለን። ፊዚስቱ ጋስ ነው ይላል።

እጅግ አከብሮት በተሞላ መንገድ በዚህና በሥላሴ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለመጠቆም እፈልጋለሁ። ውኃ፥ በረዶ፥ ወይም ትነት የቅርጽ ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ፥ የሁለት እጅ ሃይድሮጂንና የአንድ እጅ አክስጂን ውህድ እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ እግዚአብሔርም በተለያዩ «መገለጫዎቹ» ሁሉ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ነው። ምናልባት የሕይወት ጀማሪና አቆዩ የሆነውን ውኃ በፈጣሪ አባት፥ ሊጨበጥ የሚችለውን በረዶ አዳኝ በሆነው በልጁ፥ እና ባመዛኙ የማይታየውንና ለመቆጣጠርም የሚያዳግተውን ዳሩ ግን ኃይልን የሚወክለውን ትነት፥ ለሚፈልጉት ሁሉ እግዚአብሔርን በሚገልጸውና ለአማኙም በጽድቅ እንዲኖር ኃይል በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ልንመስል እንችላለን። ይሁንና ሦስቱም የእግዚአብሔር ገጽታዎች እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።

ሌሎችም ማመሳሰያዎች አሉ። ሰው ሥጋ፥ ነፍስና መንፈስ አለው። የፀሐይ ጨረርም ብርሃን፥ ሙቀትና የኬሚካል ኃይል አለው። አሳት፥ ብርሃንና ሙቀት ሦስት ቢሆኑም፥ በሌላ በኩል ሰንመለክት ግን አንድ ናቸው። እንደዚሁም አእምሮ፥ አሳብና ንግግር አንድ ዓይነት ሲሆኑ፥ እርስ በርሳቸው የሚለያዩባቸው ሁኔታዎችም አሏቸው።

ስቅለትን በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

በክርስቲያን-ሙስሊም ውዝግብ ውስጥ ሌላው ከፍተኛ ጉዳይ ሰቅለት ነው። ይህም ብዙውን ጊዜ ሞቅ ያለ ክርክር ያስነሣ ነጥብ ነው። ለክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ድርድር የማይሆን ነገር ነው። ለሙስሊሙም ቢሆን ድርድሩ ቦታ የለውም። ከቁርዓን መሠረታዊ ዐረፍተ ነገሮች አንዱ እንዲህ ይላልና፡-

> «አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በሚሳ) ተመሰለ፤ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ክርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ፥ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው» (ሱረቱ 4፡157-158)።

ዐረፍተ ነገሩ እንደዚህ ከወንጌሉ ሙሉ ለሙሉ በተቃረነ መንገድና በፍጹም «ድጋፍ» ሳይሰጠው እንዲጻፍ ያደረገው ምንድነው? (ገጽ5-7 ተመልክት)። የወቅቱን ሁኔታ መልሶ ማስቀመጡ ቀላል አይደለም። ነገር ግን በመሐመድና በጊዜው በመዲና በነበሩ አይሁዶች መካከል የነበሩ ግንኙነቶች እየሻከሩ መጡ። ከዚህም የተነሣ በሁለቱም ወገኖች መካከል የነበረው አመለካከት የበለጠ ጠላትነትን እያሳደገ መጣ። ክነቢያት ሁሉ በላይ ሰላስቀመጠው፥ ስለ ኢየሱስ በጣም ክፍተኛ አሳብ እንደ ነበረው አያጠራጥርም።

መሐመድ የሚከተለውን እንደተናገረ ተዘግቧል፡-

> «እኔ ከሰዎች ሁሉ በላይ የማርያምን ልጅ እቀርበዋለሁ» «በዚህ ምድራዊ ሕይወትም ሆነ በሚመጣው ሕይወት ከሰዎች ሁሉ በላይ ወደ ኢየሱስ እጠጋለሁ» (ሳሂህ ሙስሊም፥ ቅጽ 4፥ ገጽ 1260-1261)። እንዲህ ያለ ዐረፍተ ነገር እንዲጻፍ የገፋፋው ምንድነው?

ይህ አመለካከቱ ግን ጠላቶቹ አይሁዶች በዚህ ዓይነቱ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ላይ በቂ ኃይል ኖሯቸው ያጠፉታል ብሎ እንዲያስብ አይፈቅድም ነበር።

የከሰተቶችን ቅደም-ተከተል ባስያዙት ሰዎች ዘገባ መሠረት፥ ሱረቱ 4 የተጻፈው በመሐመድ የመዲና ኑሮ አጋማሽ ላይ ነው። ይህም በግምት 5 ኤ. ኤች. ይሆናል። በሃዲስ ውስጥ ከተመዘገቡት ከበርካታ ክስተቶችና ግለታወሻዎች አንጻር፥ ይህ ክፍለ-ጊዜ በአይሁዶችና በሙስሊሞች መካከል ጫን ያለ ተቃርኖ የተስተዋለበት ነው።

አንድ ነቢይ ከተራው ሰው ከፍተኛ የበላይነት ስላለው፥ መከራ መቀበል ወይም መሸነፍ (መሰቅሉ ግለት ለመሐመድ ይህን የመሰለ ነበር) የማይቻል ነገር ነው። ኢየሱስ ለመሐመድ በጣም ትልቅ ሰው ነበር። ይህም ከነቢያት ሁሉ በተለየ መልክ በመሐመድ ትምህርት መሠረት ኢየሱስ ከድንግል የተወለደ ብቸኛው ሰው በመሆኑ፥ ሕያው ሆኖ ወደ ሰማይ በማረጉ፥ ተመልሶ የሚመጣ በመሆኑ፥ ኃጢአት የሌለበት በመሆኑ፥ «የእግዚአብሔር ቃል» እና «ከእግዚአብሔር የመጣ መንፈስ» ተብሎ በመጠራቱና «በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው የተከበረ» በመሆኑ ነው (ገጽ 127-128 ተመልከት)። መሐመድ ክርስቶስ ሊፈጽመው ስለ መጣው የሰርየት ሥራ አልተረዳም ነበር። ያለዚህም የሰርየት ሥራ የመስቀል ላይ ሞቱ ትርጉም ሊሰጥ አይችልም።

ቀጥለን እንደምንመለከተው፥ መሐመድ ከወንጌል ጋር በመጀመሪያ ይዘቱ በፍጹም አልተዋወቀም ነበር። በቁርዓን ውስጥ የምናገኘውና ስለ ኢየሱስ የተገለጸው አውቀት የተገለበጠው ከአዋልድ መጻሕፍት ወይም በጊዜው በዐረቢያ ከነበሩት ኮፕቲክ ክርስቲያኖች (የኢየሱስ ባሕርይ መለኮታዊ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ) በአፈ-ታሪክ መልክ የቀረበና አውነትነቱ ያልተረጋገጠ ነው።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፥ አሁንም በሱረቱ 3:55 እና 19:33 ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን አላማኝና ጥንቃቄ የተሞላበት ትርጉም ለመመልከት እንፈልጋለን፡- «ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ፥ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ» (እንድትሞት አደርጋለሁ)። ይህም እንደ አሊ እብን አባስ፥ አቡዱላህ እብን ሳሊህ፥ ሙአዊሄህ፥ አብን ዒሳቅ፥ ሳልማ እና ዋሃብ እብን ሙናቢህ የመሳሰሉ በርካታ የጥንታዊ መዛግብት ዘጋቢዎች እንደሚረዱት ነው። እንዲሁም «ሰላምም በኔ ላይ ነው፥ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን፥ (እንደገና) ሕያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን» ሲል የተቀመጠበትን ቅደም ተከተል ቸል ልንል አንችልም፡- መወለድ - መሞት - መነሣት።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው ኢየሱስ የመስቀል ሞት ካልሞተ፥ አንግዲህ መቼ ሞተ? በቁርዓን በተገለጸው መሠረት መሞት ነበረበት (ሱረቱ 4:159፤ 19: 33፤ 3:55) (ዶክተር ኤ. ሃቅ)።

ከርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ (በሌላም ስፍራ) ስለ ስቅለት ህልቆ-መላፍርት የሌላቸው ግጠናከሪያዎች አሉአቸው። ከወንጌላት ውስጥ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው ታሪክ የሚያተኩረው በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ በመጨረሻው ሳምንት ስለ ሆነውና ስለ ሞቱ ነው። ይህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የምናገኘው ከስርየት ትምህርትና ከመሥዋዕት አቀራረብ ጋር ሙሉ ለሙሉ የተስማማ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ፥ የመሢሑ የመሥዋዕትነት ሞት በብሉይ ኪዳን ስለ ተተነበየ፥ «ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን»፡-

> «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ አንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን አንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፉን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ እዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ... ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ... እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ» (ኢሳይያስ 53:4-12)።
>
> «ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ ... እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ ... እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» [መዝሙር (22):15-18]።

ዓለማዊ ታሪክ ስቅለቱን ያጠናክረዋል።

የአዲስ ኪዳን መዛግብት በታሪክ ሰዎች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝተዋል። ከ5000 በላይ የሚሆኑና ከእጃችን የሚገኙ መዛግብት እንዲህ ያለ ከፍተኛ ተአማኒነት ስላላቸው፥ የስቅለቱ እውነታ ሊካድ

እይችልም። ምንም እንኳ ከጥቂቶቹ በስተቀር፥ መዛግብቶቹ የመጀመሪያዎቹ መዛግብት ከተጻፉበት በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ባይጻፉም፥ ምስክርነታቸው እውን ነው።

ይሁንና የጊዜው ርቀት ሲታይ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደ ተገለጹት በሚገባ ተመዝግበው ለትውልድ የተላለፉ የዚያን ዘመን ታሪካዊ ክስተቶች የሉም።

ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተቶችን በተመለከተ መረጃዎችን እንደማይሰጥ ብዙ ጊዜ ተነግሯል። «የመነቃቃት ዘመን» በተባለው የፍልስፍና ጊዜ የክርስትና እምነት ከጓላ ቀር ሽቀጥ በመቆጠሩ፥ የሂሱን አግባብነት ለማረጋገጥ የተወሰደ ጊዜ አልነበረም። ክዚያም በጓላ፥ ነገሮችን እንደገና በትክክለኛ ሰፍራቸው ለማስቀመጥ ከጥቂቶቹ በስተቀር የሞከረ ሰው የለም። (ዘመናዊ) የሥነ-መለኮት አዋቂዎች ተብዬዎቹም ከ«መነቃቃቱ ዘመን» የበቀለውን ይህን እኩይ ጽንሰ-አሳብ በሚገባ ተቀብለው ማስተማራቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ዳሩ ግን በበርካታ መስኮች የሳይንስ ዕድገት በመፋጠኑ፥ ክርስቲያኖች ከማንም በላይ ለእምነታቸው ድጋፍ አግኝተዋል!

> «እንደ ደብልዩ ኤም ራምሰይ፥ ኤድ. ሜየር እና ኤ.ቲ. ኦልምስቴድ የመሳሰሉት ታሪክ ጸሐፊዎች የአዲስ ኪዳን ታሪካዊ ጽሑፎችን በተመለከተ የአንዳንድ የሥነ-መለኮት ሰዎችን ከፍተኛ ጥርጣሬ በሚገባ ተቃውመዋል» («የአዲስ ኪዳን መዛግብት» በኤፍ. ኤፍ. ብሩስ)።

በእንዳንድ ሐቆች ላይ እናተኩራለን።

«5000 የሚሆኑ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ የአዲስ ኪዳን መዛግብት በሙሉ ወይም በከፊል አሉ። ከእነዚህ መዛግብት መካከል ይበልጥ የሚሻሉትና ጠቃሚ የሆኑት ወደ 350 ዓ.ም. አካባቢ የተጻፉት ናቸው።»

«የጽሑፍ መገኛዎቹን ከሌሎች ጥንታዊ የታሪክ ሥራዎች ጋር ብናወዳድረው፥ ምናልባት አዲስ ኪዳን በመዛግብቱ እውነተኛነት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ልናደንቅ እንችላለን። ለቄሣሩ ‹ጋሊክ ጦርነት› (በ58 እና 50 ዓ.ዓ. መካከል የተዘጋጀ) ከነበሩት በርካታ መዛግብት

ውስጥ፥ ዘጠኝ ወይም አሥሩ ብቻ ጥሩዎች ናቸው። ከእነዚህ መዛግብት ውስጥ እጅግ ጥንታዊው ከቄሣር በጓላ 900 ዓመታት ያህል ቆይቷል። ክሊቪ (ከ59 ዓ.ዓ. - 17 ዓ.ዓ.) 142 የሮም ታሪክ መጻሕፍት መካከል ሠላሳ እምስቱ ብቻ ይገኛሉ። ሚዛን ከሚደፉት ሃያ ከሚሆኑት መዛግብት ማከከል የመጻሕፍት ቁርጥራጮችን የሚያካትተውና ከመጽሐፍ ሦስት እስከ ስድስት ያለው አንዱ ብቻ የአራተኛው ምእተ-ዓመት ያህል ዕድሜ አለው። ‹ታሪኮቹ› ከተሰኘው የታኪተስ አሥራ አራት መጻሕፍት ውስጥ (100 ዓ.ም. አካባቢ) አራት ተኩሉ ብቻ ይገኛሉ። ክአሥራ ስድስት የ‹ዜና› መጻሕፍቱ ውስጥ አሥሩ ሙሉ ሆነው ሁለቱ ደግሞ በክፊል ይገኛሉ። የእነዚህ እሁን የሚገኙ ሁለት ታላላቅ ታሪካዊ ሥራዎቹ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ በሁለት መዛግብት ላይ ይደገፋሉ። እንደኛው የዘጠነኛው ምእተ-ዓመት ሲሆን፥ ሌላኛው የአሥራ እንደኛው ምእተ-ዓመት መዝገብ ነው። ክእናሳ ሥራዎቹ ውስጥ የሚገኘው መዛግብት ሁሉ (ዲያሎገስ ዲ አረቶሪቡስ፥ አግሪኮላ፥ ጀርማኒስ) ከአሥረኛው ምእተ-ዓመት ጥንታዊ ጽሑፍ የተገኙ ናቸው።»

«የቱሲዳይዴስ (460-400 ዓ.ዓ. አካባቢ) ታሪክ ክስምንት መዛግብት ውስጥ የምንረዳው ሲሆን ክሁሉም ጥንታዊው የ900 ዓ.ም. ዕድሜ አለው፤ ጥቂቶቹም የቄጠማ (የፓፒረስ) መጻሕፍት ቁርጥራጮች በክርስትና እምነት መጀመሪያ አካባቢ የተጻፉ ናቸው። የሄሮዶቱስንም ታሪክ (488-428 ዓ.ዓ. አካባቢ) በተመለክተ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንመለከታለን። ይሁን እንጂ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት የሥራዎቻቸው ጥንታዊ መዛግብት ከ1300 ዓመታት በጓላ ቢዘጋጁም እንኳ የሄሮዶቱስና የቱሲዳይዴስ ተአማኒነት አጠራጣሪ ነው የሚል የመከራከሪያ አሳብ፥ ማንም የጥንታዊ ዘመን ሲቅ አይቀበለውም።»

«ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ሁኔታ በዚህ ረገድ እንዴት የተለየ ነው! በሺህ ከሚቆጠሩት ክሌሎቹ ይበልጥ ጥንታዊ በመሆናቸው ክታወቁት ክእራተኛው ምእተ-ዓመት ሁለት ምርጥ መዛግብት (ኮዴክስ ቫቲካኑስ እና ኮዴክስ ሲናቲኩስ) በተጨማሪ፥ ከ100 እስክ 200 ዓመታት አስቀድመው የተዘጋጁ ብዙ የብራና ቅጂ የሆኑ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። መኖሩ በ1931 ይፋ የወጣው የቸስተር ቢቲ የመጽሐፍ ቅዱስ ብራና አሥራ አንድ የብራና ጽሑፎችን ክፍሎች ይይዛል። ክእነዚህም

ውነጥ ሦስቱ አብዛኛውን የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ይዟል። ከእነዚህም አንዱ የሐዋርያት ሥራንና አራቱን ወንጌላት ይዞ ይገኛል። የተዘጋጀውም በሦስተኛው ምእተ-ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ነው። ሌላው ለአብያተ ክርስቲያናት የተጻፉትን የጳውሎስን ደብዳቤዎችንና የዕብራውያንን መልእክት የያዘ ሲሆን፥ የተገለበጠውም በሦስተኛው ምእተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ (ማለትም ልክ ከ200 ዓ.ም. በኋላ) ነው። ሦስተኛውና የዮሐንስ ራእይን የያዘው በዚያው ምዕተ-ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ የተዘጋጀ ነው» (ከላይ እንደተመለከተው)።

ጥንታዊ የታሪክ ዘገባዎች ከጦርነቶች፥ ከጀግኖች ታሪክና በጊዜው ከሚገኙ መሪዎች በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደማያተኩሩ ሁላችንም እናውቃለን። ከዚህም የተነሣ እንደ ገሊላና ይሁዳ ባሉ የራቁ ቦታዎች የተፈጸሙ ጉዳዮች የታሪክን ዕይታ ያገኛሉ ብሎ ለመጠበቅ አስቸጋሪ ነው። ቢደረግ እንኳ የጦርነትና የቤተ መንግሥት ጉዳዮች ዋና ገጽታዎች ሆነው መቅረብ ነበረባቸው። ይህም ሆኖ የመጽሐፍ ቅዱስን ዘገባ የሚደግፉ ማጣቀሻዎች አሉ።

የሮማው ታሪክ ጸሐፊ ፕሊኒ በንጉሠ ነገሥት ትሪጀን የትንሹ እስያ ግዛት ወደ ነበረችው ቢታንያ አውራጃ እንደ አገረ ገዥ ሆኖ (የሐዋርያት ሥራ 16፡7) በ112 ዓ.ም. ተልኮ ነበር። እዚያም ሆኖ በርካታ ደብዳቤዎችን ለንጉሠ-ነገሥቱ ጽፎ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ክርስቲያኖችን ይመለከታል። በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ፥ በመንደሮችና በገጠር አካባቢዎችም ጭምር፥ ክርስቲያኖችን እንዳገኘ ተናግሯል። የእነርሱ በፍጥነት መስፋፋት ትልቅ የማኅበራዊ ችግር ሆኖ ነበር። የባዕድ ቤተ አምልኮቶች ጎብኚ በማጣታቸው ምክንያት መዘጋት ነበረባቸው። በዓላቶቻቸውም ካለመከበራቸው የተነሣ፥ ከዚያ በኋላ ለመሥዋዕት የሚሆኑት እንስሳት ተፈላጊነት ቀርቷል። በፍጥነት በመስፋፋት ላይ የሚገኘውን የክርስትና እምነት መቃወም፥ ወይም ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ መጣሉ ሁኔታውን አልለወጠውም። ፕሊኒ ሲዘግብ አሁን በብቁ አስተዳደሩ ሁኔታው እንደሚለወጥ አስተላልፎ ነበር! በክርስትና እምነት የጸኑት መገደል ነበረባቸው። እነዚህ ሰዎች በግልጽ እንቢተኞች ስለ ሆኑ መገደል እንደሚገባቸው ተናገረ። ዳሩ ግን እነርሱ በፈጸሙአቸው ጥፋቶች ግራ እንደ ተጋባም አምኗል። ተገድደው

እምነታቸውን የተዉ ሰዎች፥ ክርስቲያኖች በስብሰባቸው ጭካኔ የተሞላባቸውን ተግባራት እንደማይፈጽሙ አሳውቀውታል። ብቸኛው ጥፋታቸው ለሹማምንቱና አማልክቱ ሐውልቶች አለመሰገዳቸውና ዳሩ ግን በተወሰኑ ቀናት (እሑድ እሑድ) ከፀሐይ መውጫ በፊት ተሰብስበው ለአምላካቸው (ኳሲ ዴኦ) ለክርስቶስ መዘመራቸው ነበር። በጥምቀታቸውም ዕለት ማንኛውንም ዓይነት ጥፋት ላለመፈጸም መሐላ ያደርጉ ነበር። ሕይወታቸው ምሳሌያዊ ነበር። በመካከላቸው ማታለል፥ ዝሙት፥ ስርቆት፥ ወይም እምነትን ማጉደል አልነበረም።

በቅዱስ ቁርባናቸው ጊዜ የተለመደ ምግብ እንጂ እንደ ታማው የሕፃናት ሥጋ አልበሉም። (ክርስቲያኖች «የክርስቶስን ሥጋ በመቀበላቸው» ብዙውን ጊዜ የሰውን ሥጋ ይበላሉ ተብለው ታምተዋል)። (ከ«ኢስ ኮሚሚር ኪይነር ሚት ታትሳሽን» በሚካኤል ግሪን በቀጥታ የተተረጎመ። የእንግሊዝኛ ርዕሱ «ራን አወይ ዎርልድ» በአማርኛ «የከበለለ ዓለም» የሚል ነው።)

በፕሊኒ ዘመን የነበረው ቆርኔሌዎስ ታክቱስ የሮም መንግሥት ታላቁ ታሪክ ፀሐፊ ነበር። እርሱም ሲተርክ (በወንድሞችና በእህቶች መካከል ላለው «ፍቅር» ትኩረት መስጠታቸው ክርስቲያኖችን በአሕዛብ ዘንድ በሐሰት እንደ ጋጠወጦችና የሰው ሥጋ በላዎች አስቆጥሯቸው ነበር) ክርስቲያኖች በወንጀሎቻቸው ምክንያት በጎብረተሰቡ ዘንድ ምን ያህል እንደ ተጠሉና በ64 ዓ.ም. ኔሮ በሮም ለተቀሰቀሰው የሰደድ እሳት መንስኤዎች ናችሁ በመባል ጥፋቱ እንደ ተላከከባቸው ይናገራል።

በጽሑፉም፡- «ክርስቲያን የሚለው ስም የተወሰደው በአገረ ገዢው በጲላጦስ ዘመነ-መንግሥት ከተገደለው ከክርስቶስ ነው። ለጊዜው ጋብ ብሎ የነበረው አጓጉል አምነት፥ እንደገና በመቅጣጠል ይህ በሽታ በተጀመረባት በይሁዳ ብቻ ሳይሆን፥ ክፉው ነገር ሁሉ እየመጣ በሚከበርባት በሮምም ሳይቀር ተስፋፍቷል።»

ከመሳፍንት ወገን የነበረው ታሲቱስ፥ ባጠቃላይ በዝቅተኛው መደብ ላሉት ሰዎች በተለይም ምሥራቃውያን ላሉበት ክርስትና ግድ እንዳልነበረው ግልጽ ነው። ስለ ሆነም የአርሱ ታሪካዊ መረጃ ከሁሉም በላይ ተቀባይነት ያለው ነው (ከላይ እንደተመለከተው)።

ታሪክ ጸሐፊው ታሉስ በ52 ዓ.ም. አካባቢ በሮም ሆኖ ጽፎ ነበር። ሥራዎቹ ግን ቢጠፉም፥ ከዚያ ውስጥ የነበረው አንድ ቁራጭ መልእክት በሁለተኛው ምእተ-ዓመት ጁሊዩስ አፍሪካኑስ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። በሰቅለት ጊዜ በምድር ላይ ስለ ወደቀው ጨለማ (ማርቆስ 15፡33) የሚናገረው ጁልየስ አፍሪካኑስ እንዲህ ይላል፡-

> «በቅጽ ሦስት የታሪክ ዘገባው ታሉስ ለእኔ እንደሚመስለኝ ጨለማው የፀሐይ ግርዶሽ ነው ማለቱ ትክክል አይደለም በማለት ያስታውቃል።»

በጁልዩስ አፍሪካኑስ የቀረበውን ተቃውሞ ማክበር አለብን። ምክንያቱም ክርስቶስ በሞተበት የፋሲካ ዕለት ሙሉ ጨረቃ ስለ ነበር፥ ሙሉ የፀሐይ ግርዶሽ ሊኖር አይችልም። ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የዘገባው ክፍል ግን በአንደኛው ምእተ-ዓመት አጋማሽ አካባቢ የክርስቶስ ሞትና የአሚሚቱም ሁኔታዎች በሮም እንኳ ሳይቀር መታወቃቸውን ማሳየቱ ነው። በደንብ ከመታወቁ የተነሣ፥ ይህ ክርስቲያን ያልሆነ የታሪክ ጸሐፊ ዋጋ እንዳለው አድርጎ በማሰብ አስተያየቱን ሰጥቷል።

የሮማ ባዕድ አምላኪዎች በሃምሳዎቹ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ያወቁት (20 ዓመታት ከሰቅለት በኋላ) ስለ መሰቀሉ ብቻ አልነበረም። ለሚከተለው መረጃ ትክክለኛ ትርጉም ከሰጠነው፥ ስለ ኢየሱስ ትንሣኤም ጭምር ያውቁ ነበር። በንጉሥ ቀላውዴዎስ ቄሣር (41-54 ዓ.ም.) ዘመነ መንግሥት የተዘጋጀ ከፍተኛ መታሰቢያነት ባለው የተቀረጸ ጽሑፍ ላይ ንጉሡ ሙታን ከመቃብር እንዲወጡ ስለ መደረጋቸው በቀረበለት ዘገባ መበሳጨቱን ገልጾ የዚህ ዓይነቱ ነገር ቢደገም የሞት ቅጣት እንደሚያስከትል ያስጠነቀቃል። ይህ የመታሰቢያ ጽሑፍ (ቅርጽ) የሚገኘው የት ነው? ካልጠፋ ስፍራ፥ በናዝሬት! (ከላይ እንደተመለከተው)።

ጆሲፈስ በሮም ላይ በተነሣው የዓመፅ ንቅናቄ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት የአይሁድ መሪዎች አንዱ ነበር። ከ70 ዓ.ም. በኋላ (ኢየሩሳሌም የወደቀችበትና የፈራረሰችበት ዓመት) በመላው የሮም ጎብረትሰብ ዘንድና በተለይም በቤተ መንግሥት አካባቢ ለይሁዲ ሃይማኖት (ጁዳይዝም) መልሶ ስፍራ ለማስገኘት ሞክሯል። ስለዚህም «አንቲኩቴትስ ዩዲይካ» (93 ዓ.ም.) እና «ዲ ቤሎ ዩዲይካ» (75-79 ዓ.ም.) በተባሉት መጻሕፍት ውስጥ ስለ አባቶቹ ሃይማኖት በበለጠ ለሮም ሕዝብ ለማላወቅ ጽፎአል ... በዚህ ውስጥ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናውቃቸውን በርካታ ገጸ-ባሕርያት እናገኛለን፡- ጲላጦስ፥ ሐናንያ፥ ቀያፋ፥ ሄሮድስ፥ ቄሬኔዎስ፥ ፊልክስ፥ ፊስጦስና ሌሎችም። እንዲሁም ደግሞ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ስለ ስብከቱ፥ ስለ ጥምቀቱና ስለ ሞቱ ጽፎአል።

> «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ የሚባል ጠቢብ ሰው ነበር። እርሱም የድንቅ ሥራዎች አድራጊ፥ አውነትን በቅንነት የተቀበሉት ሰዎች መመህር በመሆኑ ሰው ነው ብሎ መጥራቱ አግባብነት ያለው አይመስልም። ወደ ራሱም በርካታ አይሁዶችንና አሕዛብን ሳበ። እርሱም ክርስቶስ (መሢሑ) ነበር። ጲላጦስ በመካከላችን ባሉት አለቆች አሳላቢነት ለመስቀል ሞት አሳልፎ በሰጠው ጊዜ፥ በመጀመሪያ የወደዱት ሰዎች አልተለዩትም ነበር። ምክንያቱም በሦስተኛው ቀን ሕያው ሆኖ ተገልጾላቸዋልና። ይህም የሆነው ቅዱሳን ነቢያት አርሱን በተመለከተ ይህንና ሌሎች በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ አሰደናቂ ነገሮች እንደ ተነበዩት ነው። እንዲሁም ከአርሱ የተሰየመው ነገድ-ክርስቲያን ዛሬም ከምድር ገጽ አልታጣም» («አንቲ ኩ ቴትስ ዩዲይካ» 18፥111፡3) (ከላይ እንደተመለከተው)

በገና አካባቢ የፕላኔቶችና የከዋክብትን እንቅስቃሴ ለማመልከት የተዘጋጀውን የሞዴል (ፕላኔተሪየም) ብንጎበኝ፥ ምናልባት በጣም የሚያስደስት ከስተት መመልከታችንን እንመስከር ይሆናል። በአርግጥ ፕላኔተሪየም አንድ ሰው ከዋክብትን በቴሌስኮፕ (የሩቅን አቅርቦ በሚያሳይ መሳሪያ) ከሚመለከትበት ሁኔታ ጋር በማመሳሰል ግር መሰኘት አይገባም። ፕላኔተሪየም ትልቅና ጨለማ ከፍል ያስፈልገዋል። ከከፍሉ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ በጨለማው ጣሪያ ላይ ቀጫጭን ጠንካራ የብርሃን ጨረሮችን የሚረጭ በጣም የተወሳሰበ መሣሪያ ይቀመጣል። ተመልካች ወደ ላይ አንጋጦ በሚመለከትበት ስዓት፥ ልክ ከምሽቱ ብሩህ ሰማይ ሥር ያለ ይመስለዋል። ከዋክብቱም በኮምፒውተር አማካኝነት ዘፈቀደአዊ አንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዋክብትን በሙሉ፥ ፕላኔቶችና በርቀት ያሉት ኒብሌዎች (በቡድን ሆነው እጅግ የተጠጋጉ ከዋክብት) ጭምር በተወሰነ ጊዜና ቦታ በተፈጥሮ ሰማይ ላይ እንዳሉ የከዋክብት ክምችቶች

ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። ስማዩ ሲለወጥ አንዲሁ ስው ሠራሹ የፕላኔተሪየም «ስማይ»ም ሊለወጥ ይችላል። በገና በዓል ስሞን የቤተ ልሔም ከተማ የምሽት ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ጊዜ ምን ይመስል እንደ ነበር ሊታይ ይችላል። የከዋከብት መንገድ የማይዛነፍ ከመሆኑም የተነሣ አንድ ስው በታሪክ ውስጥ ማንኛውንም የምሽት ስማይ መልሶ መሥራት ይችላል። ይህም ኮሞስ=ሥርዓት ነው።

ያልሠለጠነ ተመልካች ስፕላኔተሪየም እና በማንኛውም ጥንታዊ የምሽት መካከል ምንም ልዩነት አያገኝም። የመሪነቱን ሥራ የሚያከናውነው የሥነ ከዋከብት አዋቂው (አስተሮኖመሩ) ነው፤ ደማቆች የሰማይ ብርሃናት ጁፒተርና ሳተርን የሚባሉት ፕላኔቶች አንደ ጉልህ ኮከብ እስኪመስሉ ድረስ ተቀራርበው በአንድ ላይ ተጣምረው ጉልህ ደማቅ ኮከብ እንደሚመስሉ የሚያመለክተው። ይህ መጣመር በ6 ዓ.ዓ. በአጭር ጊዜ ውስጥ ሦስት ጊዜ ተደጋግሟል። ይህ ቁም ነገር ይኖረው ይሆን? አስኪ እንየው፡-

> «ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ . . .» (ማቴዎስ 2፡1)

ይህ ታሪክ በሚገባ የታወቀ ነው። ነገር ግን ሄሮድስ በ4 ዓ.ዓ. እንደ ሞተ የታወቀ አይደለም። ከሁለት ዓመታት በታች የሆኑ የቤተ ልሔም ሕፃናት እንዲሞቱ ስምን ፈለገ? አንድ ሰው ገና በተወለደ ጨቅላና መሐይ በጀመረ ሕፃን መካከል መለየት አይችልም ይሆን? ይችላል። የምሥራቅ አገር አዋቂዎች ከመጡ ጀምሮ ረዥም የጊዜ ገደብ መቆጠር አለበት። ለዚህም ነው እንግዲህ ማረጋገጫ የፈለገው። ስለዚህ አንደ ታሪክ ጸሐፊዎቹ፥ ክርስቶስ የተወለደው በዜሮ ዓመተ ምሕረት ወይም በዲሴምበር (በታኅሣሥ) ውስጥ አንዳልሆነ ለመቀበል እንችላለን።

ስለ ሆነም ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በክርስቶስ መወለድ ጊዜ አንደ ተፈጸመ አድርገን እንደመድማለን። እጅግ ከታወቁት የመጀመሪያ የከዋከብት ተመራማሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ጆሐንስ ኬፕለር ይህን የከዋከብት ሁኔታ በ1604 በወረቀት ላይ በማስላት በ6 ዓ.ዓ. አረጋግጧል።

«በ1925 ዓ.ም. የጀርመን ሊቅ የሆነው ፒ. እስክኔብል በጥንታዊው ዓለም ዝነኛ የሙያ ተቋም በሆነው በባቢሎን በሚገኘው በሲፓር የአስትሮሎጂ (የከዋከብት ጥናት) ትምህርት ቤት ውስጥ በኒም-ባቢሎናዊ ኪዩኒፎርም (የተለየ የጽሑፍ አጣጣል) የተጻፈ «ፒስከስ» በተሰኘው የከዋከብት ክምችቶች ውስጥ ስላለው የፕላኔቶች አቅጣጫ የሚያስታውቅ ማስታወሻ አግኝቷል። በዚህም ላይ ጁፒተርና ሳተርን በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ በጥንቃቄ ተመልክተዋል። በቀን መቁጠሪያችን ላይ ሲስላ ዓመቱ 7ዓ.ዓ. ነበር።» «በአይሁድ ባህል መሠረት፥ ፒስክስ የእስራኤል ምልክት፥ የመሢሑ (የክርስቶስ) ምልክት ነበር . . . ጁፒተር ሁልጊዜም በሁሉም ሕዝቦች ዕድለኛና ክብር ኮክብ ሆኖ ይታሰባል። በጥንታዊ የአይሁድ ባሕል መሥረት ሳተርን የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚጠብቅ ተገምቷል።» ታስቱስ ክአይሁድ አምላክ ጋር ያስተካክለዋል...»

«ክናቡከደነፆር ዘመን ጀምሮ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች በባቢሎን ኖረዋል። ምናልባትም ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹ በሲፓር የአስትሮሎጂ ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረው ይሆናል። በመሢሁ ‹የምዕራብ አገር› የከዋከብት ክምችት ውስጥ ይህ አስደናቂ የጁፒተር ክእስራኤል ጠባቂው ከሳተርን ጋር መጣመር የአይሁድ የሥነ-ከዋከብት ሊቃውንትን ስሜት በጥልቀት ሳያንቀሳቅስ አልቀረም። ምክንያቱም ይህ በኮከብ ቆጣሪዎች አስተሳሰብ መሠረት ታላቅ ንጉሥ ክምዕራብ አገር (ከባቢሎን በስተ ምሥራቅ ክአባቶቻቸው ምድር አንደሚመጣ ተመልክቶ ነበር። ለዚህ ነበር ጠቢባኑ ክምሥራቅ ተነሥተው በዓይናቸው እርሱን ለማየት የተጓዙት» («መጽሐፍ ቅዱስ አንደ ታሪክ» በደብልዩ ኬለር)

ኬፕለር አንኳ የጸሐፈውን የሬቢ (መምህር) አባርባነልን ማጣቀሻ ካነበበ በኋላ፥ የተባለውን የከዋከብት ክምችት ዝርዝር ነገር ገሃድ ለማውጣት ተንቀሳቅስ ነበር። ማጣቀሻው የሚከተለው ነበር፡-

> «የአይሁድ የሥነ-ከዋከብት ሊቃውንት ይህን ያልተለመደ ተጽዕኖ በዚሁ የከዋከብት ክምችት ላይ እንዳመካኙ ይነገራል። መሢሑ

ጁፒተርና ሳተርን በ‹ፒስክስ› ከዋክብት ክምችት ውስጥ በሚጣጣሩበት ጊዜ ይመጣል» (ከላይ እንደተመለከተው)።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ (2፡1-12) የሚከተለውን እናነባለን፡-

«ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሥ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ስብአ ሰገል፡- የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም (እዲስ የተወለደ ሕፃን ወደሚፈልጉበት ወደ ንግሡ ከተማ) መጡ። ንጉሥ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፥ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር፤ የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። እነርሱም፡-

> አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና።

ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት።

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን (የትኞቹን የዕድሜ ክልሎች እንደሚገድል ለማወቅ?) ከእነርሱ በጥንቃቄ ተረድተው፥ ወደ ቤተ ልሔምም እነርሱን ሰድዶ፡- ሂዱ፥ ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ እላቸው። እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ እነሆም፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው። ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፥ ወድቀውም ሰገዱለት፥ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት። ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ።»

የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ በሲፓር ከነበሩት ተመራማሪዎች ጋር ግንኙነት እንዳለው ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹ ኮኮብ ቆጣሪዎች ከዚህ የተጠቀሰውን የኮከብ ክምችት በማየት የአይሁድን

የእተረጓጎም አሳብ እንደ ተረዱ እናውቅም። ዳሩ ግን በግኝቶቹ ውስጥ እሰደናቂ የሆነ ቁም ነገር አለ።

ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት እደነቁ፡-

> «ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?» (ማቴዎስ 8፡27)።

ይህ የሆነው በገሊላ ባሕር ላይ ማዕበሉን ፀጥ ባሰኘ ጊዜ ነበር። እኛ ምናልባት እንዲህ ለማለት እንችል ይሆናል፡-

ከዋክብት እንኳ ዘገባ የሚያቀርቡለት ይህ ማን ነው?

ይህ በምንም ዓይነት ዘመናዊ የኮኮብ ቆጠራ ለማካሄድ ማበረታቻ አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ልምምድ ያወግዘዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ቸር ከመሆኑ የተነሣ እዚህ ላይ እንኳ የነገሥታትን ንጉሥ የፈለጉ ሰዎች እንዲያገኙት ፈቅዶላቸዋል።

እያንዳንዱ የወንጌል ታሪክ ጸሐፊ የሰቅለቱን ሁኔታ በትልቅ ዝርዝር ጽፎታል።

የሙስሊሞች ክርክር ይህ ሁሉ ሊሆን ቢችልም (ሱረቱ 4፡15)፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ስለ ወሰደው፥ በመስቀል ላይ የተቸነከረው ሰው ኢየሱስ ይመስላል እንጂ እርሱ እይደለም ነው። ይህ ክርክር በሚከተሉት ነጥቦች ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም፡-

1. ክትንሣኤው በኋላ፥ ክርስቶስ ከ500 ለሚበዙ ክርስቲያኖች ተገልጾላቸዋል፤ እነርሱም አውነቱን የመሰክሩ ሲሆኑ፥ የምስማሩን ችንካርና በጦር የተወጋ ጎኑን እላይታቸዋል።

2. የሞተው የብሉይ ኪዳን «መጽሐፍ እንደሚል» ክብዙ ዘመን አስቀድሞ በትንቢት በተነገረለት መሠረት ነው።

3. ክርስቶስ ስለ ሞቱ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር።

4. የዓይን ምስክሮች (ሐዋርያት) መስክረውለታል።

5. የታሪክ ሰዎችም ዘግበውታል።

እንደ ሌሎች የእስልምና ጉዳዮች ሁሉ በዚህ ክስተት ላይ የሚሰነዘረው ክርክር በሙሉ የሚያርፈው በአንድ ሰው ምስክርነት ላይ ነው፤ ይህም ከሌላው መረጃ ሁሉ ጋር ተጻራሪ ነው። ብዙ ጊዜ የሚነሣው ሌላው ጥያቄ ማቴዎስ 12:38-40ን ይመለከታል:-

«በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና:- መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው:- ክፉና ኤመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።»

ሃያሲያን ሲጠይቁ:- «ዮናስ በዓሣ አንባሪው ሆድ ውስጥ የቆየው እንዴት ነበር? ሞቶ ወይስ በሕይወት ነበር? ይላሉ። ማረጋገጫው «ዮናስ በዓሣ አንባሪው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበር ...» ስለሚል፥ ይህ በግልጽ ከዋናው ነጥብ ማፈንገጥ ነው። ምሳሌው ወይም መግለጫው ነጥቡን ለማብራራት እየሞከረ ነው። እዚህ ላይ የጊዜን ርዝማኔ ይመለከታል።

ክርስቶስ አስቀድሞ ብዙ ምልክቶችን እንደ ሰጠና ከዚህም ጥያቄ በኋላ ይህንኑ ምልክት መስጠት እንደ ቀጠለ እንመለከታለን። ምልክቱ ለማያምን ሰው በመጻሕፍት ዘገባ መሠረት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሆኖ ይታያል። እንግዲህ ሃያሲያኑ ሊናገሩ፥ ኢየሱስ ዓርብ ዕለት ጠዋት ተሰቀለ፤ ወደ 9 ሰዓት አካባቢ ሞተ፤ ከዚያም የበዓል ቀን ከመጀመሩ በፊት፥ ማለትም ከፀሐይ መጥለቅ ቀደም ብሎ ተቀበረ። ያም የዓርብንና የቅዳሜን ቀናት (2) ያካትታል። ምክንያቱም እሑድ ዕለት ከፀሐይ መውጣት አስቀድሞ ኢየሱስ ተነሥቷልና! በመቃብር ውስጥ የነበረው ከዓርብ ዕለት አስከ ቅዳሜና ከቅዳሜ ዕለት እስከ እሑድ ባሉት ሌሊቶች ነው። ስለዚህም የሦስት ቀናትን ቁጥር ለማግኘት አንችልም ይላሉ። ይህ የአንባቢውን የባሕል ግንዛቤ የሚጠይቅ በመሆኑ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው።

ከሁሉ አስቀድመን የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ፥ «ቀንና ሌሊት» የሚሉ ቃላት ሁልጊዜም ከተመሳሳይ ቁጥሮች ጋር እንደሚስለፉ መረዳት አለብን («ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት» ወይም «አርባ ቀንና አርባ ሌሊት»

ወዘተ። እንጂ በፍጹም «ሦስት ሌሊትና ሁለት ቀን» ወይም «አምስት ቀንና አራት ሌሊት» አይሆንም።) በዚህም ዓይነት በዕብራይስጡ የቃላት አገባብ «ዩ-ለዬላ» ከእኛው የ«አንድ ቀን ማለትም 24 ሰዓታት ወይም በዚህ ክልል ውስጥ ከሚገኝ ክፍለ - ጊዜ ጋር ይዛመዳል። (1:17፤ 1ኛ ሳሙኤል 3:12፤ ኢዮብ 2:13፤ ዘፍጥረት 7:14፤ ዘጸአት 24:18፤ 34:28፤ ዘዳግም 9:9-10፥ 18፥25፤ 10:10፤ 28:66፤ 1ኛ ነገሥት 19:8 እና ማቴዎስ 4:2 ተመልከት።)

ቀን በፀሐይ መጥለቅ ይጀምራል፤ ይህም 12 ሰዓት አካባቢ ማለት ነው። ኢየሱስ ዓርብ ዕለት በ9 ሰዓት ሞቷል። ይህ አንድ ቀን ተብሎ ተቆጥሯል። ቅዳሜውን ሙሉ ደግሞ ሞቶ «በምድር ልብ ውስጥ» ሰለ ነበር ሁለተኛውን ቀን አስቆጠረ ማለት ነው። እንዲሁም ምናልባት በሦስተኛው ቀን አጋማሽ ላይ ማለትም እሑድ ዕለት በፀሐይ መውጫ ጊዜ ተነሥቷል። ይህም ሦስተኛውን ቀን ያሟላል። በሦስተኛው ቀን መነሣቱ በብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ተደግፏል (ሉቃስ 24:21፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:4 ወዘተ)።

ለዚህ ዳጎስ ያለ ደጋፊ አሳብ ለማግኘት ከመጽሐፈ «አስቴር» ውስጥ አስቴር ለመርዶክዮስ ከምትናገርበት እናነባለን:-

«... ለእኔም ጹሙ፤ ሦስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትበሉም፥ አትጠጡም፤ እኔና ደንገጥሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን በሦስተኛውም ቀን አስቴርም:- ለንጉሡ መልካም ሆኖ ቢታይ ንጉሡ ወዳዘጋጀሁለት ግብዣ (እራት)... ዛሬ ይምጣ አለች» (አስቴር 4:16-5:5)። ለሦስት ቀናት ቢጾሙም፥ በሦስተኛው ቀን እራት በልተዋል። እንደዚሁም የጦቢያ መጽሐፍ 3:12-13 ከብሉይ ኪዳን ዘመን በመተረክ (200 ዓ.ዓ.):- በእንደዚህ ዓይነት ቃላት ወደ ላይኛው ቤት ከፍል አመራች። ለሦስት ሌሊትና ቀን አልበላችም፤ አልጠጣችም። እግዚአብሔርም ከጎፍረት እንዲጠብቃት (በግድያ ወንጀል ሰለ ተከሰሰች) እየጠየቀች መጸለይዋን አላቋረጠችም። ከዚያም በኋላ፥ በሦስተኛው ቀን ጸሎቷን በመፈጸም እግዚአብሔርን አመሰገነች» ይህ «ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ተነሣ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15:4 ወዘተ) ከሚለው የአዲስ ኪዳን ዘገባ ጋር ይስማማል።

የኢየሱስን ዓለም- አቀፋዊነት በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

ሙስሊሞች የኢየሱስን ዓለም-አቀፋዊ አባባል ለመቃወም የሚችሉትን ያህል ሙከራ አድርገዋል።

> «ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ» (ዮሐንስ 14፡6)።

ይህንንም ለመፈጸም ከሁሉ የተሻለው መንገድ እንደ ሕዝበ-እስራኤል ብሔራዊ ነቢይ በመቁጠር ዝቅ ማድረግ ሆኖ ቆይቷል። ስለ ሆነም መሐመድ እንደ ተላከላቸው ለሚነገረው ለአሕዛብ ኢየሱስ አስፈላጊነቱን ያጣል ማለት ነው።

እስልምና ኢየሱስ ክልላዊ ነቢይ መሆኑን ደጋግሞ ተናግሯል ብሎ ይከራከራል፦

> «ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም» (ማቴዎስ 15፡24)።

> «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» (ማቴዎስ 1፡21) (ሕዝቡ የሚለው አይሁድን መሆኑ ነው።)

> አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ላካቸው፦ «በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥ ወደ ላምራውያንም ከተማ አትግቡ ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ» (ማቴዎስ 10፡5-6)።

እዚህ ላይ የወንጌል ዓለም-አቀፋዊነት እጠያያቂ ተደርጓል። ለመሆኑ ይህ አባባል ትክክል ነውን? ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በአይሁዶች ብቻ ተወሰነ? የዚህ መልስ መሠረት የሚገኘው በዘፍጥረት 12፡3 ላይ ነው፦

> «የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።»

የሚባረኩትም በአብርሃም፥ በትክክል ለማስቀመጥም በዘሩ ነው። ይህ በይስሐቅ የቃል ኪዳን መስመር ውስጥ ይገኛል፤ በመሆኑም ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ በውኃ ጉድጓድ ከሳምራዊቱ ሴት ጋር ሲወያዩ ሳለ (ዮሐንስ 4)፥ «መዳን ከአይሁድ» እንደ ሆነ ተናግሯል። «መዳን ለአይሁድ» እንዳላለ ልብ ማለት ያሻል።

አይሁዶች ብቻ የኢየሱስን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ። በእስራኤል ታሪክና በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር በተገኙ ጽሑፎች ብቻ ስለ ተያዘ፥ ማንም ሮማዊ፥ ሕንዳዊ፥ ወይም ጃፓናዊ ይህን ነገር ሊረዳው አይችልም ነበር። እይሁዶች ኢየሱስን እየጠበቁ ቆይተው ነበር። እርሱም አይሁዳዊ መሆን ነበረበት (ዘዳግም 18፡15)። እንዲያውም ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት ቤት መሆኑን ለማረጋገጥ የዘር ሐረጉም መገለጽ ነበረበት (ዘፍጥረት 49፡10፤ 2ኛ ሳሙኤል 17፡13)። በመሆኑም ምንም እንኳ በመጣላቸው ጊዜ ባያውቁትም፥ አይሁዶች ሁሉ መሢሕን በናፍቆት ሊጠባበቁ ኖረዋል።

አይሁዶች ብቻ ከተረዱትና ካወቁት በኋላ እርሱን በገሃድ ለማወጅ ይችሉ ነበር። ስለ ሆነም ሁሉም ሐዋርያትና ከሞላ ጐደል ሁሉም የመጀመሪያ ክርስቲያኖች አይሁዶች ነበሩ። እነርሱም ቢሆኑ በመጀመሪያ ይህን የመረዳት ትልቅ ችግር ነበረባቸው። እግዚአብሔር ለጴጥሮስ በኢዮጴ በቤቱ ሰገነት ላይ እስከ ተናገረበት ጊዜ ድረስ (የሐዋ.ያት ሥራ 10)፥ ወንጌሉን ለአይሁዶች ብቻ ይናገሩ ነበር። ለጴጥሮስ ብቻም ሳይሆን፥ ለሳውልም በደማስቆ መንገድ ላይ (የሐዋርያት ሥራ 9)፥ እና ለፊልጶስ ብቻውን ላለ በጋዛ ስርጥ ባለው በረሃማ መንገድ ላይ (የሐዋርያት ሥራ 8) ተናግሯል። ለአሕዛብ ሁሉ የምሥራቹን ቃል ለማድረስ፥ ወደ ዓለም እንዲሄዱ ክርስቶስ ታላቁን ተልዕኮ ከሰጣቸው በኋላ እንኳ (ከማቴዎስ 28፡19-20)፥ ሐዋርያት ለአይሁዶች ብቻ ሰብከዋል። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ርቀው እንዲሄዱ መርቷቸዋል (የሐዋርያት 1፡8፤ ሉቃስ 24፡27 ተመልከት)።

ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፦

> «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» (ዮሐንስ 16፡12-13) ብሏል።

ይህ ልምምድ በበዓለ ኀምሳ (ጰንጠ-ቆስጤ) ዕለት ተጀመረ።

በኢዮጴ እና በቆርኔሌዎስ ቤት ከተደረገው እንግዳ ልምምድ በኋላ ነበር ሐዋርያት ታላቁን ተልዕኮ በተለየ ብርሃን ማየት የጀመሩት። ይኸውም ብሔራዊ ሳይሆን ዓለም -አቀፋዊ ወንጌል እንደ ሆነ መገንዘባቸው ነበር።

«በቂሣርያም ኢጣሊቁ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነው ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ። እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልከና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ የሚጸልይ ነበረ። ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል፡- ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ በግልጥ አየው። እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ፡- ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለው። መልአኩም አለው፡- ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ። እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል። የተናገረውም መልአክ በሄደ ጊዜ፥ ከሎሌዎቹ ሁለቱን፥ ከማይለዩትም ጭፍሮቹ እግዚአብሔርን የሚያመልክ እንዱን ወታደር ጠርቶ፥ ነገሩን ሁሉ ተረከላቸው ወደ ኢዮጴም ላካቸው።

«እነርሱም በነገው ሲሄዱ ወደ ከተማም ሲቀርቡ፥ ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ። ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም ተመሰጠ መጣበት፤ ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ፤ በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት። ጴጥሮስ ሆይ፥ ተነሥተህ እርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ጴጥሮስ ግን፡- ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ አንዳች ርኩስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ። ደግሞም ሁለተኛ፡- እግዚአብሔር ያነጻውን እንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፥ ወዲያውም ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ።

«ጴጥሮስም ሰላየው ራእይ፥ ምን ይሆን? ብሎ በልቡ ሲያመነታ፥ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምዖን ቤት ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው፡- ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ እንግድነት ተቀምጦአልን? ብለው ይጠይቁ ነበር። ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ፡- እነሆ፥ ሦስት ሰዎች

ይፈልጉሃል፤ ተነሥተህ ውረድ፥ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው።»

ቆርኔሌዎስ የሆነውን ሁሉ ለጴጥሮስ ከገለጸለት በኋላ፥ ጴጥሮስ መልሶ እንዲህ አለ፡-

«እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ። የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን አየስበከ ይህን ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ። ዮሐንስ ከስበከው ጥምቀት በኋላ ከገሊላ ጀምሮ በይሁዳ ሁሉ የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ። እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወስ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን። ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ እንመስክር ዘንድ አዘዘን። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» (የሐዋርያት ሥራ 10፡1-20፥ 34፥43)።

ምናልባትም የሚከተለው ገለጻ መረዳታችንን ይጨምርልን ይሆናል። ያለ መሰኖ አንድ በረሃማ ስፍራ ውኃ ሊያገኝ አይችልም፤ እናም ግድብ ይገደባል። ይሁንና ያለ ቧንቧዎች ወይም ቦዮች ውኃው ከማጠራቀሚያው ወደ መስኮች ሊፈስ አይችልም። እንደዚሁም ሕይወትን ለሚሰጠው ውኃ ቧንቧዎቹ እይሁዶች ነበሩ። ክርስቶስ ራሱን የሕይወት ውኃ ብሎ ጠርቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያትም ዓለሙን ለሚወከሉ መስኮች ውኃን የሚያደርሱ የመጨረሻዎቹ የውኃ መተላለፊያዎች ናቸው።

ኢየሱስ በሕይወት ዘመኑ ለመስክች ውኃ የሚያደርሱ ቧንቧዎች ማዘጋጀቱ አግባብ ያለው ነገር ነው። ይህም ሕይወቱን ከሞቱ አጅግ በተለየ ሁኔታ ዓለም- አቀፋዊ ያደርገዋል። በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ክርስቶስ በሮማዊ የመቶ አለቃ ውስጥ ትልቅ እምነት ስለ ተመለከተ እንዲህ አለ፡-

> «አውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም። እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ የመንግሥት ልጆች (አይሁዶች) ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ» (ማቴዎስ 8፡10-12)።

ሥራው ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ፥ ታላቁ ተልዕኮ በመባል የሚታወቀውን የመጨረሻ ትእዛዝ ሰጠ፡-

> «ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት እድርጓቸው እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴዎስ 28፡19-20)።

ለሙስሊሙ ሱራህ 21፡91ን ማንበብ የበለጠ ማረጋገጫ ይሆንለታል፡- «እርሷንም ልጅዋንም (ኢየሱስ) (እንደዚሁ)፥ ለዓለማት ታምር ያደረግናትን (መርየምን አስታውስ)።»

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መሐመድ እንደ ተተነበዩ ሆነው የቀረቡ ትንቢቶች

ቁርአን እንደሚከተለው ይናገራል፡-

1. «የመርየም ልጅ፥ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፍቴ ያለውን የማረጋገጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ፥ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን፥ ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» (ሱረቱ 61፡6)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንደዚህ ዓይነት ዘገባ እናገኛለን?

አሕመድ መሐመድ ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ስም ሊሆን፥ የሁለቱም ትርጉም «የተመሰገነ» ማለት ነው። ይህ በግሪክ ቋንቋ «ጰራክሌቶስ» እንደ ሆነ ተነግሮናል። በዮሐንስ ወንጌል 14፡16 ላይ የሚከተለውን እናገኛለን፡-

> «እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ ጰራክሌቶስ (አጽናኝ ወይም አማካሪ) ይሰጣችኋል።»

በቁርአን ምንባብ በመደገፍ፥ ሙስሊሞች ይህ ጥቅስ ከዚህ በላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ በግልጽ የተተነበየውን የመሐመድን መምጣት ለማድበስበስ በፈለጉ ክርስቲያኖች የተዘጋጀ ማጭበርበሪያ ነው ብለው ይናገራሉ። ዳሩ ግን ከመሐመድ መምጣት በብዙ መቶ ዓመታት ወደ ኋላ የሚርቁት የዚህ የዮሐንስ ወንጌል መዛግብት ሁሉ «ጰራክሌቶስ» የሚለውን ቃል እንጂ «ጴርክሉቶስን» ይዘው አንደማይገኙ መግለጽ አለብን። ቀጣዩ ቁጥር (ጴርክሌቶስ)፡-

> «እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ (ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት) ዘንድ ስለሚኖር፥ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ»

በማለት ይገልጽልናል።

ስለ ሆነም መሐመድን በመንፈስ ቅዱስ ቦታ የሚያስቀምጥ ማንኛውም ትርጓሜ ከእውነት ጋር ጎብረት አንደ ሌለው ግልጽ ሊሆን ይገባል።

2. «የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ሳይሞት የእስራኤልን ልጆች የባረከባት በረከት ይህች ናት። እንዲህም አለ፦

«እግዚአብሔር ከሲና መጣ፥በሴይርም ተገለጠ፤ ከፋራን ተራራ አበራላቸው፥ከአእላፋትም ቅዱሳት መጣ፤ በስተ ቀኙም የእሳት ሕግ ነበረላቸው። ሕዝቡንም ወደዳቸው፤ ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ናቸው፤ በእግሮችህም አጠገብ ተቀመጡ፤ ቃሎችህን ይቀበላሉ። ሙሴ ለያዕቆብ ጉባኤ ርስት የሆነውን ሕግ አዘዘን። የሕዝቡ አለቆች ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ጋር በተከማቹ ጊዜ፥ ንጉሥ በይሹሩን ነበረ» (ዘዳግም 33፡1-5)።

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ የዚህን ምንባብ ሁለተኛ ጥቅስ በመውሰድ፥ እግዚአብሔር ከሲና ሲመጣ በሙሴ በኩል ተገለጠ፤ ከሴይር ሲገለጥ፥ በኢየሱስ በኩል መጣ፤ ከፋራንም ተራራ ሲያበራና ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ሲመጣ፥ በመሐመድ በኩል ተገለጠ ብለው ይናገራሉ። ይህ ጥናት ለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍል ትክክለኛ ትርጉም ስፍራ አይሰጥም። ዳሩ ግን ከዓውደ-ንባቡ እንደምንረዳው፥ ይህ ከፍል የሚያመለክተው ወደ ያህዌ እንጂ፥ ወደ ሙሴ ወይም ወደ ሌላ ማንኛውም ነቢይ ያለመሆኑ ግልጽ ነው! የዚህ ጥቅስ አስላማዊ አተረጓጎም አጓጉል የሆነ ነው። በተጨማሪም የፋራን ተራራ ለመካ ቅርብ በሆነው በአረብ ባሕረ ሰላጤ አካባቢ ይገኛል በሚል የተሳሳተ አሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። ማንኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ መልከአ ምድር ተማሪ ሁለቱ ተራሮች (ሴይር እና ሲና) እና የፋራን ደጋማ ስፍራዎች ከመካ በ1000 ኪሎ ሜትሮች ርቀው ባሕረ ሰላጤ ውስጥ እንደሚገኙ ያውቃል።

3. ሌላው ሙስሊሞች ለመሐመድ እንደ ተነገረ አድርገው የሚያቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍል በዮሐንስ ወንጌል 1፡19-23 ላይ ይገኛል፦

«አይሁድም፥ አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። መስከረም አልካደምም እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ። አንኪያስ፦ ማን ነህ? . . . አርሱም፦ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፦ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።»

ምንም እንኳ ሙስሊሞች በማያጠራጥር ሁኔታ የክርስቶስን አምላካዊነት የሚያውጀውን የዚህ ምዕራፍ ማንኛውንም ሌላ ከፍል ላለመቀበል ቢመስኑም፥ «ያ ነቢይ» ወይም በመጀመሪያው መጽሐፍ ላይ እንደሚለው «ነቢዩ» የተጠበቀው መሐመድ እንደ ነበረ ያስባሉ። እስራኤል በዚያን ጊዜ ነቢይ እየጠበቀች ነበር። በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነቢዩን ይጠብቁ ነበር።አርሱም ከዘዳግም 18፡15 ጀምሮ የተተነበየለት ነው፦

«አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፦ እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልሰማ፥ ይህችን ታላቅ አሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደ ለመንኸው ሁሉ፥ ለአምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ አርሱንም ታደምጣለህ። እግዚአብሔርም አለኝ፦ የተናገሩት መልካም ነው፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ» (ዘዳግም 18፡15-19)።

ይህ ነቢይ ኢየሱስ እንደ ሆነ በሐዋርያት ሥራ 3፡17-23 በግልጽ ተቀምጧል፦

«አሁንም ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት አውቄአለሁ፤ እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው። እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፥ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም። እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና። ሙሴም ለአባቶች፦ ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ አርሱን ስሙት። ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝቡ ተለይታ ትጥፋለች አለ።»

በአይሁድ አስተሳሰብ ግን «ነቢዩ» መሢሕ አልነበረም፡-

«ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ፡- ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤ ሌሎች፡- ይህ ክርስቶስ ነው አሉ (ዮሐንስ 7፡40)።

«ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ። እነርሱም፡- አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት። እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው አግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ» (ማቴዎስ 16፡13-16)።

ከዚህም ሌላ፥ ፈሪሳውያን ከተመረጠው ሕዝብ ወገን ሆነው ሳለ የሚመጣው ነቢይ ማንም አሕዛብ እርሱ እንደሚሆን አድርገው አይጠብቁም። (ዘዳግም 18፡15 ተመልከት፡- «አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል... ነቢይ ያስነሣልሃል» ይህም ከአይሁዶች መካከል ማለት ነው።)

ሰለዚህ ነቢዩ አለ ጥርጥር መሢሑ ነው።

4. ስለ መሐመድ እንደ ተነገሩ ሆነው ከቀረቡት ትንቢቶች ሁሉ ትልቅ ተቀባይነት ያለው በዘዳግም 18፡15-22 ላይ ይገኛል፡-

«አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ሰብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፡- እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልስማ፥ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደ ለመንኸው ሁሉ፥ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ። እግዚአብሔርም አለኝ፡- የተናገሩት መልካም ነው፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ። ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ፥ እርሱ ይገደል። በልብህም፡- እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፥ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን

ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።»

መሐመድ ራሱን እዚህ ላይ የተጠቀሰውን ነቢይ አድርጎ በደንብ ስለሚናገር፥ የዚህ ምንባብ የመጨረሻ ክፍል ጥንቃቄ የተሞላበት እይታ ያሰፈልገዋል (ሱሪቱ 2፡129፥ 159፤ 3፡81፥ 164፤ 7፤ 157)።

በእስልምና የዘዳግም ከፍለ-ምንባብ እንደሚከተለው ነው፡-

1. ሙሴና መሐመድ ሁለቱም ከጠላቶቻቸው እጅ መሸሽ ነበረባቸው። አያንዳንዳቸው ከእማቶቻቸው ዘንድ ትብብር አገኙ። ዮቶር የልጁ ባል የሆነው ሙሴን በችግሩ ጊዜ ማጽናናት ነበረበት (ዘጸአት 18፡14-26)። ነገር ግን በዋሻ የነበረውን ተባባሪውን ያጽናናው መሐመድ ነበር።

2. ሙሴ በኋላ በአማቱ በዮቶር ያትሮብ ተብሎ በተለየመው በምድያን ተሸሸገ፤ መሐመድ ደግሞ ከሸሸቱ በኋላ መዲና ተብሎ በድጋሚ ወደ ተሰየመው ወደዚህ ያትሮብ ሄደ። የሙሴ ሽሽት በአማቱ ምሪት ጥቅም ሲያስገኝለት የመሐመድ ሽሽት ታላላቅ ለሆኑ ተከታታይ ድሎች መንገድ ጠርጎለታል።

3. ሙሴ ለሕዝቡ የሚሆን እጠቃላይ መመሪያ ተሰጥቶት ነበር፤ ዳሩ ግን መሐመድ በራሱ ፍጹም የሆነ፥ ለሰዎች ሁሉና ለሁል ጊዜ የሚሠራ ፍጹም መመሪያ ተቀብሏል።

4. ጌታ እግዚአብሔር በግብፅ ለሙሴና ለአሮን እንዲህ በማለት ተናገረ፡- «ይህ ወር የወራቶች ሁሉ መጀመሪያ ይሆንላችኋል፤ የዓመቱም የመጀመሪያ ወር ይሆናል።»

   በተመሳሳይ ሁኔታ ለሙስሊሞችም የመሐመድ የሽሽት ወርና ዓመት የሙስሊሙ የወርና የዓመት መጀመሪያ ሆኗል።

5. ሙሴ ሕዝቡን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር አላቅቆአቸዋል፤ መሐመድ ጠላቶቹን በጨበጣ ውጊያ በማሸነፍ ልጆቻቸውን ወደ እምነቱ እፍልሷል።

6. የሙሴ ጥረቶች ብዙ መከራዎችንና ደም ማፍሰስን ጠይቀዋል። ዳሩ ግን የመሐመድ ጥረቶች የሃይማኖት ነጻነት ለማግኘት ሲባል የተደረጉ ናቸው።

7. ከእርሱ በኋላ ለመጡት ትውልዶች የተሰጠችውን ከነዓንን ለመውረስ ስለ ፈለገ፥ የሙሴ ሕግጋት ጠብ አጫሪዎች ነበሩ፥ መሐመድም ጦርነቶችን መከላከል ቢኖርበትም በመጨረሻ ዐረቢያ ተገዛችለት። ከነዓንም እንኳ በተተኪዎቹ አገዛዝ ሥር ወድቃለች።

8. ሙሴ በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ ተቀምጧል፤ መሐመድም እንዲሁ የሕዝቡ ዋና ፈራጅ ሲሆን አይሁዶች እንኳ ሳይቀሩ ይህን ተቀብለውታል።

9. ሙሴ በምድያን ለአሥር ዓመታት እንደ ሰበከ ሁሉ፥ መሐመድም በመዲና እንደዚሁ አድርጓል።

10. ሙሴ ሕግ ሰጪ፥ ጂኔራልና የሕዝቡ መሪ ነበር። መሐመድም ደግሞ ድለ አድራጊ ጂኔራል፥ ለሰዎች ፍጹም የሆነ መሪና ሲለወጥ የማይችል ዓለም-አቀፋዊ መመሪያ ሰጪ ነበር።

11. ወደ እርሱ እጅግ ከተጠጉት ግብፃውያን እጅ ኃይለኛ የውኃ ማዕበል ሙሴን አድኖታል፤ ዳሩ ግን መሐመድ በቀውጢ ሁኔታ ውስጥ በነበረ ጊዜ የጋረደው የሸረሪት ድር ብቻ ነበር።

12. የሙሴ ተባባሪዎች የጠላትን ሠራዊት በተመለከቱ ጊዜ፥ «በእርግጥ ደርሰውብናል» አሉ፤ ሙሴም «በምንም ዓይነት፥ ጌታዬ ከእኔ ጋር ነው፤ እርሱ መውጫውን ያሳየኛል» ብሎ መመለስ ነበረበት። በሂራ ዋሻ ውስጥ በበለጠ አሰቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበረ ጊዜ የመሐመድ ምላሽ፥ «አትጨነቁ፤ በእርግጥ አላህ ከእኛ ጋር ነው» የሚል ነበር። (በአል- ሐጅ ሱልጣን ሐፊዝ አብዱል ተጽፎ፥ በሙላና ሰይድ ቢያ-ኡድ-ዲን አሕመድ ግላኒ ተሻሽሎ ከቀረበውና «ብርሃኑ» ከተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 214-126 የተወሰደ።»

እኛም ምላሻችንን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡-

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ምድያን የሚገኘው በሲና ተራራ አጠገብ እንጂ፥ ያትሮብ ወይም ዛሬ እንደሚታወቀው መዲና ባለበት ቦታ አይደለም።

7. ምናልባትም ከአንዳንድ አጋጣሚዎች በስተቀር፥ የትኞቹ የመሐመድ ጦርነቶች የመከላከል እንደ ነበሩ ለመረዳት ያስቸግራል። ሙስሊሞች በእስፔይን፥ እንዲያውም በፈረንሳይ፥ በሕንድ፥ በስሜን አፍሪካ፥ በሶሪያ፥ በቱርክና በባልካንዝ ምን ይከላከሉ እንደ ነበር አናውቅም። በእርግጥ ጸሐፊው «አገዛዝ» የሚለውን ቃል ሲጠቀም፥ «ከቀንበር ሥር ማኖር» ማለት ይሆን?

8. አይሁዶች መሐመድን እንደ ፈራጅ ከመቀበል በቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም።

9. ምድያም ከተማ ሰላልነበረ፥ ሙሴ በዚያ አልሰበከም። በዚያ የቆየው በጎችን እየጠበቀ ነው። በተጨማሪም ይህን ያደረገው ለ40 ዓመታት እንጂ ለ10 ዓመታት አልነበረም።

10. «ዓለም -አቀፋዊ መመሪያ» የተባለው ቁርዓን እንደ ሆነ እናሰባለን። በውስጡ ምንም ዓይነት ለውጥ አልተደረገም ማለቱ ትክክል አይደለም። ወደ ሱረቱ 16፡101 እና 2፡106፥ በተጨማሪም ወደ «ማንሱክ» እና «ናሲክ» ሥነ-መለኮት ሙሉ በሙሉ እናጣቅሳለን። (እባክህ «ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን ይጠይቃሉ» የሚለውን መጽሐፍ አንብብ።)

11. ሙሴን ከግብፆች ያዳነው የውኃ ማዕበል አልነበረም። ውኃው እንደ ግድግዳ በጎንና በጎን ቆሞ ሳለ፥ አይሁዶች በባሕሩ ውስጥ በደረቅ መንገድ ተሻገሩ። እስራኤላውያን ከተሻገሩ በኋላ፥ ውኃ እንደገና በመመለስ የሚያሳድዱአቸውን ግብፃዊያን አጠፉ (ዘጸአት 14፡ሱረቱ 2፡50)።

12. በታሪክ ሁሉ በአሰጨናቂ ሁኔታዎች ውስጥ ብዙ አማኞች ተመሳሳይ ድርጊቶች ፈጽመዋል።

ተመሳሳይነት ሳይሆን ይልቁንም ተቃርኖ በሚያሰከትሉት ቁጥሮች 1፥ 2፥ 5፥ 6፥ ና 11 ላይ ተቃውሞ ለመስንዘር እንፈልጋለን።

ቁጥር 3 በሙስሊሙ ዓለም በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘ ነው። ዳሩ ግን እኛ ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ ሙስሊሞች ቁርዓን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይበልጣል ለሚለው አባባላቸው ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ

እንጠይቃቸዋለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚበልጠው በየትኞቹ ነጥቦች፥ ወይም ጭማሪዎች፥ ወይም ቅጥያዎች አማካኝነት እንደ ሆነ በሚገባ ለማወቅ እንፈልጋለን፤ እንዲሁም የትኛው የበላይ መረጃ በውስጡ እንዳለና መሐመድም ኢየሱስን የሚበልጠው ከምን አኳያ እንደ ሆነ ለማወቅ እንሻለን።

ከዚህም ሁሉ ባሻገር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡ ራሱ በግልጽ «ያ ከእናንተ መካከል ይመጣል» ይላል። ይህ ማለት ነቢዩ እይሁዳዊ ነው ከማለት ሌላ ሊሆን አይችልም።

ሙስሊሞች አንዳንድ ጊዜ «ከወንድሞቻቸው መካከል» (ማለትም የይስሐቅ ወንድም እስማኤል ስለ ሆነ፥ ከእስማኤል ይመጣል) መምጣትም አለበት በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንያቱም «ከእናንተ መካከል» የሚለው ሐረግ ከቃል ኪዳኑ ውጭ ያሉትን ሊያጠቃልል አይችልም። ይሁንና በነቢዩና በሙሴ መካከል ያሉትን የተመሳሳይነት ዝርዝሮች በማቅረብ ላይ ሳለን፥ ሌላውን ዝርዝር እንመልከት፡-

ሀ. በጊዜው እስራኤላውያን በባዕድ እገር አገዛዝ ሥር ነበሩ፤ ሙሴና ክርስቶስ የተወለዱት በጉስቁልና ነበር (ዘጸአት 1፡9-14)።

ለ. በሁለቱም ልደት ጊዜ የሞት ሤራ ተወጥኖባቸው ነበር (ዘጸአት 1፡15-16፥ 22፤ ማቴዎስ 2፡13-18)።

ሐ. ሁለቱም በመለኮታዊ ጣልቃ- ገብነት ከሞት ተርፈዋል (ዘጸአት 2፡2-10፤ ማቴዎስ 2፡13-15)።

መ. ሁለቱም በተአምራትና በድንቅ ተገልጠዋል (ዘጸአት 7፡10፥ 19፥ 20፤ ምዕራፍ 8-12፤ 14፡21-22፤ 17፡6-7፤ ማቴዎስ 8፡14-17፤ ሉቃስ 7፡11፤ ማቴዎስ 14፡13፤ ወዘተ)።

ሠ. ሙሴ በበረሃ ውስጥ ለእርባ ዓመታት ተዘጋጀ፤ ክርስቶስ ለእርባ ቀናት (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እርባ ቁጥር ዝግጅት ለማመልከት የቆመ ነው)። (የሐዋርያት ሥራ 7፡23ን ከዘጸአት 7፡7፤ ማቴዎስ 4፡1-11 ጋር ተመልከት።)

ረ. ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ «ታማኝ አገልጋይ»ተብለው ተጠርተዋል (ዕብራውያን 3፡2-5)።

ሰ. ሙሴ እስራኤልን ከጨቋኞቸው እስራት ነፃ አውጥቷቸዋል። ክርስቶስ ደግሞ አማኞችን ከኃጢአት እሥራት (በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ግብፅ ምሳሌ ከሆነችበት) ፈትቷል (ዘጸአት፥ ኢሳይያስ 53፡ ዮሐንስ 8፡32-36፤ ሮሜ 6፡18-22፤ 8፡2፤ ገላትያ 5፡1)።

ሸ. ውኃ ለሁለቱም ሥልጣን ተገዝቷል፡- ቀይ ባሕር ለሙሴ፥ የገሊላ ባሕር ለክርስቶስ (ዘጸአት 14፡21፤ 17፡6፤ ማቴዎስ 14፡22-33፤ ዮሐንስ 6፡16፤ ማቴዎስ 8፡18)።

ቀ. ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር «ፊት ለፊት» እንደ ተናገረ ሁሉ፥ ኢየሱስም መልኩ በተለወጠበት ተራራ ላይ እንዲሁ አድርጓል (ዘጸአት 33፡11፤ ማቴዎስ 17፡3)።

በ. ከዚህ ልምምድ በኋላ የሙሴ ፊት ሲያንጸባርቅ፥ የኢየሱስም ሁለንተና እንዲሁ ሆኗል (ዘጸአት 34፡29፤ ማቴዎስ 17፡2)።

ተ. ሙሴ የብሉይ ኪዳን መካከለኛ ነበር፤ ክርስቶስም ደግሞ የአዲስ ኪዳን ወይም የተስፋው ቃል መካከለኛ ነው (ዘጸአት ምዕራፍ 19 እና 20፤ ዕብራውያን 12፡24)።

ቸ. ሁለቱም ተፈጻሚነት ያገኙ ክስተቶችን ተንብየዋል (ዘዳግም 18፡15-22፤ 28፡15-29፥ 67፤ ማቴዎስ 24)።

ኀ. እይሁዶች በሁለቱም ላይ ዓመፀውባቸዋል። (ዘጸአት 5፡21፤ 14፡11-12፤ 17፡2-4፤ ዘኍልቁ 11፡1-33፤ ሉቃስ 4፡16-30፤ ዮሐንስ 11፡47-50፤ ማቴዎስ 26፡50-56፤ 27፡15-23፤ ወዘተ።)

ነ. ሁለቱም በኃጢአት ምክንያት ሞተዋል። ሙሴ ለራሱ ኃጢአት፥ ክርስቶስ ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት ሞቷል (ዘኍልቁ 20፡12፤ ዘዳግም፤ 34፡4-5፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3፤ ዮሐንስ 1፡29፤ 10፡14-16፤ ኢሳይያስ 53፤ ወዘተ።)

ኘ. ሙሴ ክሞት እንደ ተነሣ ለማመን በቂ ምክንያት አለን (ይሁዳ 9፤ ሉቃስ 9:30)። በወንጌል እንደ ተገለጸው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ክሞት እንደ ተነሣ ጥርጥር የለውም (ማቴዎስ 28:1-6፤ ሉቃስ 24፥ 34፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:4)።

አ. በሙሴ ሕይወት ውስጥ ከሁሉም የላቀውና ይጠብቀው የነበረው ክስተት እርሱ ክሞተ በኋላ ተፈጽሟል። ይኸውም ወደ ተስፋዪቱ ምድር መግባት ነበር። ክርስቶስም በኩል እንዲሁ ነበር፡- ክርስቶስ ክሙሴ በተለየ መንገድ በሞቱ እዲስ ሕይወት አስገኝቶልናል (ሮሜ 5:6-8፤ 8:34፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:3፥ 22፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5:15፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5:9-10፤ ወዘተ።)

በማጠቃለያ ሙሴ ውኃውን ከዓለት ውስጥ እንዳፈለቀና በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ያም ዓለት ክርስቶስ ነበር» እንደ ተባልን፥ እርሱም ደግሞ «ማንም የተጠማ ቢኖር፥ ወደ እኔ ይምጣ» (1ኛ ቆሮንቶስ 10:4፡ ዮሐንስ 7:37-38፤ 4:13-14) እንዳለ ለመግለጽ እንወዳለን።

እዚህ ላይ መታየት የሚችሉ ሌሎች መለስተኛ «ትንቢቶች» ቢኖሩም እስፈላጊዎች መስለው ስላልታዩን ትተናቸዋል። ነገር ግን እንድ ሙስሊም ስለ መሐመድ የተነገሩትን ክስተቶች እንደሚይዝ በማሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ቢደገፍና እነዚህም ትንቢቶች የመልእክቶቹን እውነተኛነት እንደሚያረጋግጡ ቢያስብ፥ ይህን በማድረጉ መጽሐፍ ቅዱስ ብልሽት ወይም ለውጥ እንዳልደረሰበት እንደሚመስክር ለማስገንዘብ እንወዳለን። ይህ ካልሆነ ግን በአሸዋ ላይ ቤት እየሠራ ነው ማለት ነው (ጂ. ክርስትንሰን)።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደ መጣልን

ሙስሊሞች የመገለጥን የ«ናዚል» ጽንስ- አላብ በመቀበልና፥ መጽሐፍ ቅዱስ በተለይም አዲስ ኪዳን የተሰጠበትን መንገድ በማየት «ይህ መገለጥ ሊሆን አይችልም» ብለው ይደመድማሉ።

የጻሐፊዎችን ቁጥር፥ ጽሑፎቻቸውም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የመሠራጨታቸውን ነገር፥ ከዚያም መስብሰባቸውንና የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደ ሆነ እንዳልሆነ በወሰኑት በተለያዩ እብያተ ክርስቲያን ጉባኤዎች መመርመራቸውን ይመለከታሉ።

«ራእይ» ወይም መገለጥ በሚለው ምዕራፍ ውስጥ (ከገጽ14 ቀጥሎ) ሐዋርያት ክርስቶስን፥ እባሎቹን፥ ሥራዎቹን፥ የሕይወቱን ልምምድና ባሕርዩን በጥልቀት ያውቁ እንደነበር ተረድተናል። እነርሱም የነጻ ደኅንነቱን የምሥራች ለሁሉም እንዲያውጁ ተመርጠዋል፤ የሚሰሙአቸውም ሰዎች እምነታቸውን በተጠናቀቀው የክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ እንዲያደርጉ ማስተማር ነበረባቸው። እነዚህና ሌሎች ሁለት ወይም ሦስት የሚሆኑ ሰዎች ናቸው እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ የጻፏቸው ዘገባዎች ዛሬ ተሰባስበው አዲስ ኪዳንን ያስገኙት።

እነዚህ ጽሑፎች ከተሰበሰቡ በኋላ፥ ሌሎች ብዙዎች፥ እንዳንዶቹም የበለጠ ተአማኒነት ያላቸው ለመምሰል በሐዋርያት ስም ተሠራጩ። እነዚህም በበጎ ዓላማ የተጻፉ ቢሆኑም ተረታ ተረቶች ነበሩ። እነዚህ ጸሐፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ያስቧቸውንና ከተጋነኑ እፈ ታሪኮች የተወደዱትን ሥራዎችንና አባባሎችን የእርሱ እንደ ሆኑ በማቅረብ፥ ኢየሱስን ሊያስከብሩ ፈለጉ። በቅዱላት መጻሕፍትና በእፈ ታሪክ መካከል መለየት የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ነበር። ደግነቱ፥ በዛሬው አመለካከት እንኳ ቢሆን፥ በሁለቱ መካከል መለየት እስቸጋሪ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ የሚያውቅ ሰው፥ እዋልድን (የእነዚህ ጽሑፎች ሁሉ ስብስብ) በሚያነብበት ወቅት፥ በእነዚህ ጽሑፎች በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን የባሕርይ ልዩነት ወዲያውኑ ያገኘዋል።

ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያት እንደ ሆኑ ከሚነገርላቸው ከማናቸውም ጽሑፎች ጋር በተጋፈጠችባቸው ጊዜያት ሁሉ በመጀመሪያው

ከታመነውና ተቀባይነት ካገኘው ክሐዋርያቱ ምስክርነት ጋር ታነጻጽራቸዋለች። ትምህርትም ሆነ ታሪካዊ ዘገባ መፈተን ሊያስፈልገው፥ ክርስቲያኖች ክሐዋርያት ዘገባዎች አንጻር ፈትነውታል። እነዚህም በነቢያት የተተነበየላቸውና በጠለቀ እውቀት ላይ የተመሠረቱ የዓይን ምስክር ዘገባዎች ነበሩ። ስለዚህም አዲስ ኪዳን በተወሰነ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፥ በተወሰኑ የጳጳሳት ቡድን በዘፈቀደ ተቀባይነት ያገኘ እንዳልሆነ በክፍተኛ የመተማመን ስሜት ልንናገር እንችላለን። ምርጫው ዓለም-አቀፋዊና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ብቻ አልነበረም፤ ቀደም ብሎ በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በግልና በራሳቸው ግንዛቤ በብዙ ዓመታት ውስጥ የተደረገ ውሳኔ ነበር። ምናልባትም ሊያላስብ የሚችል አነስተኛ ጉዳይ ቢኖር፥ እንደ አዲስ ኪዳን ሆኖ ተቀባይነት ያገኘው እጅግ ብዙ ከመሆን ይልቅ በጣም አናሳ መሆኑ ብቻ ነው። በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የተወገዙትን ጨምሮ፥ ምናልባትም ጥንታዊ መዛግብትን ሁሉ ማግኘታችን ትልቅ ዕድል ነው። ይህ የሐዋርያት ተብዬዎቹን የኋለኞች ጽሑፎች አያጠቃልልም። (ቀጥሎ ያለውን «የበርናባስ ወንጌል»ን ተመልከት።)

አሁንማ የውሳኔያቸውን አውነተኛነት ማረጋገጥ ወይም ውሸተኛነት ማጋለጥ እንኳን በምንችልበት ደረጃ ላይ ነን። በዘመናት ሁሉ ሊቃውንትና አማኞች በዚህ ረገድ ያልተስማሙበት ሁኔታ የለም። ከዚህ ተጨማሪ በሰው ግላዊ የሕይወት ልምምድ የሚታወቅ ዳሩ ግን በጣም ሚን ያለው ማረጋገጫ መገለጽ አለበት። ሕይወቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገነባበትና የሚታመንበት ሰው የሚሠራ ነገር አንደ ሆነ ያየዋል! በዮሐንስ 7፡17 ኢየሱስ ራሱ ይህን መፈተኛ ያቀርብልናል። ውጤቱም የተለወጠ ሕይወት ነው።

ብዙ ሙስሊሞች ክእግዚአብሔር የሆነው መጽሐፍ ከስማይ መውረድ አለበት የማለት አዝማሚያ ያላቸው ይመስላሉ። ቁርዓን እንደዚህ ዓይነት መጽሐፍ አንደ ሆነ ይነገራል። ነፃ አእምሮ ላለው ቅን አንባቢ «የቁርዓን ስብስብና ቅንጅት» የሚለውን ምዕራፍ «ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን እውነተኛ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ እንዲመለከት እንመክራለን (ክዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ባለው አድራሻ በመጻፍ መጽሐፉን ለማግኘት ይቻላል)።

የበርናባስ ወንጌል

ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን በተደጋጋሚ «የበርናባስ ወንጌል» በተባለው ነገር ስመገዳደር ይፈልጋሉ። የደቡብ አፍሪካው ሚስተር አዳም ፒርብሃይ በውስጥዋ የእዚህ «ወንጌል- መገኘት» ክስው ልጅ ታላላቅ ግኝቶች አንዱ እንደ ሆነ የሚመለክቱበት አንዲት አነስተኛ መጽሐፍ አሳትመዋል። በጣም አሳማኝ በሆነ መንገድ «የበርናባስ ወንጌል» ክአውነቶች ሁሉ በላይ አንደ ሆነ ይገልጻሉ (ስለ ኢየሱስና ስለ እግዚአብሔር ከአንድ የበለጠ እውነት ያለ ይመስል)። እንዲሁም ለ2000 ዓመታት ያህል ታፍኖ መቆየቱ ከሁሉ የከፋ የታሪክ አሳዛኝ ክስተት ነው ብለዋል። ሚስተር ፒርብሃይን ምንም እንኳ ቅዱስ በርናባስ ክክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አንዱ ቢሆንም (በመሠረቱ ግን አልነበረም!)፥ አሳስፈላጊ የሆኑ የእነ ማርቆስ፥ ሉቃስና ቅዱስ ጳውሎስ (!?) ወንጌላት ተጠቅሰው ላሉ፥ የእርሱ ወንጌል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አለመጠቀሱ አስደንቋቸዋል።

«የበርናባስ ወንጌል» ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ክምታስተምራቸው ከሌሎች ነገሮች ጋር ስለማይስማማ የተወችውና ያጠፋችው መዝገብ እንደ ሆነ ተገልጿል። ከዚህ ወንጌል አኳያ የመሐመድ መምጣት በግልጽ ተተንብዮአል። ክዚህ ወንጌል ቅጂዎች አንድ በተለየ ሁኔታ አንደገና በመገኘቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውሸትነት ላይ ምስክርነቱን ይሰጣል ተብሏል። አሁን እነዚህን ብሂሎች በሚገባ እንመለከታቸዋለን፥

1. ታሪክ

«የበርናባስ ወንጌል» (የበ. ወ) መጀመሪያ የተገኘው በ1709 ዓ.ም. በሆላንድ ነው። የተጻፈውም በጣልያንኛ ሲሆን፥ በተሰባበረ ዐረብኛ የግርጌ ማስታወሻዎችም ተስጥተውታል። የ«ወንጌሉ» ምንጮች አይታወቁም። አሁን ይህ መዝገብ በቪየና ቤተ መዘክር ውስጥ ተቀምጧል።

ጆርጅ ሴል በ1734 ዓ.ም ቁርአንን ክዐረብኛ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉመዋል። በመቅድሙም በእስፓንሽ ቋንቋ የተጻፈውን የዚሁን «ወንጌል» ሌላ ቅጂ ይገልጻሉ። ይህ መዝገብ ስለ ጠፋ ስለ እርሱ የምናውቀው ቢኖር፥ ሴል የጻፉትን ነው። በዚያም ላይ ሲናገር ሙስጠፋ ዲ አራንዳ (አራንዳ በእስፔይን የምትገኝ ከተማ ነች) በተባለ የእስፔይን ሙስሊም ክጣልያንኛ እንደ ተተረጐመ ይገልጻል። በተጨማሪም

የጣልያንኛው መጽሐፍ ፖፕ (አቡን) ስክስቱስ እምስተኛ እንቅልፍ ሽለብ አድርጎአቸው ላለ፥ ከፓፓል ቤተ መጽሐፍ ፍራ ማሪኖ በተባሉ መነኩሴ ተሰርቆ አንደ ነበር ይገልጻል። እርሱን ካነበቡ በኋላ ፍራ ማሪኖ ሙስሊም ሆኑ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ሙስሊሞች «የበርናባስ ወንጌል» እውነተኛ እንደ ሆነ ምናልባትም «የመጀመሪያው» ሳይሆን እንዳልቀረ ይናገራሉ። 1907 የበ.ወ. በሎራ እና በሎንስዴይል ራግ ወደ እንግሊዝኛ ተተረጐመ። በመግቢያው ላይ የበርናባስ ወንጌል የመካከለኛው ዘመን ማጭበርበሪያነቱ ውስጣዊና ውጫዊ መረጃዎችን ያቀርባሉ።

ከዚያን ጊዜ አንስቶ፥ የዐረብኛና የኡርዱ ቋንቋ ትርጉሞች ቢሠሩም ሁላቸውም ግን ያለ እነ ራግ መግቢያ ነበሩ። ሌ/ኮሎኔል ኤም.ኤ. ራሂም (ፓኪስታናዊ) አሁንም መግቢያውን በመተውና ከአስልምና ርዕዮተ- ዓለም አንጻር የተጻፈ ሌላ በመተካት የበርናባስ ወንጌል በ1973 በድጋሚ በእንግሊዝኛ እላትሟል። ይህንንም ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል ተስውሮ በኖረው ወንጌል ሊለካ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጦ እንደ ተበላሸ ለማሳየት በደንብ ተጠቅመውበታል። የበርናባስ ወንጌል ኢየሱስን በተመለከተ የአስልምናን ትምህርት በሚገባ የሚያጠናክር ነው።

2. ይዘቱ

የበርናባስ ወንጌል የተለየ ትረካ ነው የሚያቀርበው። ይህም ማለት የክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ዘገባ መሆኑ ነው። በአስልምና የሚታየው የኢየሱስ ማንነት የጎላበት እና በብዙ መሠረታዊ ትምህርቶች ረገድ፥ ተቀባይነት ካገኘው የወንጌል ዘገባ ውጪ ነው። ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ኢየሱስ ከርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም መለኮታዊ አይደለም። ይልቁንም ለመሢሑ መሐመድ መምጣት መንገድ ለማዘጋጀት «በምድረ በዳ የሚጮኽ ድምፅ» ነው። በበርናባስ ወንጌል ውስጥ ክርስቶስ መሢሕ አይደለም። ዳሩ ግን በወንጌላት ውስጥ መጥምቁ ዮሐንስ ከነበረው ጋር የሚመሳሰል ሚና እንዳለው ይገመታል። በበርናባስ ወንጌል ዮሐንስ መጥምቁ አልተጠቀሰም። ከዚህም የተነሣ በበርናባስ ወንጌል ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የዓለም አዳኝ የሆነው የመሐመድ መምጣት ነው (ምዕራፍ 96ለ እና 97ለ፤ ወዘተ)። እንደሚገመተው፥ ክርስቶስ አልተሰቀለም። በቦታው ግን ይሁዳ ተገድሏል ይላል። (ከሱረቱ 4፡156

ጋር አንድ ነው)። ክርስቶስ በእሥራቱ ጊዜ በጌቴሴማኒ በነበረው ቤት ውስጥ ተደብቆ ነበር። ከዚያም በአራት (1) ሊቃነ መላእክት (በጣም የቅርብ ጊዜ ወግ ወይም ተረታ ተረት) በመስኮቱ በኩል በመውሰድ ከሰባቱ ሰማያት ወዶ ሦስተኛው እርጓል።

ጠቅላላው የበርናባስ ወንጌል መሐመድ ከኢየሱስ በላይ መሆኑን ለማሳየት ጥረት ያደርጋል።

የእስልምና ተግዳሮት

1. «የበርናባስ ወንጌል» ሕልውና ከመካከለኛው ዘመን በፊት «በገላሲያ የእምነት መግለጫ» (ፓፕ ገላስዩስ 492-495 ዓ.ም.) እንደተረጋገጠ ተነግሯል። በዚህ የእምነት መግለጫ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የበርናባስን ወንጌል ከሴሎች አሥር ጽሑፎች ጋር እውነትነቱን በመጠራጠር አስወግዳለች። አሥሩም ጽሑፎች በታዴዎስ፥ በማትያስ፥ በጴጥሮስ፥ በያዕቆብ (ትንሹ)፥ በቶማስ፥ በበርቴሎሜዎስ፥ በእንድርያስ፥ ወዘተ. ስሞች የተጻፉ ነበሩ። ይህ የበርናባስ ወንጌል የተጻፈው በግሪክ ነበር። ዳሩ ግን ገላስዩስ አንዳዘጋጀው የተነገረው የእምነት መግለጫ ዘመን ብዙ አጨቃጭቋል። ከመቶ ዓመታት በኋላ ሊሆን ይችላል።

2. ሙስሊሞች የአቡን ስክስቱስ ቀዳማዊ የእምነት መግለጫ (456 ዓ.ም.) ከላይ አጠራጣሪ ሆነው የቀረቡትን ጽሑፎች እንደሚጠቅስ ይናገራሉ። ይህም ለው ከ402-417 ዓ.ም. አቡን ሆኖ እገልግሏል። ይሁንና በዚህ መግለጫ ውስጥ የበርናባስን ወንጌል የሚጠቅስ ነገር የለም።

3. ሙስሊሞች «የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ» እንዲሁ በ382 ዓ.ም. የበርናባስን ወንጌል ይጠቅሳል ይላሉ። ይህ በግልጽ የሚያመለክተው «የሮሜን ጉባኤ» ነው። ስለዚህ ጉባኤ የምናውቀው ሁሉ የሚመጣው ከገላስያ መግለጫ ነው። ይህም ከ(1) ጋር እንድ ዓይነት የሆነ ምንጭ ነው።

የበርናባስ ወንጌል እንደተጠቀሰ አንከድም። ዛሬ ስለ እርሱ የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን የበርናባስ አስመጻፍ አውነት ነው። አሊያም ቤተ ክርስቲያን ባላገለለችው ነበር። ከዚህም በላይ የተጠቀሱት «ወንጌላት»

የግጭበርበር ሥራዎች ስለ ሆኑ፥ እንደ ሐሰተኛ መጻሕፍት ታግደዋል። በርናባስ በሁሉም ስፍራ የተከበረ ነው። ይህን የሚቃረኑና በጳውሎስና በበርናባስ መካከል ስለ ተደረጉት ከርከሮች የሚነገሩ ዐረፍተ ነገሮች እውነት አይደሉም። በቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች የሚወጡ መግለጫዎች በዘፈቀደ በግለሰቦች የተዘጋጁ አይደሉም። ነገር ግን ማንኛውም መለኮታዊ እንደ ሆነ የተገመተው ጽሑፍ ሐዋርያዊ ምንጭ እንዳለው ለማረጋገጥ እጅግ ተቆርቋሪ በሆኑ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ነው።

ይህ ጉድለት የታየበት ማንኛውም ጽሑፍ ተትቷል። የፍራ ማሪኖ የበርናባስ ወንጌል በማንኛውም መንገድ በገላስያ መግለጫ፥ ተቀባይነት ካጣው የበርናባስ ወንጌል በፍጹም ግንኙነት እንደሌለው መረጃ አለ።

4. በ478 ዓ.ም. በቆጵሮስ መቃብሩ በተገኘ ጊዜ የበርናባስ ወንጌል ቅጂ በበርናባስ እቅፍ ውስጥ ተገኝቷል። በአፈ-ታሪክ እንደሚነገረው፥ በርናባስ በሕልም ለላለኑስ (ቆጵሮስ) ጳጳስ ተገልጾ «ዋሻና በዚያውም ውስጥ የሬሳ ላጥን ታገኛለህ። ምክንያቱም በዚያ ውስጥ እንደ ነበረ የተጠበቀው በድኔና በእጇ የተጻፈ ወንጌል ተቀምጦአል» ብሏል።

በእጋጣሚ ከዚህ በላይ የቀረበው ጥቅስ በዐረፍተ ነገሩ አጋማሽ ላይ ነው የሚያበቃው። በመጀመሪያው ጽሑፉ ውስጥ አንዲህ ሲል ይቀጥላል፡-

«ይህም ቅዱስ ሐዋርያና ወንጌላዊ ከሆነ ከማቴዎስ ያገኘሁት ነው።»

ስለዚህ በከንዶቹ ያደረገውን በራሱ የተጻፈውን የማቴዎስን ወንጌል እንደነበረ ተገምቷል። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የበርናባስ ወንጌል ዳግም አሳታሚዎች ከተርጓሚዎች ፈቃድ ላያገኙ ማላተማቸውና (የስውን ሥራ እንደ ራስ አድርጎ ማቅረብ) የምርምር ውጤቶቻቸው የሆኑትን ገላጭ ማስታወሻዎች ማስወገዳቸውንም እንግዳ ነገር ሆኖ እናገኘዋለን። እንዲሁም ሁሉም የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች በ200 ዓ.ም. በተግባር ተቀባይነት ያገኙ እንደ ነበሩ በየስፍራው ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ተስራጭተው እንደ ነበር ለመግለጽ እንሻለን። አከራካሪ የነበሩት የዕብራውያን፥ የ1ኛ እና የ2ኛ ጴጥሮስ፥ እንዲሁም የያዕቆብ መልእክት ሲሆኑ፥ ነገር ግን ከሮም ጉባኤ 382 ዓ.ም. በፊት ተቀባይነት አግኝተዋል። አስከዚያ ጊዜ ድረስ ወይም ከዚያ በኋላ ስለ በርናባስ ወንጌል ከቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንዳቸውም አልተጠቀሰም። ሌሎች የአዲስ

ኪዳን መጻሕፍት ግን በስም ወይም በጥቅሶች ስሚገባ ተጠቅሰዋል። የነበረና እውነተኛ የሆነ ሌላ የወንጌል ትረካ ደብዛ ላይተው አፈር በልቷል ማለት ታሪክ የማይቀበለው ነገር ነው።

ይህ ከቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ልምምድ ጋር የሚስማማ ወይም ከአስተዳደር መዋቅሩ እንጻር ሲታይ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም። ሙስሊሞች የበርናባስ ወንጌል የመጀመሪያ ወንጌል ነው ማለት ይወዳሉ። ምክንያታቸውንም ሲሰጡ፥ እራት የወንጌል ታሪኮች ካሉ፥ በእርግጥ አንድ የመጀመሪያ መኖር ይገባዋል ይላሉ። ስለዚህም ዳግም መገኘቱን በደስታ ይቀበላሉ።

የክርስቲያን መልስ

አንድ ወንጌል በጥንቃቄ ላይመረመር ይጣላል ማለት ዘበት ነው። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተመረጡት በመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሆን፥ ይህም የሚሆነው ከሐዋርያት የተገኙ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ይህም ማለት ሐዋርያት እንደማያውቋቸውና በዘመናቸው እንደ ሆኑ ሁሉ፥ ከክርስቶስ ትምህርት ጋር ሲስማሙ ነው። የበርናባስ ወንጌል እነዚህን ሁኔታዎች አያሟላም።

ውጫዊ መረጃ

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር ከእርሱ ውጭ ከሆኑ ምንጮች የተሰበሰበ ማረጋገጫ ማለት ሲሆን ይችላል (ቪ.ኤች.ቲ. ጌይርድነር ገጽ 9)። ብቸኛው የበርናባስ ወንጌል ማጣቀሻ የሚገኘው ሐዋርያዊ መረጃና እውነተኛ ይዘት በማጣቱ ምክንያት ተቀባይነት ማጣቱን በሚያረጋግጠው እዲስ ኪዳን ተጠናቅቆ ረዥም ጊዜ ካለፈ በኋላ በወጣው በገላስያ መግለጫ ውስጥ ነው። የሚከተሉት አውነቶች ስለ በርናባስ ወንጌል መኖር ውጫዊ መረጃ እንደሌለ ያሳያሉ።

1. ከሐዋርያት አስከ ገላስያ መግለጫ ባለው ጊዜ ውስጥ ወይም ከዚያ በኋላ ስለ በርናባስ ወንጌል የሚጠቅስ ነገር የለም።

2. የተወሰኑ የሙስሊም ሊቃውንት የበርናባስ ወንጌል ማጭበርበሪያ መሆኑን የሚያረጋግጠውንና በእነ ራግ ትርጉም ውስጥ የሚገኘውን ነገር በማስወገዳቸው ታማኝነት እንደሚጐድላቸው ማላየታቸው፥ ስለ በርናባስ መቃብርና በከንዱ ላይ ስለ ነበረው ወንጌል ይናገራል

> የተባለውን ዐረፍተ ነገር ግማሽ ክፍል ማስቀረታቸው እና የበርናባስ ወንጌልን እንደ ፀረ-ክርስቲያን የመከራከሪያ እላብ ቢያናፍሱትም ውጫዊ መረጃ ሊሆናቸው አልተቻለም። ይልቁንም በሐቀኝነታቸው ላይ ጥርጣሬ ያስነሣል።

በመሠረቱ እውነተኛው «የበርናባስ ወንጌል» ስለ መኖሩ ተቀባይነት ያለው መረጃ የለም።

የፍራ ማሪኖ ስከስቱስ እምስተኛ (1585-1589 ዓ.ም.) ቤተ መጻሕፍት ውስጥ የበርናባስ ወንጌል የማግኘት ዘገባ ሊታመን የሚችል ዓይነት አይደለም።

> «በአጋጣሚ ኤሬኒዮስ (ከቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ) የበርናባስ ወንጌልን እንደ መረጃ በመጥቀስ ጳውሎስን እየነቀፈ ካስፈረው ጽሑፍ ጋር በመገናኘቱ ይህን ወንጌል የማግኘት ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት አደረበት። እንዲሁም አግዚአብሔር «ከአቡኑ ስከስትስ አምስተኛ ጋር ስጣም እንዲቀራረብ አደረገው። እንድ ቀን በአቡኑ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ እያሉ ቅዱስነታቸው እንቅልፍ ጣላቸውና የሚያነበውን መጽሐፍ ፈልጎ የዘረጋው እጁ ስዚያ በፈለገው መጽሐፍ ላይ አረፈ። በደስታም ፈነደቀ... ሽልማቱንም ለመደበቅ እላመነታም... እቡኑ ሲነቁ ተስናብቶአቸው ያንን ቅዱስ መዝገብ ይዞ ሄደ። አርሱም በማንበብ ወደ መሐመዳውያንነት ተለወጠ።

ኤራኒዮስ ስለ በርናባስ ወንጌል በፍጹም እንዳልጠቀሰ፥ ወይም ጳውሎስንም በመቃወም እንዳልተናገረ እንረዳለን። የጳውሎስን ጽሑፎች በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት አንደ ተጻፉና አራቱ የታወቁ የወንጌል ትረካዎችም ብቻ ከአግዚአብሔር እንደ ተሰጡ እድርጎ ተቀብሏል። (ጌይርድኔር ገጽ 12)። ተአማኒነት ያለው አንድ ሥነ-ጽሑፍ ካለን ይህ ራሱን የቻለ መረጃ ሊሆን ይችላል። ተአማኒነቱን ለማረጋገጥ ማናቸውም ውሸቶች እያሰፈልጉትም። ሚስተር አዳም ፒርብሃይ ስለ በርናባስ በ«ኢዝላሚስኮፕ» ላይ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡-

> «ስሙ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ለግልጽ ዓላማ ተወግዷል።»

ምንም እንኳ ከበዓለ-ጎምላ በኋላ በመለወጡ በወንጌላት ውስጥም ባይሆንም፥ የበርናባስ ስም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሃያ ጊዜ መጠቀሱን ሚስተር ፒርብሃይ አላስተዋሉም። ራሂም በእትሙ መቅደም ላይ ስለ ጳውሎስና በርናባስ የሚከተለውን ይዘግባል፡-

> «ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ ተለያይተዋል እናም በርናባስ በምሥጢራዊ መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ላይ ታጥቷል» (ከርትዚንገር፥ ገጽ 9)።

ጳውሎስ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ስለ በርናባስ በጣም እድርጎ በ1ኛ ቆሮንቶስ 9፡6 ላይ ስለሚናገር፥ ይህም ደግሞ ስሕተት ነው። እንዲሁም ጳውሎስ የበርናባስ ወንድም ልጅ ከነበረው ከማርቆስ ጋር ግንኙነቱን መልሶ እስተካከሏል። (ቈላስይስ 4፡10 እና 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡11)። በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የመከራከሪያ ነጥብ የነሳረው እርሱ ነበር። ይህም በሁለተኛው የጳውሎስ የሚሊዮናዊነት ጉዞ ላይ ለመለያየት እንዲወስኑ እድርጓቸዋል።

ውስጣዊ መረጃ

ይህ ከራሱ ከመጽሐፉ ይዘት የሚገኝ ነው። ማንኛውም መጽሐፍ የአንድ የተወሰነ የዘመን ምልክት እንደሚኖረው እውን ነው። ስልቱ፥ ቋንቋውና የመጽሐፉ ዐቢይ ነጥብ ይህንን ለማድረግ ይረዳል (ጌይርድኔር ገጽ 9)።

በመጀመሪያ በበ.ወ. ውስጥ የቀረቡት የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች የተወሰዱት ከሹልጌት ትርጉም (በግምት 380 ዓ.ም.) መሆኑን ለመመልከት እንሻለን። ይህ የላቲን መጽሐፍ ቅዱስ እስከ አሁን ድረስ ከአገልግሎት ላይ የዋለው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የበ.ወ. ሹልጌት ከመጻፉ በፊት አንደ ተዘጋጀ ስለሚገመት፥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው መጽሐፉ የተቀነባበረበት ወቅት መዛባቱን የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

> «እንድ ሰው የማላይህ ፊልም በ1905 የተሠራ ነው ቢልህና የሚታየው እያንዳንዱ ነገር ዘመኑ ባለፈበት ፊልም እንደሚታየው የድሮ ልብሶችና ፋሽኖች ያሉበት ቢሆንብህ፥ ምናልባት ታምነው ይሆናል። ነገር ግን በትዕይንቱ መሀል አንድ ኮንኮርድ (እጅግ ዘመናዊ

አውሮፕላን) ወደ ስግይ እየመጠቀ ብታይ፡- (ይህ ፊልም ፈጠራ ነው) ትላለህ» (ጆን ጊልክርስት)።

አንዲህ ነው እንግዲህ የወቅት መዛባት ግለት። የበ.ወ. ስዚህና ለሌሎችም ሙከራዎች እንዴት ብቁ ሊሆን ይችላል?

1. በበ.ወ. በምዕራፍ 1 «በርናባስ» ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቷል። ይህ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች አንጻር ትክክል አይደለም። ምንም እንኳ በርናባስ እንደ ሐዋርያ የተጠቀሰ ቢሆንም (የሐዋርያት ሥራ 14፡4፥ 14)፥ የበ.ወ. አሳብ ፍጹም ልዩ ነው። በርናባስ የተለወጠው ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ ሲሆን፥ በዚህም ምክንያት በሐዋርያት ሥራ 1፡21-22 እንደ ተጠቀሰው የሐዋርያነትን መስፈርት አያሟላም። (እንዲሁም 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡8፤ 9፡1-2፥ 1፡1፤ ሮሜ 1፡1፤ ወዘተ ልብ ማለት ያሻል።)

2. የበ.ወ. አንባቢ ናዝሬትን በገሊላ ሐይቅ ዳርቻ ሲያገኛት ይደንቀዋል (ምዕራፍ 20)። ዳሩ ግን ከተማዪቱ የምትገኘው ከሐይቁ በጣም ርቃ በተራራዎች ተከብባ ነው።

3. በቀጣዩ ምዕራፍ ኢየሱስን ወደ ቅፍርናሆም ሽቅብ ሲወጣ እናገኘዋለን። ቅፍርናሆም ግን የምትገኘው ከሐይቁ ዳርቻ (ዝቅተኛ ስፍራ) ላይ ነው።

4. በምዕራፍ 151 ኢየሱስ በመርከብ ተሳፍሮ (ከናዝሬት?) ወደ ኢየሩላሌም እንደ ደረሰ እናነባለን። ይህ ደግሞ በጀልባ ተደርጎ አንደ ሆነ መጠየቃችን አይቀርም።

5. በምዕራፍ 6 ሌላ አስገራሚ ተራ ስሕተት ይገኛል። እዚህ ላይ ስለ ስብዓ ስገሎች ወይም ክምሥራቅ ስለ መጡት አዋቂዎች ይናገራል። አዲስ ኪዳን የሰዎቹን ቁጥር አይወስንም። ነገር ግን ስብዓ ስገሎቹ ያመጡዋቸውን ሦስት ስጦታዎች ወርቅ፥ ዕጣን፥ ከርቤ በማለት ይዘረዝራል። ይህም ወደ በኋላ ከምሥራቅ የመጡ ሦስት ስዎች ናቸው ወደሚል ግምት አምርቷል። ነገር ግን ይህ ከአዲስ ኪዳን የተወሰደ ወይንም የዚያን ዘመን እምነት አይደለም።

6. በምዕራፍ 91-92 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ «40ዎቹን ቀናት» አንደ ጠበቁ እናነባለን። ዓውደ-ንባቡ ይህ በቤተ ክርስቲያን የተከበረውንና ከፋሲካ በፊት ያለውን የ40 ቀናት ጊዜ እንደሚጠቅስ በግልጽ ያሳይል። የተከበረው ግን ከመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ብዙ ዘግይቶ ነው። (ቤተ ክርስቲያን በዚህ ወቅት በኢየሱስ መከራ ላይ የጽሞና ጊዜ የመውሰድ ልምምድ ታደርጋለች። ይህ ኢየሱስ በሕይወት ላለ አለመታወቁ መቼም ግልጽ ነው።) ኮዳዴ መከበር የጀመረው ክ4ኛው ምእተ ዓመት ጀምሮ እንደ ሆነ እንረዳለን። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ለ40 ቀናት ጾም ወደ ሲና ተራራ እንደ ሄዱ ተገልጿል። ይህም 450 ኪ.ሜ. ያህል ርቀት ያለው ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህን የሚያጠናክር መረጃ የለም።

7. በተጨማሪም አንድ ግጭት በሙርነት ሊያክትም እንደ ነበርና ዳሩ ግን ሮማውያን እያንዳንዳቸው 200000 የሆኑ ሦስት ምድብ ሠራዊቶች በምጽጳ እንዳሰባሰቡ እናነባለን (ምዕራፍ 91)። ይሁንና በዚያን ጊዜ የነበረው የሮማ ወታደር 300000 ብቻ ነበር (ኤንላይክሎፒዲያ ብሪታኒካ)።

8. «ኢየሱስ ወደ ካህኑ (ሊቀ ካህናት) በአክብሮት ቀረበ። እርሱ ግን ወድቆ ለኢየሱስ ሊሰግድ ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ ግን ጮኾ (የሕያው እግዚአብሔር ካህን ሆይ፥ ምን እንደምታደርግ እስተውል! በእምላካችን ላይ ኃጢአት አትሥራ» (ምዕራፍ 93) ብሏል። ይህ ዐረፍተ ነገር ከአዲስ ኪዳን ጋር በግልጽ ስለሚቃረን ማብራሪያ አያሻውም።

9. በበ.ወ. ምዕራፍ ሦስት የክርስቶስ ልደት ምጥ-አልባ እንደ ነበር ተገልጿል። ይህ አምነት ክቶማስ አክዊነስ (1274) በፊት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልተለመደም ነበር። ነገር ግን በሉረቱ 19፡23 ላይ ተገልጿል።

10. በበ.ወ. መሠረት ኢየሱስ የተወለደው ጲላጦስ ንጉሥ ሆኖ ሳለ ነው። ነገር ግን እርሱ የነገሠው በ26ና 27 ዓ.ም. መካከል ብቻ ነው።

11. በዘ.ወ. መሠረት ኢየሱስ በቀን አምስት ጊዜ የሚጸልይ ሲሆን፥ የሙስሊም የጸሎት ጊዜያትም በሙሉ ተጠቅሰዋል (ዶ/ር ጂ. ሰሎሞፕ ገጽ 128)።

12. «ድንግል» የሚለው ግዕረግ ለግርያም የተሰጣት ከ4ኛው ምእተ ዓመት በፊት አልነበረም። ይሁንና በዘ.ወ. ውስጥ ይገኛል።

13. ከ184-254 ዓ.ም. የነበረው አሪገን፥ ታቦር የተባለው ተራራ ኢየሱስ የተለወጠበትና መልኩ ያንጸባረቀበት ስፍራ መሆኑን በመገመት የመጀመሪያው ሊቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን አይደግፈውም። የሞሪያ ተራራ እንደ ሆነ የሚናገረው የክርስትና ባህል በሦስተኛው ምእተ ዓመት ብቻ ነው የተጀመረው፤ የበ.ወ. ግን ይህን መልእክት ይይዛል።

14. የበ.ወ. አራት ሊቃነ መላእክትን ይጠቅሳል። ይህም ደግሞ ከመጀመሪያው የመከከለኛው ዘመን ክፍለ ጊዜ የነበረ የቤተ ክርስቲያን ወግ ነው።

15. የእስልምና የ«መጽሐፉ» ጽንሰ-አሳብ በምዕራፍ 10 ውስጥ ይገኛል። በዚህም ስፍራ መጽሐፉን እንደሚያብረቀርቅ መሰተዋት መልአኩ ገብርኤል ለኢየሱስ እንደ ሰጠውና መጽሐፉም ወደ ልቡ እንደ ዘለቀ እናነባለን። ይህ ከሱረቱ 5:49 እና 2:97 ጋር በደንብ ይመሳሰላል።

16. በምዕራፍ 54 ውስጥ፥ የጣልያንኛው መጽሐፍ በ60 ሚኑቲ ሰለሚመነዘረው ዲናር ይናገራል። እነዚህ የወርቅ ሣንቲሞች ያገለገሉት በካሊፍ አብዱል መሊክ ዘመን (በ685 ዓ.ም.) በእስፔይን አገር ብቻ ነው።

17. በምዕራፍ 152፥ ወታደሮች «እንድ ሰው ወይንን መልሶ ለመሙላት የእንጨት በርሜሉን ሲያጥብ እንደሚያንከባልሰው እንዲሁ ከቤተ መቅደስ ተጠርገው እንደ ተወገዱ» እናነባለን። የእንጨት በርሜሎች የተሠሩት በጎል አገር ሲሆን፥ በአዲሰ ኪዳን ዘመን በምሥራቁ ዓለም አገልግሎት አይሰጡም ነበር። ወይንና ሌሎችም መጠጦች ከቆዳ በሚሠራው አቁማዳ ውስጥ ይቀመጡ ነበር።

18. በምዕራፍ 97 መሐመድ በግልጽ መሢሕ ተብሎ ተጠርቷል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ቁርዓንም ይህንን ማዕረግ የሚጠቀመው ለኢየሱስ ነው። በዘ.ወ. መግቢያ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ መጠራቱና በምዕራፍ 42 እና 82 «በርናባስ» የኢየሱስን መሢሕነት መካዱ ለመረዳት የሚያስቸግር ነገር ነው። እንዲህ ያለ ዐረፍተ ነገር መጻፍ የሚችለው በሥነ-መለኮት እጅግ መሀይም የሆነ ሰው ብቻ ነው። ምክንያቱም «ክርስቶስ» የሚለው የግሪክ ቃል ለዕብራይስጡ «መሢሕ» የቆመ ነው።

19. «በእውነተኛው የሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ... እስማኤል የመሢሑ አባት፥ ይሰሐቅ ደግሞ የመሢሑ መልእክተኛ አባት» እንደ ሆነ ተጽፎአል (ምዕራፍ 191)።

20. የመጨረሻው የበርናባስ ወንጌል ምዕራፍ በሆነው በምዕራፍ 222 ውስጥ የሚከተለውን እናነባለን፡-

«ኢየሱስ ከተለያቸው በኋላ (በጌቴሴማኒ የአትክልት ሰፍራ ተደብቆ ከነበረባት ቤት ውስጥ በመሰኮት ከተነጠቀ በኋላ) ደቀ መዛሙርቱ በተለያዩ የእስራኤል ግዛቶች ውስጥ ተበተኑ፤ በዓለምም ሁሉ ተሠራጩ። እንዲሁም ሁልጊዜም እንደሚደረገው በሰይጣን የተጠላው እውነት በሐሰት ተሰደደ። ምክንያቱም የተወሰኑ ከቱ ሰዎች ደቀ መዛሙርትን መስለው ኢየሱስ ሞቶ አልተነሣም እያሉ መሰበክ ያዙ። ሌሎች ደግሞ በእርግጥ ሞቷል፤ ነገር ግን ተነሥቷል ብለው ሰበኩ። ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ስብከዋል፤ እየሰበኩም ነው። ተታልለው ይህንን ከሰበኩት መካከል አንዱ ጳውሎስ ነው።»

እዚህ ላይ የበርናባስ ወንጌል የቀደሙትን ወንጌላትና ጳውሎስን ለማረም ይጥራል። ጸሐፊው ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ሁሉ መበተናቸውን ያወቀው መቼና እንዴት እንደ ሆነ ለመጠየቅ እንፈልጋለን። ይህ ጥያቄ ምላሽ የማያገኙበት ቢሆንም፥ እኛ በቀላሉ እንመልስዋለን። ምክንያቱም ይህ ደግሞ የሌለውን እንዳለ አድርጎ የማቅረብ ሌላው ገጽታ እንደ ሆነ እናምናለንና!

21. የኢጣሊያው ገጣሚ ዳንቴ የበርናባስ ወንጌል በተዘጋጀበት ወቅት አካባቢ (1265-1321 ዓ.ም.) የኖረ ሰው ነው። ከዳንቴ ሥራዎች

ውስጥ በርካታ ጥቅሶች በበርባናስ ወንጌል ውስጥ መገኘታቸው አስገራሚ ነው። እጅግ ብዙ ስለ ሆኑ፥ እንደ አጋጣሚ የተገኙ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም። የበ.ወ. ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንዲህ እንዳለው ይጠቅሳል፡- «ሲ*ያል አንድ ሲሆን፥ ነገር ግን አንዱ ከሌላው ግርጌ የቀጠለ ሰባት ማዕከሎች እንዳሉት እወቅ። ስለዚህ ኃጢአት ሰባት ዓይነት እንደ ሆነ ሁሉ፥ ለይጣንም ሰባት የሲ*ያል ደጆች አሰናድቷል። በዚያም ውስጥ ሰባት ቅጣቶች አሉ» (ምዕራፍ 135ሀ)።

ይህ በቀጥታ ዳንቴ «ኢንፈርኖ» በተሰኘው መጽሐፉ በካንቶስ 5፥ 6፥ ወዘተ... ውስጥ የሚናገረው ነገር ነው። እንዲሁም በርናባስ አግዚአብሔር ለብአዊ ስሜቶችን ከፈጠረ በኋላ «ለሲ*ያልና ለኃይለኛ በረዶ» (ምዕራፍ 106) እላልፎ በመስጠት እንደ ኮነነ ይናገራል። ይህም ከካንቶስ 28 እና 3 ከ«ኢንፈርኖ» ጋር የሚስማማ ነው። የሰብአዊ ኃጢአቶች ገለጻና ልክ እንደ ወንዞች ምንጫቸው ወደ ሆነው ሰይጣን መመለሳቸው፥ የተጠቀሰው ዳንቴ ስለ ሲ*ያል ወንዞች ከጻፈው በተዘዋዋሪ መንገድ የተወሰደ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ አማኞች ለመሠቃየት ሳይሆን፥ የማያምኑት ሲሠቃዩ ለማየት ወደ ሲ*ያል ስለ መሄዳቸው የሚናገሩ ምንባቦች የዳንቴን ገለጻ ያስታውሱናል። በከብር ደረጃዎች መካከል ልዩነቶች ለመኖራቸውና ማናቸውም ዓይነት ቅራኔዎችም ሆነ ምቀኝነቶች በሰማይ ላለመገኘታቸው የተደረገው ገለጻም ከዳንቴው «ገነት»፥ ካንቶስ 3 ሙሉ ለሙሉ የተወሰደ ነው። በተጨማሪም «በርናባስ» በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዳንቴ ለመጥቀሱ የበለጠ መረጃ የሚሆነው «ስለ ሰማዩ መልከአ-ምድር» ያቀረበው ገለጻ ነው። በዚያ ውስጥ «በርናባስ» ከዳንቴ ጋር በመስማማት ከቁርዓን ከራሱ ጋር እንኳ ይቃረናል። ቁርዓን (ሱረቱ 2፡29) ሰባት ለማያት እንዳሉ ሲናገር፥ «በርናባስ» ግን ቁጥራቸውን ወደ ዘጠኝ ከፍ ያደርገዋል (ምዕራፍ 178 ሀ) (ጌይርድኔር፥ ገጽ 19-21)።

እነዚህ ጥቂት ጥቆማዎች የበርባናስ ወንጌል ጸሐፊ ከዳንቴ ጽሑፎች ጋር እውቂያ እንደ ነበረውና ከዚህ የተነሣ ከዳንቴ በኋላ እንደ ኖረ፥ ወይም ደግሞ በእርሱ ዘመን እንደ ነበረ ለማረጋገጥ በቂ መረጃዎች ናቸው።

22. በበርባናስ ወንጌል ምዕራፍ 145 ውስጥ ፈሪሳውያን እስከ ኤልያስ ዘመን ርቀውና 17000 ሆነው እናገኛቸዋለን። በመሠረቱ ታሪክ ስለ ፈሪሳውያን የሚያውቀው ከሰባት ምእተ ዓመታት በኋላ ከ135-104 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

23. በምዕራፍ 82 «እሁን በየ100 ዓመቱ ሰለሚመጣው የኢዮቤልዩ በዓል» በመባል የተደረገ ገለጻ እናገኛለን። የኢዮቤልዩ በዓል በብሉይ ኪዳን ይከበር የነበረው በየ50 ዓመቱ (ከሰባት ጊዜ ሰባት በኋላ) ነበር። የዚህ የተሳሳተ መረጃ ምንጭ እንደሚከተለው ነው፡- በ1300 ዓ.ም. አቡን ቦኒፌሰ 8ኛ ኢዮቤልዩን የአንድ መቶ ዓመት ክስተት አድርገው አቋቁመውታል። ይሁንና የምጣኔ ሀብቱን ሰኪታማነት በማሰብ አቡን ከለመንት 6ኛ የቦኒፌስን ውሳኔ ሽረው ቀጣዩን ኢዮቤልዩ በ1350 አከብረዋል። የኢዮቤልዩ በዓል የአንድ ምእተ ዓመት ክስተት እንዲሆን የተፈለገበት ጊዜ ይህ ብቻ ነበረ። በተግባር ላይም እልዋለም ነበር (ጌይርድኔር፥ ገጽ 19)።

24. ሔዋን በገነት ውስጥ የ«ፖም» ፍሬ እንደ በላች ተጽፎአል (ምዕራፍ 40 ና 41)። ሔዋን የበላችው ተለይቶ በስሙ ያልተጠራ ፍሬን እንደ ሆነ በሚገባ እናውቃለን። ነገር ግን ፍሬው የፖም ነው የሚለው እምነት እጅግ ቅርብ ከሆነ ወቅት የተነሣ ነው።

25. የበርናባስ ወንጌል የመነጨው በመካከለኛው ዘመን መሆኑን የሚያሳየው ሌላው ማረጋገጫ በሁለት ተቀናቃኝ አፍቃሪዎች መካከል የተደረገ ፍልሚያ ተመዝግቦ መገኘቱ ነው (ምዕራፍ 99)። የዚህ ዓይነቱ የጀግንነት ተግባር የመካከለኛ ዘመን ማኅበረሰብ ፈጠራ ነው (ጌይርድኔር ገጽ 24)።

26. በ80 ኛው የበርናባስ ወንጌል ምዕራፍ ውስጥ ዳንኤል በናቡከደነፆር ተማርኮ የተወሰደው ገና በሁለት ዓመቱ እንደ ሆነ የሚናገር ታሪክ እናገኛለን። ይህ ዐረፍተ ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ቢተያይ፥ የሚጣጣም አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ መሠረት፥ ናቡከደነፆር ዳንኤል የተረጐመለትን አስደናቂ ሕልም ያየው በሁለተኛ ዘመነ-መንግሥቱ ነበር።

«ንጉሡም ዳንኤልን ክፍ ከፍ አደረገው፥ ብዙም ታላቅ ስጦታ ሰጠው፥ በባቢሎንም አውራጃ ሁሉ ላይ ሾመው፥ በባቢሎንም ጠቢባን ሁሉ ላይ ዋነኛ አለቃ አደረገው» (ዳንኤል 2፡48)።

ናቡከደነፆር ዳንኤልን የማረከው በመጀመሪያው ዘመነ-መንግሥቱ ነው ብንል (ዳንኤል የተማረከበትን ጊዜ ከዚህ በላይ ወደ ኋላ መግፋት አይቻልም) እና በ«በርናባስ» ዘገባ መሠረት ያኔ ዳንኤል የሁለት ዓመታት ልጅ ቢሆን፥ በሁለተኛው የናቡከደነፆር ዘመነ-መንግሥት፥ ዳንኤል ምስት ዓመቱ ብቻ ነበረ ማለት ነው (ጌይርድኔር ገጽ 26)። በመሠረቱ ዳንኤል የተወለደው በ621 ዓ.ዓ. ስለ ሆነና ምርኮውም በ605 ዓ.ዓ. ስለ ተጀመረ፥ በምርኮ በተወሰደ ጊዜ የ16 ዓመታት ልጅ ነበር።

27. እስማኤል በመሠውያው ላይ በአብርሃም እንደ ቀረበ (ምዕራፍ 44) እናነባለን። ይህ በመሠረቱ አስላማዊ ጽንስ-አሳብ ነው።

28. በምዕራፍ 212፥ እግዚአብሔር የአብርሃም የእስማኤልና የይስሐቅ አምላክ ነው ተብሏል። በብሉይ ኪዳን መሠረት የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ መባል ነበረበት።

29. ተውራት (ሕግ) በእስማኤላዊ ተጽፎአል የሚለውን እጅግ አጠራጣሪና የተሳሳተ ሆኖ እናገኘዋለን (ምዕራፍ 192)።

30. በእርግጥ ከሁሉም የሚያጠራጥረው የመሐመድ ስም መጠቀስ ነው (በምዕራፍ 44፥ 54፥ 112፥ 97 እና 163፤ ወዘተ.)። በተለይም ሌላው መረጃ ሁሉ የበርናባስ ወንጌል የመከከለኛው ዘመን ግጭበርበሪያ መሆኑን ስለሚያመለክት፥ በጣም አጠራጣሪ ነው። ሌላ አስላማዊ አሳብም በዚህ የበርባናስ ወንጌል ውስጥ ተንጸባርቆአል።

31. በምዕራፍ 39 አዳም ደግቅ ጽሑፍን ሲመለከት፥ ይዘቱ ከካሊማ የተለየ አይደለም፡- «አንድ አምላክ ብቻ አለ» እንዲሁም «መሐመድ የአምላክ መልእክተኛ ነው።»

32. የበርናባስን ወንጌል የሚቀበሉ ሙስሊሞች በምዕራፍ 115 ውስጥ የአንድ ለአንድ ጋብቻ አጥብቆ እንደሚደግፍ ማየት ነበረባቸው።

33. እንደዚሁም የእስልምናው የፍቺ መመሪያ የተተወበትን ምዕራፍ 38ን እንመለከታለን።

ማጠቃለያ

መጽሐፉን ከመረመርን፥ የውስጥና የውጪ መረጃዎችን ካገላበጥን፥ እንዲሁም የመካከለኛው ዘመን ባሕርይ እንዳስውና ይህን ወንጌል እስላማዊ ለማድረግ የተደረገውን ጥረት ከተረዳን በኋላ፥ የበርናባስ ወንጌል ክርስቲያኖችን ስለ «እስልምና እውነት» ለማሳመን በአንድ ሙስሊም የተጻፈ ነው ብለን እናጠቃልላለን። እስልምናን በቀጥታ ከማወጅ ይልቅ፥ መልእክቱን ሌላ አስመስሎ አባባሉንም እውነተኛ ለማስኘት የበርናባስን ስም ተጠቅሟል። ስለ ሆነም ይህ የተጭበረበረና ሐሰት ነው። የታለመውም በመስቀል ላይ የተፈጸመውን የክርስቶስን የስርየት ሥራ ጨምሮ የክርስትናን መሠረታዊ እምነት በማጥፋቱ ላይ ነው። ክርስቲያኖች ግልጽ በሆኑ ምክንያቶች እንደዚህ ያሉ የማጭበርበርና የመዋሸት ዘዴዎችን አይቀበሉም።

ምራቃቸውን የዋጡ ሙስሊሞች ውሸትነቱን እያወቁ እንዲህ ያለ መጽሐፍ በማዘጋጀት እንደዚህ በመሳሰሉ ደካማ መሠረቶች ላይ ማስፋፋታቸውን ስንመለከት ግራ ይገባናል። እንዲህ ያለው ነገር ፈታኝና የግል ጥቅም የሚሰጥ ቢሆን እንኳ፥ መተው አለበት። እኛ ይህን እውነትን ለመሸፋፈን እንደ መሞከርና እንደ ከንቱ ጥረት አድርገን እንመለከታለን። ለተሻሉ ክርክሮች ምላሽ በሚያጣበት ጊዜ ብቻ ታማኝ ያልሆነ ሰው ወደ እነዚህ ዘዴዎች ዘወር እንደሚል በማሰብ እናጠቃልላለን።

መጽሐፍ ቅዱስ፡-

> «ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ» (ኤፌሶን 5፡11)።
>
> «ነገር ግን የሚያሳፍረውን ሰውር ነገር ጥለናልና በተንኰል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡2) በማለት ያስተምረናል።

ዋቢ መጻሕፍት፡-

(Sources):

1."The Gospel of Barnabas" edited and translated by Lonsdale and Laura Ragg (1907), published by
Begum Aisha Bawany Wakf

Bank House No.1

Habib Square

M.A. Sinnah Road

Karachi-pakistan

2. "The Gospel of Barnabas, an Essay and Inquiry" by Selim 'Abdul-Ahad and W.H.T. Gairdner. (1975)
Publishers, "Henry Martyn Institute of Islamic Studies".

P.0. Box 153, Hyderabad India.

3. "Pseudo-Barnabas in the context of Muslim-Christian Apologetics" by Dr. Jan Slomp. (1974)
published by: "Christian Study Centre"

126-B Murree Road, Rawalpindi,

pakistan

4. A paper by J.N.J. Kritizinger entitled "The Gospel of Barnabas Carefully Examined"

5. "Origins and Sources of the Gospel of Barnabas" by John Gilcbrist, 4b Bright Street, Benoni 1500

6.. "Missing Documents from the Gospel of Barnabas" by Adam Peerbhai

የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለምን በዙ?

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችን ይህን ጥያቄ ይጠይቃሉ። በተመሳሳይ መሠረት ላይ ለመቆም፥ እስኪ ላንድ አፍታ በሙስሊሞች መካከል ያሉትን ክፍፍሎችና ቡድኖች እንመልከት። በአንድ የሃዲስ ዘገባ መሠረት፥ መሐመድ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሏል፡-

> «ሕዝቤ ወደ 73 ቡድኖች ይከፋፈላል ... ከእንዱ በስተቀር ሁሉም ወደ ሲያል ይሄዳል ... ይህም በእኔና በተባባሪዎቼ የተመሰከረለት ሃይማኖት ነው» (ሚሽካት ቅጽ 1 ምዕራፍ 6፡2)።

> «ቁጥሩ (የቡድኖች) ክነቢዩ ትንበያ በላይ እጅግ በዝቷል። የእስልምና ቡድኖች በቁጥርና በዓይነት እንኳ ክክርስትና ሃይማኖት ይበልጣሉና» (የእስልምና መዝገበ-ቃላት ገጽ 567)።

(የመዝገበ-ቃላቱ ዕድሜ 1885 ዓ.ም. ስለ ሆነ፥ ይህ የመጨረሻው ዐረፍተ ነገር ዛሬ እውነት ላይሆን ይችላል)።

የመሐመድን ትንቢት «ለማሟላት» ግያሱ'ል-ሉግሃት 73ን 12 ክፍሎችን የያዙ ስድስት ቡድኖች (12 በ6 = 72) አድርጎ ያካፍላል። ከዚያም «ነጂያ» (የዳኑ) ማለትም ሱኒዎችን 73ኛ አድርጎ ይጨምራቸዋል። (የእስልምና መዝገበ ቃላት ገጽ 567-569)። እነዚያ ከ73 በላይ የሆኑት አልተጠቀሱም።

የተለያዩ ዝርዝሮች ተሰብስበዋል። አንዳቸውም ግን በኋላ የተጨመሩትን አይገልጹም። እነዚህ አዲሶች፡- አሕመዳውያን፥ ባቢስቶች፥ እና ባሃይስቶች ናቸው። ብዙዎቹ የእምነት ቡድኖች በጣም ጥቂት የሥነ-መለኮት ልዩነቶች ብቻ አሏቸው፤ በብዙዎቹ የክርስትና እምነት ክፍሎችም ዘንድ ያለው ይኸው ነው።

እስኪ «ቤተ ክርስቲያን» ማለት በእርግጥ ምን ማለት እንደ ሆነ ለመመልከት ላንድ አፍታ ቆም እንበል። ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ማለት እንደ መስጊድ፥ ምኩራብ፥ ወይም ቤተ መቅደስ ያለ ሕንፃ እንደ ሆነ የሚያስቡ ይመስላል። ይህ እባባል በአጠቃላይ የሚያገለግል ቢሆንም ትክክል አይደለም። ስለ ቤተ ክርስቲያን ስናስብ ምናልባት ደግሞ እንደ

አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም ፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ወደ አእምሮአችን ይመጣ ይሆናል። አሁንም ይህ ቃል ጠቅላላ ግልጋሎት እየሰጠ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ትክክል አይደለም። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ተርጓሚዎች «ኤክሌዚያ» የሚለውን የግሪክ ቃል ለመተርጉም የተጠቀሙበት ሲሆን፥ የቃሉም ትርጉም በቀላሉ «ተጠርተው የወጡ» ማለት ነው። ከምንድነው ተጠርተው የወጡት? ከዓለም ውስጥ ነው። ይህም ዓለም የተሰኘው ቃል የሚወክለው በእነርሱ ላይ እግዚአብሔር ያለውን አለኝታ ቸል ያሉ ብዙ ሕዝብን ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ከአንድ ነገር ተጠርቶ ከወጣ፥ በዚያን ጊዜ ደግሞ ወደ አንድ ነገር ተጠርቶ ገብቷል። ከእግዚአብሔርና ከሌሎች አማኞች ጋር ጎብረት ለማድረግ ተጠርቷል።

መከፋፈል የተለያዩ ጽንሰ-አሳቦች፥ መሠረታዊ ትምህርቶች ወይም አመለካከቶች ውጤት ነው። በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ጊዜ አንዳንድ መሪዎች ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍ አፈንግጠዋል። የመጀመሪያዎቹ ይሁዲነት አቀንቃኞች ነበሩ። በኢየሱስ ከርስቶስ በማመን ከሚገኘው ደኅንነት በተጨማሪ፥ የአይሁድን የብሉይ ኪዳን ሕግጋት መጠበቅን ጠየቁ። ከዚያ በኋላ ከራእይ በተጨማሪ የግሪክ ፍልስፍናዎች (ኖሲስ) ተጨመሩ። ከእምነት በተጨማሪ ሥጋዊ ደስታ ከሚሰጡ ነገሮች ሁሉ መራቅም መለመድ እንዳለበት አንዳንድ ሰዎች አስተምረዋል። ቁልፍ ነገር ሁሉ ተንቆ፥ መንፈሳዊ ነገር ብቻ ይተኰርበት ነበር። በዚህም የእግዚአብሔርን የፍጥረት ብቃት ጥያቄ ውስጥ ከትተዋል።

ኖስቲክ የሆነው ባሲሊዲዝ በተጨማሪም ከርስቶስ በፍጹም ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር በመሆኑ፥ በመስቀል ላይ እንዳልተሠቃየ አስተምሯል። የቀሬናው ስምዖንም የእርሱን ስፍራ ወስዷል። ይህ እምነት በእስልምናም በመጠኑ ተንጸባርቋል። ከኖስቲኮች በተቃራኒ ባሲሊዲዝ ጥቂት ተከታዮች ብቻ ነበሯቸው።

ሌሎች ብዙዎች የተለያዩ ፍልስፍናዎችን ተከትለዋል። ነገር ግን የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ብያኔያቸውን በአዲስ ኪዳን ላይ በማስደገፍ፥ ለመጽሐፉ እውነተኞች ሆነው ቆይተዋል።

በንጉሥ ቆንስጣንጢኖስ ዘመን-መንግሥት የክርስትና እምነት ሕዝባዊ እውቅና በማግኘቱ፥ መንፈሳዊ ዝቅጠት ተጠነሰሰ። የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በተግባር በወግ የመተካቱ ነገር ይበልጥ እየጨመረ ሄደ። የኢየሱስ እናት ማርያም «የእግዚአብሔር እናት» ተብላ ተጠራች። ፖፖች (ሊቃነ ጳጳሳት) ትልቅ ኃይል ያዙ፤ በመሆኑም የቀሳውስት አልቅና በገንዘብ የሚገዛ ሆነ። የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተማርናትን ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ አልመሰለችም። እነዚያ መጽሐፍ ቅዱስን ያጠኑና በዚህ ዓይነት ልምምድ ላይ የተቃውሞ ድምፃቸውን ያሰሙ ክርስቲያኖች እንደ አሳሾች ተቆጥረው ተሰደዋል፤ ተገድለዋልም።

ከዚያም የተሐድሶ ዘመን የተባለው መጣ። ሐሰ፥ ሉተር፥ ከልቪን፥ ዝዊንግሊ እና ሌሎችም ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ ምክረዋል (1517 ዓ.ም.)። ነገር ግን ተቀባይነትን አላገኙም። ይሁንና ይህ ጥሪታቸው የቤተ ክርስቲያንን መበላሸት በተገነዘቡት በበርካታ ሕዝቦችና የፖለቲካ መሪዎች ግልጽ ዓመፅ አስከተለ። አውሮፓ በዚህ ጉዳይ ላይ በክፍፍል ውስጥ ስለ ነበረች፥ ወደ ሮማን ካቶሊክ እና «ፕሮቴስታንት» አብያተ ክርስቲያናት ተከፈለች። ጦርነቶች ተፋፋሙ። ከሁሉም አስጨናቂ የነበረው የ30 ዓመታት ጦርነት ሲሆን፥ ከሞት፥ ከጎዘን፥ ክረሃብና ክጭንቀት በስተቀር ያመጣው ፋይዳ አልነበረም። ይህ ጦርነት ዛሬ በስሜን አየርላንድ ወይም ሊባኖስ እንደሚደረገው፥ ከእውነተኛ ሃይማኖት ጋር ብዙ ግንኙነት አልነበረውም።

ካልቪንን የተከተሉ ሰዎች (ስዊዘርላንድ፥ ሆላንድ፥ ከጀርመን በከፊል) ወደ «ታደሱት» አብያተ-ክርስቲያናት (ፕርስቢቴሪያን፥ የታደሰች የደች ቤተ ክርስቲያን፥ ሄርቮርምዴ ክርክ፥ ወዘተ.) ተካትተው ነበር። በጀርመን ሉተር የመንፈሳዊ እንቅስቃሴውን በመጀመሩ፥ በዚህ ምክንያት «የሉተራን» ቤተ ክርስቲያን ሊመሠረት ጀመረ። በእንግሊዝና በስኮትላንድ የፖለቲካ ጉዳዮችና የዘውዱ ጣልቃ ገብነት ጫን ያለ ሰለ ነበር፥ ተሐድሶው የተለየ ገጽታ ነበረው። ለስውር ዓላማዎች ሄንሪ 8ኛ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ። ይህም በእንግሊዝና በሮም አብያተ ክርስቲያናት መካከል መነጣጠልን አስከትሏል። ይህ ግን በራሱ ተሐድሶ ተብሎ ሊጠራ አይችልም። ይሁንና ግሩም የሆኑ በርካታ ክርስቲያኖች ስለ

ነበሩ፥ በዚያን ጊዜ «በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲቀመጥና ሕዝቡ እንዲያነቡት እንዲበረታቱ» ታዝዞ ነበር («የቤተ ክርስቲያን ታሪክ» በኤ.ኤም. ሬንዊክ ገጽ 129)። በእርግጥ የተለመደ ድርጊት ሊሆን ይገባው ነበር። ይህ በፍጹም አልሆነም፡- ሉተርና ቲንዴይል መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለመዱት የሕዝብ ቋንቋዎች ማለትም ወደ ጀርመንኛና እንግሊዝኛ በተረጐሙት ጊዜ ብቻ ነበር በተራው ሰው ሊደመጥ ወይም ሊነበብ የቻለው።

ከዚህ ጊዜ በፊት (እና ብዙ ከቆየ በኋላም በሮማን ካቶሊክ አገሮች) መጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውና የሚነበበው የምሁራን ቋንቋ በሆነው በላቲን ብቻ ነበር። እንደ ድርጅት የተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ምሪትና ትምህርት ስለማትሰጥ፥ ሁሉም ሰው የግል መረዳት፥ እምነት ወይም የሕይወት ብቃት ሳይኖረው በልደት ብቻ የቤተ ክርስቲያን አባል ስለሚሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ ክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን ከተገለጸው ሁኔታ ጋር ጥቂት ወይንም ምንም መመሳሰል ከሌላት ድርጅታዊት ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን በተደጋጋሚ ለይተዋል። ግሳዊ ታማኝነታቸውን ለእግዚአብሔር በእምነትና በልምድ ለማደስ በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ ተሰበሰቡ። ነገር ግን «ችግር ፈጣሪዎች» ተብለው በመቆጠር ብዙ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ተሰድደዋል።

በእንግሊዝ አገር የነበሩ ፕዩሪታንስ (የእንግሊዝ ፕሮቴስታንቶች ቡድን) እንደዚህ ዓይነት ቡድኖች ነበሩ። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመመለሱ አስፈላጊነት ላይ በማጥበቅ ቤተ ክርስቲያንን ያሠሩትን ባህሎች ለማግለል ፈለጉ። እምነታቸውም በአውሮፓ ፕሮቴስታንቶች በከፍተኛ ደረጃ የተነቃቃ ሲሆን፥ ለክርስቲያኖች በግብረ-ገብ የመኖሩን አስፈላጊነት አመልክተዋል። ከድርጅታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የሚሰነዘረው የጥቃት ተቃውሞ የራሳቸውን የተለየ ቡድን እንዲመሠርቱ ገፋፍቷቸዋል። ይህም የኮንግሬጌሽናል እና ፕርስቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት ጅማሬ ነበር። እነርሱም እጅግ ብዙ ስደትና ተቃውሞ አጋጥሟቸዋል።

ከእነርሱም ብዙዎቹ ብቸኛው አማራጭ ቢኖር ወደ አሜሪካ መፍለስ እንደ ሆነ አስበዋል። እነዚህም በ1620 ዓ.ም. በ«አዲስ ዓለም» ውስጥ ለመኖር «ሜይፍላወር» በተባለው መርከብ ተሳፍረው የተጓዙት የመጀመሪያዎቹ «መናኝ አባቶች» ነበሩ።

ከዚህ ዕድገት ጎን ባፕቲስቶች በብሪታንያ መመሥረት ጀመሩ። እነርሱም ክርስቲያን ለመሆን ግላዊ ውሳኔ ማድረግ እንደሚያሻ አጽንተው ተናገሩ። ይህ በእርግጥ፥ በቤተ ክርስቲያን ደንብ በጥምቀትና በእምነት ማጽኛ የተተካው ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነበር። በእርግጥ ጥምቀት የክርስቶስ ትእዛዝ ስለ ነበረ፥ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ስትለማመድ ቆይታለች። ይህ ግን ቢያንስ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ለምልክት እንዲሆን የተደረገ ነበር። ተግባራዊ እምነት ከሌለበት ትርጉም የለሽ ነው። ጥምቀት የሚገልጸው አንድ ሰው ለደኅንነቱ በኢየሱስ ክርስቶስ አንደ ታመነና አሁን «ለኃጢአት እንደ ሞተ» መመሰከሩን ነው። «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ አንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን ... ክእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ ... አሮጌው ሰዋችን ክእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን ... እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቊጠሩ» (ሮሜ 6:4-11)።

ከዚህም የተነሣ አንድ ሰው የእግዚአብሔር ደኅንነት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ጽኑዕ የሆነ እምነት ሳይኖረው ክርስቲያን ሊሆን አይችልም።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያኖች የሚገኙባቸው አዳዲስ ቡድኖች ቢኖሩም፥ ቅሉ እንግሊዝ እንደገና ወደ መንፈሳዊ ዝቅጠት ውስጥ ገባች። ይሁንና ጆን ዌስሊ የንስሐን ስብከት በምድረ-እንግሊዝ ሁሉ መሰበክ በጀመረ ጊዜ መነቃቃት መጣ፡-

> «በወንጌል ጉዞዎቹ በ50 ዓመታት ውስጥ 250000 ማይሎች ተጉዟል። ብዙውን ጊዜም የተጓዘው በፈረስ ጀርባ ነበር። ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ሁሉ አስደናቂ የሆኑ ትዕይንቶች ባለማቋረጥ ታይተዋል። በሜዳ ላይ በሚያደርጋቸው ስብሰባዎቹ ውስጥ ልበ ድንጋይ ኃጢአተኞች የጸጸት የእንባ ጠብታዎች ጉንጮቻቸውን እያጠቡ ሲወርዱ ይታዩ ነበር» («የቤተ ክርስቲያን ታሪክ» በኤ. ኤም. ሬንዊክ)።

ሆኖም እርሱም ቢሆን እንዲህ ያለው አገልግሎት አስፈላጊ እንዳልሆነ በተመለከተችው በድርጅታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ማጣቱ አሳዛኝ ነገር ነው። ወደዚህ እምነት ለሚመጡ ሰዎች መንፈሳዊ መጠለያ ለመስጠት እንዲቻል «ሜቶዲስት» ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመ።

ስለዚህ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ይህን የመንፈሳዊ ዝቅጠት ሂደትና ዝቅጠቱንም ለማደስ የፈለጉትን የክርስትና ቡድኖች መፈጠር ለመመልከት እንችላለን። ይሁንና የድርጅታዊቷን ቤተ ክርስቲያን ምቾት ስለሚያናጉት ተቀባይነት አላገኙም።

ምንም እንኳ መንፈሳዊ ዝቅጠት ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ቢያጠፋትም፥ ሁልጊዜም የመንፈሳዊ መነቃቃት ለእውነት የታመነ ምስክርነት ይዞ ስለ ጸናና ለድርጅታዊቷም ቤተ ክርስቲያን ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎችን ስላቀረበ፥ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ዛሬ በብዙ «ሙት» አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እየተመነደገ ሲሄድ እንመለከታለን።

እንዲሁም ደግሞ ክመጽሐፍ ቅዱስ በተለየ መንገድ ያስተማሩ የተለየ ቡድን አስተማሪዎች ነበሩ። ብዙዎቹ ያልታወቁ ሲሆኑ፥ ጥቂቶቹ ግን በጣም የታወቁ እየሆኑ መጥተዋል። እነዚህ ከሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚያምኑ ክርስቲያኖች በመሠረታዊ ጉዳዮች ይለያያሉ፤ እርስ በርስም ይቃረናሉ። በዚህ ረገድ «የይሖዋ ምስክሮች» እና «አዲሶቹ መሠረተ-ሐዋርያት» ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ዛሬ የክርስቲያን አብያተ-ክርስቲያናትን ምናልባት በአራት ክፍሎች ለመክፈል ይቻላል፡- የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡- መጀመሪያ ተቃዋሚዎች የወጡበት አካል ሲሆን፥ እሁንም በራሱ ጠንካራ ድርጅት ነው። ከዚያም ፕሮቴስታንት የተባሉ አብያተ ክርስቲያናትን እናገኛለን። እነዚህም የአቡኑ ሥልጣንና በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉትን በርካታ ሥነ-ምግባራዊና መንፈሳዊ ብልሹ ልምምዶች ተቃውመዋል። ይሁንና ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹ ወደ ግትር የሥልጣን ተዋረድና ወደ ድርጅታዊነቱ አዝቅጠዋል፤ ደግሞም በአባሎቻቸው መካከል ኤግኖስቲኮችና እንዲያውም ክሃዲያንም ይገኛሉ። በአባሎቻቸው ዘንድ የኃጢአት ተግባራትንም ስለማይቃወሙ፥ ብዙው ሕዝብ እንደዚህ ዓይነት

ሕይወት አለው። ብዙ አገልጋዮች እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑና እምነታቸውን ከተግባር ለማዋል የሚለማመዱ ሳይሆኑ የሰም ክርስቲያኖች መሆናቸው ሊያስገርመን አይገባም። ልዩነትን የሚፈጥሩ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሦስተኛ ክፍል ይወሰዳሉ። አራተኛውም የወንጌላውያኑን ይይዛል። እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የኑሮ ዘይቤ ለመኖር የሚፈልጉ ሲሆን፥ ማንም ሰው «ዳግም ሳይወለድ» (ዮሐንስ 3፡3-5) ክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል በትክክል ያስቀምጣሉ። ይህ ከስብአዊ ዓቅም በላይ ስለ ሆነ፥ መለወጥ ያስፈልጋል። ሰው በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን አማካኝነት የራሱን ኃጢአተኛነት ይመለከትና በጸጋው የተፈለገውን ይቅርታ በማግኘት መፍትሔ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ይመጣል። በእኛ እግር በመተካትና ስለ እኛ በመስቀል ላይ በመሞት ይህንን ደኅንነት የሰጠን እርሱ ነው። አንድ ሰው ንስሐ በሚገባበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በእምነት በመመለስ፥ ይቅርታ ይጠይቃል። ከዚህ በኋላ ብቻ ነው ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ኅብረት ሊገባና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት አዲስን ሕይወት ለመኖር «ዳግም ሊወለድ» የሚችለው።

የወንጌል አማኞች በአብዛኞቹ የእምነት ከፍሎች ውስጥ ይገኛሉ። ሉተር አንድ ጊዜ እንዳለው «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያን» ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ መሠረት በእርግጥም የቤተ ክርስቲያን አካል ናቸው። ሌሎች ምናልባት መሐይማን፥ ተጻራሪ፥ ወይም ተታላይ እና ክዚህም የተነሣ፥ ከድርጅት አንጻር ብቻ የቤተ ክርስቲያን አካል ሊሆኑ ይችላሉ።

ደግሞም በርካታ ወንጌላውያን አብያተ-ክርስቲያናት አሉ። እዚህ አባል መሆን የሚቻለው አማኙ በኢየሱስ አዳኝነት ላይ ግልጽ የሆነ ምስክርነት በይፋ ከሰጠ በኋላ ብቻ ነው።

እነዚህኛዎቹ ቡድኖችና አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የተለየ ነገር ይሆን የሚያምኑት? አንባቢው እንደ ተመለከተውና ከዚህም በላይ እንደ ተገለጸው፥ በተወሰነ ደረጃ «አዎን» ለማለት ይቻላል።

የቤተ ክርስቲያን አመራርን ወይም የአምልኮ ዓይነቶችን፥ ወይም ጥምቀትን በተመለከተ ጥቃቅን ልዩነቶች አሉ። አንዳንድ አብያተ

ክርስቲያናት ወደ ስሜታዊነቱ ሲያጋድሉ፥ ሌሎች ደግሞ በአቀራረባቸው የበለጠ ሕግ-አጥባቂዎችና ምሁራን ይሆናሉ። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ ምንም ግጭት የለባቸውም።

ምናልባት ይህ መጠነኛ መግለጫ ሙስሊም አንባቢዎቻችን በአብያተ-ክርስቲያናት መካከል ስላለው ልዩነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳ ይሆናል። አንድ ለው በትክክል እንዲህ ብሏል፡-

> በመጽሐፍ ቅዱስ በሚያምኑ ክርስቲያኖች መካከል ለልዩነታቸው ስፍራ የሚሰጥ አንድነት አለ።

ማጠቃለያ

የአንድን ነገር እውነተኛነት ለማስመስከር 500፥ ወይም 50፥ ወይም ደግሞ 10 ብቻ መስካሪዎችና መርማሪዎች ቢኖሩና አስፈላጊውንም መረጃ ቢያቀርቡ፥ በመስቀለኛ ጥያቄ ውስጥ ከምስክሮቹ አንዱ ቀን ወይም ስም ቢያምታታ እንኳ፥ ስለ ነገሩ እውነተኛነት የሚኖረው ጥርጣሬ እጅግ አናሳ ነው። ይህ የዚያን ምስክርነት እውነተኛነት ሊያጠያይቅ፥ ወይም ደግሞ ብይኑን ወደ አሉታዊነት ሊለውጥ አይችልም።

እነዚህን ከቀድሞ ተቀባይነት አግኝተው የተመሠረቱትን እውነቶች ብዙ ጊዜያት ካለፉ በኋላ፥ አንድ ሰው ቢከራከራቸውና አስፈላጊ መስፈርቶችን እንደ ምስክር አድርጎ ለመረጃነት ሳያቀርብ፥ ወይም ለአባባሉ ሌሎች ተቀባይነት ያላቸውን ማጠናከሪያዎች ሳይይዝ፥ በጭፍኑ ብቻ ውሸትና ተለውጠው የተበላሹ ናቸው ቢል፥ ያ ሰው ይህንን ከማድረግ መገታት ይኖርበታል። ከዚያም ደጋፊዎቹ ጉዳያቸውን ለማጠናከር፥ የውሸት መረጃዎችንና ውሸቶችን ቢቀምሩ ጠቅላላው ጉዳይ እንዲያውም የበለጠ ተቀባይነት ያጣል።

ከላይ የተጠቀሱትን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሰነዘሩ ተቃውሞዎች በተመለከተ፥ እነዚህ ሙሉ ለሙሉ ለማለት ይቻላል፥ በተሳሳተ ግንዛቤ፥ በግልብ አስተሳሰብ፥ በእውቀት ማጣት፥ ወይም በብዙ በኩል ሆን ብሎ በማምታታት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ብለን እንደመድማለን። ስሕተት የተፈጸመባቸው እውነተኛ ሁኔታዎች በሙሉ፥ ከሁለት ብቸኛ ክስተቶች (ገጽ 53-54) በስተቀር፥ የመገልበጥ ስሕተቶች ናቸው። መዛግብት ለረዥም ዘመናት በእጅ ሲገለበጡ ስለ ቆዩ ከዚህ ችግር ነጻ ለመሆን አልተቻለም።

በማናቸውም ወቀሳ በተሰነዘረባቸው ሁኔታዎች መልእክቱ በመጠኑም እንኳ የተስወጠበት ወይንም የተጣመመበት መንገድ የለም። በሌላ በኩል፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት ሚዛን የሚደፉ መረጃዎች አሉ። በይበልጥ የተፈጸሙትን ትንቢቶች እናስባለን፤ የታሪክና የክርስ-ምድር ግኝትም ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

የመጨረሻው መረጃ ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ ካስረከቡ በኋላ ሕይወታቸው ሙሉ ለሙሉ የተለወጠላቸው ህልቆ-መሳፍርት የሌላቸው እውነተኛ ክርስቲያኖች ምስክርነት ነው። እሁንም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነት ምክንያት በሕይወታቸው ውስጥ የሚካሄደውን እንደገና የመታደስ ተአምር ለመመስከር ይችላሉ። እነዚህ ከዚህ በላይ ለቀረቡት መረጃዎች ተጨማሪ ሆነው የቀረቡ ተጨባጭ ማስረጃዎች ቢሆኑም፥ እምነትን ለሚለማመድ ሰው እውነትነታቸው ልክ እንደ ራሷ እንደ ሕይወት ያህል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በታማኝነት ለሚፈልጉትና ፈቃዱን ለመፈጸም ለሚፈቅዱት ሰዎች ራሱን ግልጽ ያደርጋል። ኢየሱስ ይህን እንዲህ ሲል ገልጸታል፡-

> «አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር። አይሁድም፡- ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ብለው ይደነቁ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፡- ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል» (ዮሐንስ 7፡14-17)።

አንግዲህ፥ ማንኛውንም ሙስሊም አንባቢ ባለማወቅ ወይም በከፋት በጥርጣሬ ለመሙላትና ባለበት ለማሰኪድ የሚፈልጉትን ሰዎች ዘገባ ላትቀበል፥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ኢየሱስ የራስህን እርምጃ በራስህ አመለካከት እንድትወስድ እንማጸናለን፤ እንለምናለን፤ አደራ እንላለን። ሁሉንም ነገር ላፍታ ተወት አድርግና አዲስ ኪዳንን ራስህ ግለጠው። አሳቦችህንና መረዳትህን እንዲመራው የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔር ጠይቀው።

በማንቋሸሽና በማዛባት ትምህርት ላይ ያለፉት ዓመታት በአእምሮህ ላይ ምልክት ትተው ማለፋቸው የማይቀር ነው። ከዚህ ላይ የሚታከለው ችግር፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ተመላላይ ቃላት ብዙውን ጊዜ በእስልምና የተለየ ትርጉም ሲሰጡ መቆየታቸው ነው።

ምንም ቢሆን የእግዚአብሔርን እውነት በተጨባጭ ሁኔታ ማግኘትን ብቸኛ ዓላማ በማድረግ፥ በቅን ልቦና የሚቃረኑትን እምነቶች ለመፈተሽ በመወሰን፥ መንገዱን ለማግኘት በምታደርገው ጥረት ጸሎትህን ሰምቶ በሚመልሰው በእግዚአብሔር እርዳታ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ጠቅላላ አሳብ እንድታገኝ ሊረዱህ በሚችሉ ክርስቲያኖች እገዛ፥ ያለ ጥርጥር ወደ ዋንኛው እውነት ትደርሳለህ። ይህ እውነት ብቻ በዚህ ሕይወት ፍጻሜ፥ እቅድና ዓላማ፥ በሚመጣው ሕይወት ደግሞ ዘላለማዊ በረከት ወዳለበት ጎዳና ይመራሃል። ልብ በል፡- ዋናው ነገር እውነት ከተተወ ወዲያ ምንም ዓይነት ታማኝነት ቢኖር ፋይዳ የለውም። በመጀመሪያ ወደ ራስህ ማጠቃለያ ከደረስህ በኋላ፥ ያንኑ ለማጠናከር ምክንያቶችን አትፈልግ። በመጀመሪያ ደረጃ፥ እውነቶችን ሁሉና የሚደግፉትንም መረጃ ሰብስብ። ከዚያም የራስህን ማጠቃለያ አብጅ!

እንግዲህ ወንጌል ምንድን ነው?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ በርካታ ትላልቅ መጻሕፍት ተጽፈዋል። እኛ ግን ዋናውን ነገር ለመጭመቅ መሞከርና መሠረታዊ ነጥቦችን ብቻ መመልከት አለብን። ከዚያ በኋላ ራስህ በራስህ ማንበብና ማጥናት ይኖርብሃል።

«ወንጌል» ማለት «የምስራች» ማለት ነው። በእርግጥ በዓለም ላይ ብዙ ዓይነት የምስራቾች ቢኖሩም፥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ዓውድ ግን እንዲህ ማለት ነው፦ እግዚአብሔር ሰው ከራሱ ጋር የሚታረቅበትን መንገድ ከፍቷል። ይህ መንገድ ከሰው ልጅ መጀመሪያ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ሲዘጋጅ ቆይቷል። በመጀመሪያ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በሰላምና በጎብረት ኖሯል። ከዚያም ውድቀት መጣ፦ አዳም (በዕብራይስጥ «ሰው») እና ሔዋን በራሳቸው ራስ ወዳድ ፍላጎትና መሻት በሰይጣን «አመራር ሰጪነት» ተገፋፍተው የራሳቸውን ዓላማ የማሟላትን መንገድ መረጡ። ፍላጎታቸውም እንደ እግዚአብሔር መሆን ነበር። ትዕቢትና ድፍረት በጌታቸው ላይ እንዲያምፁ አደረጋቸው። በዚህም ከዔድን ገነት ተባረሩ። ወዲያውም ልጆቻቸው ሰው ያለ አግዚአብሔር ብልሹ ለመሆኑ ምሳሌ ሆነዋል። ወንድም ወንድሙን ገደለው።

ከዚያን ጊዜ አንሥቶ የሰውን ልጅ ዓመፅና ብልሽት እናነባለን። ሰው ወደ ኃጢአት ከሚገፋፋው ኃይል ጋር ነው የተወለደው። ማንም ሰው ለማንኛውም ዓይነት ከፉ ባሕርይ መመሪያ አላስፈለገውም። ሁሉም ሰው ለዚህ ብቁ ሆኖ ተወልዷል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦

> «እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ከፉ እንደ ሆነ አየ» (ዘፍጥረት 6፡5)።

የሰው ልጅ ግን የእግዚአብሔርን ውሳኔ እንደ ኩሸት ቁጥሮ ገለል በማድረግ፥ በሰብአዊ ብቃት ዘገምተኛ ለውጥ በማመን፥ በተሰፈኛነት መኖርን መርጧል። ይህ ዛሬም ቢሆን ያው ነው። እግዚአብሔር ግን ይህን እመለካከት በጭራሽ አይጋራም። ከብዙ ቆይታ በኋላ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚከተለውን እናነባለን፦

> «ሕግ (የእግዚአብሔር ትእዛዛት) መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ (በላቲን ካርኒስ ማለት ሥጋ ማለት ስለ ሆነ፥ ይህ ሥጋዊ አእምሮ ያለው መሆኑ ነው)። የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም...በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም...እንግዲያስ መልካሙን እደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ከፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ። በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ» (ሮሜ 7፡14-23)።

ማንኛውም እውነትን ለማግኘትና ለመቀበል የተዘጋጀ ሰው ከዚህ ዐረፍተ ነገር እውነተኛነት ጋር መስማማት መቻል አለበት። ለፈውስ የመጀመሪያው የመወጣጫ መሰላል ማስተዋል ነው። ከሁሉም የከፋው መታለል የሚመጣው ሰው በኃጢአተኛ ተፈጥሮው፥ ራሱን ከሌሎች ጋር በማወዳደር፥ ለካስ ያን ያህል የከፋሁ አይደለሁም ብሎ ሲደመድም ነው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የራሱን ሁኔታ በሚረዳበት ጊዜ ለበደሉ በሃይማኖታዊ «ሥርዓቶች» እና በደግ ሥራዎች ለማካካስ ይሞክር ይሆናል፤ ይህ ደግሞ የተጋነነ ዓይነት እምቢተኝነትና ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ርቆ ለመኖር የመፍቀዱ መግለጫ ነው።

የዘፍጥረቱን ታሪክ ቀጥለን ስንመለከት የእግዚአብሔር ቅጣት የሆነው የውኃ ጥፋት ሲመጣ እንመለከታለን። ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ፦

> «በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ ... ኖኅም ... ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ፤ ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ» (ዘፍጥረት 6፡8-9)።

ኖኅ እግዚአብሔርን ስላመነ፥ እግዚአብሔር ለእርሱና ለቤተሰቡ ዓላማ ነበረው። እርሱ «የጽድቅ ሰባኪ» ነበረ (2ኛ ጴጥሮስ 2፡5)። ከእግዚአብሔር ዘንድ ማስጠንቀቂያ ተቀብሎ መርከብ በመሥራት «በዚህ

ዓለምን ኮነነ፡ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ» (ዕብራውያን 11፡7)።

እንግዲህ የጽድቁ ባሕርይ ምን ነበር? በኃጢአት ለመተባበር እምቢ ብሎ ከእግዚአብሔር ቃል እኳያ ተግባሩን መፈጸሙ ነው። ይህ ነው እንግዲህ እምነት ማለት።

የሚያሳዝነው ግን የኖኅ ትውልድ ከጥፋት ውኃ በፊት ከነበሩት የተሻሉ አለመሆናቸው ነው። ዕቅዳቸውንም ነድፈው እንዲህ አሉ፡-

> «ኑ፥ ጡብ እንሥራ፥ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ። ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው፤ የምድርም ዝፍት እንደ ጭቃ ሆነችላቸው። (ምናልባት በሙት ባሕር አካባቢ የሚገኘው የአሳተ ገሞራ ትፋት የፈጠረው ዝፍት ይሆናል።) እንዲህም፡- ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፤ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ» (ዘፍጥረት 11፡3-4)።

ጡብ በእሳት የሚተኰሰው ለምንድን ነው? ውኃን ለመቋቋም እንዲችልና ጠንካራ እንዲሆን ነው። ዝፍት ለማጣበቂያው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ከሸክላ በላይ ጠንካራ ባይሆንም፥ ውኃ የመቋቋም ችሎታ ስላለው ነው። ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ መገንባት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? አንዱ ምክንያት ተጠቅሷል፡- «ስማችንን እናስጠራው።» እግዚአብሔር ለባሪያው ለአብርሃም፡-

> «ስምህንም አከብረዋለሁ» (ዘፍጥረት 12፡2)

ማለቱ ትኩረትን የሚስብ ነገር ነው።

የአብርሃም ስም በእግዚአብሔር ጸጋና ፈቃድ ዝና አግኝቶአል። ዳሩ ግን ለራሳቸው ስም ለማስቀረት የፈለጉ ሰዎች ተረስተዋል። እንዲሁም ግንቡ የተገነባበት ሁለተኛም ሰውር ምክንያት አለ። ተጨማሪ የጥፋት ውኃ ቅጣት ከእግዚአብሔር ዘንድ ቢመጣ የሚያመልጡበት መንገድ ነበረ። ከዓመፃቸው የተነሣ አሁንም የውኃ መጥለቅለቅ ቢመጣ፥ ከግንቡ ጫፍ ተቀምጠው ይተርፋሉ። ይህን ነበር እነርሱ ያስቡት («ጫፉ ሰማይ የደረሰ»)። ግንባቸው በተገነባ ጊዜ፡-

> «እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ» (ዘፍጥረት 11፡5)

የሚለውን ለበጣ የታከለበትን አባባል እናነባለን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ «ግንቦችን» ለመገንባት ሲሞክር ቆይቷል። የፍልስፍና «ግንቦችን፥» የፖለቲካ «ግንቦችን፥» በይበልጥ ደግሞ የሃይማኖት «ግንቦችን» ሠራ። የኋለኞቹ ከእርሱ መመዘኛዎች አኳያ ለመኖር ባለመብታታችን ከሚከተለን የእግዚአብሔር ፍርድ እኛን ለመከለል ተሰሩ የሚሰጡት የሃይማኖት ሰልቶች ናቸው። እነዚህ የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ከራሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚጠይቃቸው መስፈርቶቹ ናቸው፡-

> «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ።
> ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።...
> የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ!...
> የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» (ዘጸአት 20፡2-4፥7)።

ከዚህ ላይ የተጨመሩት በሰዎች መካከል የሚኖሩትን ግንኙነቶች የሚመለከቱ ሕጎች ናቸው፡-

> አባትህንና እናትህን አክብር፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ ...በሐሰት አትመስክር ... ክባልጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ» (ዘጸአት 20፡12-17)።

የኋለኞቹ ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደሚክተለው ተጠቃለለው ቀርበዋል፡-

«ትአዛዝ ሁሉ... ‹ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ› በሚለው ቃል ተጠቃልሎአል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው» (ሮሜ 13፡9-10)።

እንዲህ ያለ ፍቅር ያለው ሰው የት አለ? እንዲህ ያለ ፍቅር ያላት ሴት የት አለች? በእርግጥ «እወድሃለሁ» እንላለን። ይህን ስንል ግን፥ «አንተን (አንቺን) የራሴ ንብረት ለማድረግ እፈልጋለሁ» ማለታችን ነው።

በዚህ በተበላሸው ጎበረተሰብ አብራም፥ ወይም በኋላ እንደ ተጠራው አብርሃም ኖሯል። እግዚአብሔር ከቤተሰቡና ከሃይማኖታዊ ከልሉ እንዲወጣ ጠራው፥ እርሱም ታዘዘ። በምንም ዓይነት ፍጹም ሰው አልነበረም (ዘፍጥረት 12፡10-20፤ 15፡1-6 ን ከ 16፡1-4፤ 17፡15-19፤ 20፡1-11፤ ወዘተ. አወዳድር)። ነገር ግን፡-

> «አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።» አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ ታዘዘ፤ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጋር ተጣበቀ።
>
> «አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም» (ሮሜ 4፡2)።

በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነቱ ነበር እንደ ጽድቅ የተቆጠረለት። በሒሳብ መዛግብት ውስጥ የገቢና የወጪ መመዝገቢያ ሰፍራ አለ። ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የተጠበቀ መዝገብ አለ። በዚህም መዝገብ ውስጥ እያንዳንዱ ኃጢአት - ከእግዚአብሔር በላይ አንድን ሰው ወይም ነገር መውደድ፥ ሌላውን ሰው ከራስ በታች መውደድ (እዚህ ላይ ላፍታ ልናስብበት ይገባል)፥ በአሳብ፥ በቃል፥ ወይም በድርጊት የተፈጸመ ማንኛውም ስሕተት በእኛ ላይ ይመዘገባል። ከዚያም ደግ ሥራዎችን እንሠራለን። እነርሱስ የት ላይ ይጻፋሉ? የትም። እነዚህን ማድረግ ኃላፊነታችን ነው። ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሏል፡-

> «የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፡- የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ» (ሉቃስ 17፡10)።

በሌላ ስፍራ ደግሞ ስለ አብርሃም የሚከተለውን እናነባለን፡-

> «እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?» (ያዕቆብ 2፡22)።

ሥራዎች በራሳቸው ለኃጢአት ማካካሻ ሊሆኑ አይችሉም። ጽድቅ ሆኖ ለአብርሃም የተቆጠረለትም እምነቱ ነበር፡-

> «አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።»

እግዚአብሔር በአብርሃምና በዘሮቹ በኩል ለሰው ልጅ ከእርሱ ጋር የሚኖረውን የሕይወት መሠረትና ከአለመታዘዝ በስተያ የዕርቁን መመሪያ ለማሳየት ፈለገ። እስራኤል የአንዱን አምላክ መልካም የምሰራችና ዕቅድ በስውና በአጋንንት ማታለል (የመናፍስት አሠራር) የሃይማኖት ጽልመት ውስጥ ለሚደናበረው ሰው ማምጣት ነበረባት። እስራኤል ግን የአብርሃምን አምላክ «በመዘንጋት» በራሷ የሃይማኖት መሥመር ተጓዘች። ይህም መሥመር ፈሪሃ-እግዚአብሔር የማይታይበት ነበር።

እንደገና እግዚአብሔር ሙሴን በመላክ ተጨማሪ እርምጃ ወሰደ። በግብፅ የባርነት ቀንበር ሥር የነበሩት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ባደረጋቸው ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች ሳቢያ ነጻ ወጡ። ማንም ሰው ይህን የእግዚአብሔርን ዓርማና ኃይል አላጣውም ነበር፤ ያውቀዋል። ከዚያም እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ይህም ዛሬ «የጥንቱ ቃል ኪዳን» ወይንም «ብሉይ ኪዳን» ተብሎ ይታወቃል። እስራኤል አዲስ የሕይወት መንገድ እንድትከተል እግዚአብሔር አዟል። ታላቁን የእርሱን ትእዛዝ አንዲህ በማለት ሰጥቷል፡-

> «ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር አንድትበዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባበት ምድር አንዲባርክህ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም፥ ለሌሎችም እግልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም፥ ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ አነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባበት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም። በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረክትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ

ሕይወትን ምረጥ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ» (ዘዳግም 30፡15-20)።

ጻሩ ግን አንድ ሰው ከእነዚህ ትእዛዛት ውስጥ አንዱን ቢጥስ፥ ምን ይደርስበታል? ይጠፋ ይሆን?

«ነገር ግን መጽሐፍ፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል። ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ግንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ፡- አትግደል ብሎአልና፤ ባታመነዝርም፥ ነገር ግን ብትገድል፥ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል» (ያዕቆብ 2፡8-11)።

«ከእገሩ ሕዝብም አንድ ሰው ኃጢአትን ሳያውቅ ቢሠራ፥ እግዚአብሔርም፡- አትሥራ ያለውን ትእዛዝ ቢተላለፍ፥ ቢበድልም፥ ለእርሱም የሠራው ኃጢአት ቢታወቀው፥ ስለ ሠራው ኃጢአት ነውር የሌለባትን እንስት ፍየል ለቍርባኑ ያመጣል። እጁንም በኃጢአት መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል፤ የሚቃጠልም መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ የኃጢአትን መሥዋዕት ያርዳል። ካህኑም ከደምዋ በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል፥ ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ያፈስሰዋል ... ካህኑም ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል ካህኑም ስለ እርሱ ያስተሰርያል፥ እርሱም ይቅር ይባላል» (ዘሌዋውያን 4፡27-31)።

አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ ቢተላለፍና እርሱን ባዘዘው መንገድ ዕርቅን ባያደርግ ጠፍቷል ማለት ነው። ጻሩ ግን እግዚአብሔር ለምን ይህን ጭካኔ የተሞላበትን የመሥዋዕት መንገድ መረጠ? ምክንያቱም የኃጢአትን አስከፊነት ለሰዎች በሚገባ ለማስገንዘብ ስለ ፈለገ ነው። ቀጥሎ ለምትፈጽመው ኃጢአት የምትወደውን እንስሳህን ገድለህ

የምታቃጥል ከሆነ፥ ያንን ላለማድረግ የምትችለውን ሁሉ ጥረት ታደርጋለህ።

እግዚአብሔር ሕዝቡ ራሳቸውን ገዝተው ለእርሱ ብቻ እንዲኖሩለት ፈለገ። በሙሴ መረነትም ቢሆን ሕዝቡ እንደገና በማጉረምረምና በማመፅ፥ በባዕድ እምልኮትና በጽልመት ውስጥ ወድቋል። እግዚአብሔር ከሕይወት ሥርዓቱ ጋር መተዉ ብቻ ሳይሆን ተዘንግቷልም።

በኋላም የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ ተፈጸሙ። እስራኤል በሽንፈትና በመጨረሻም በእግዚአብሔር ትንቢት የቃል በቃል ፍጻሜ ሳቢያ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ተበትና ለብዙ ምእተ ዓመታት እጅግ አስጨናቂ በሆነ ስደት ለመኖር ተገድዳለች።

የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ የሆንችው እስራኤል ካለመታዘዝ የተነሣ ተተወች። ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ዕቅዱን ማሳካቱን ቀጥሏል። እስቀድሞ ለአዳምና ለሔዋን የሰይጣንን ራስ «ለመቀጥቀጥ» ከዘራቸው ውስጥ ስለሚመጣው አንድ ሰው ነግሮአቸው ነበር። እርሱም ከአብርሃም የዘር ሐረግ ውስጥ መምጣት ነበረበት («በአንተ የምድር ነገዶች ሁሉ ይባረካሉ»)፤ እንዲሁም በይስሐቅ («በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል») (ዘፍጥረት 12፡3፤ 21፡12)።

አይሁዶች ይህን ይጠበቅ የነበረውን ነጻ-አውጪ መሢሓችን ብለው ይጠሩታል (ሕዝቡን በአምላኩ ፊት እንደሚያቀርብ ካህን ንጉሥ ወይም ገዢ መሆኑን ለማመልከት)። ከይሁዳ ነገድ፥ ከዳዊት ወገን እንደሚመጣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፡-

«ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን እደረግሁ፥ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ፡- ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፥ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ ... እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ፥ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል። ለዘላለምም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ፥ ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው። ዘሩንም ለዓለምና ለዘላለም፥ ዙፋኑንም እንደ ሰማይ ዘመን አደርጋለሁ» [መዝሙር (89)፡3፥27-29]።

«እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትም፥ እንዲህ ብሎ፡- ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ» [መዝሙር (132)፡ 11]።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም» (ኢሳይያስ 9፡6-7)።

በዳዊት ዙፋን የተተካው ልጁ ነበር። ነገር ግን ከብዙ ዘመናት በፊት ያ መንግሥት ጠፍቷል፤ ተረስቷልም። እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ዘላለማዊ መንግሥት ስለ ሆነና ደግሞም ማንኛውም የሰው መንግሥት ዘላለማዊ ስላልሆነ፥ የሚናገረው የተለየ ነገር ነው። ነቢዩ የሚናገርለት ልጅ (ከድንግል የሚወለድ ኢሳይያስ 7፡14) መሢሑ ኢየሱስ ነው። እርሱም ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ነው! ዳሩ ግን ይህ የተሰጠው ተስፋ ሰላም፥ ጽድቅና ፍርድ የት አለ? መንግሥቱስ የት አለ? ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች እንዲህ በማለት መልሶአቸዋል፡-

«የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም፡- እነኋት በዚህ ወይም፡- እነኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና» (ሉቃስ 17፡20-21)።

እነዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት አካል የሆኑት ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አላቸው። ይቅር ተብለው ወደ እግዚአብሔር በመመለስ፥ ጽድቅን ተቀብለዋል።

«በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ . . .» (ፊልጵስዩስ 3፡9)።

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፥ ወደ እርሱ ያመለከቱ የነበሩትን በርካታ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፈጽሟል። የእግዚአብሔርንም መንግሥት መሥርቷል።

በእርሱም ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች ገልጧል። ለሰው ልጅ መንገዱን እያሳየ፥ ይከታተለው በነበረው የዓለም ሕዝብ ፊት ኃጢአትን ሳይሠራ በፍጹምነት ተመላልሷል። ከዚያም ከእግዚአብሔር አብ ጋር ለመታረቅ ማንም ሰው እንደሚያስፈልገው መሥዋዕት ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቷል።

«ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ» (1ኛ ጴጥሮስ 2፡24)።

«የምስራቹ» ወይም «ወንጌሉ» እንግዲህ ይህ ነው! አለ እርሱ በ«እኔነቱ» ትእዛዛት መሠረት «ከኃጢአት በታች ተሸጦ» ከመኖር በቀር ሰው የሚያደርገው ነገር የለውም። በትንቢት እንደ ተነገረው፥ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ የእኛን በደልና ኃጢአት በራሱ ላይ አደረገ። የኃጢአት ውጤት የሆነውን መከራ በመቀበልም ተሠቃይቷል። በእኔ ላይ ሊያርፍ የሚገባው ፍርድ በእርሱ ላይ ወደቀ፡-

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ . . . ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም» (ዮሐንስ 10፡15፥ 27-28)።

ይህ የምስራች ነው! እንተ ለመሥራት የማትችለው ሁሉ ተሠርቶልሃል። እንግዲህ የቀረውን የሕይወት ዘመንህን እዳኝህ የሆነውን (ኢሳይያስ 63፡7-11) እግዚአብሔርን በማመስገን በደስታ አሳልፍ። ሕይወትህ የእርሱ ነው፤ በመሆኑም ባዝኖ ክቆየ በኋላ በፍለጋ እንደ ተገኘ በግ፥ ድምፁን ሰምተህ በእምነት ተከተለው። ለእነርሱ ብሎ ነፍሱን እንደ ቤዛ አድርጎ ስለ ሰጠ፥ የራሱንም ዘላለማዊ ሕይወት ስለሚለግሳቸው፥ የራሱ የሆኑትን ያውቃቸዋል። ይህ የምስራች ነው!

ኢየሱስ ግን ሞቶ አልቀረም! ክብርን የተሞላ እግዚአብሔር ከሙታን አስነሥቶታል! እኩንም የምስራች! ወደ ሰማይም በማረግ፥

«በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (ሮሜ 8፡34)።

ተጨማሪ የምስራች! ወይስ ለአንተ መጥፎ ዜና ይሆን? አሁንም በፊቱ ጉልበታቸውን ለማንበርከክ ያልፈለጉትን በጽድቅ ለመዳኘት ደግሞ ይመጣል (ፊልጵስዩስ 2፡9-10)፤ ይቅርታውን ለመቀበል እምቢተኞች ወይም ትዕቢተኞች በሆኑት ላይ ይገለጣል። እንዲሁም በሥጋ የሞቱትንና ዳሩ ግን ተስፋቸውንና እምነታቸውን በእርሱ ላይ የጣሉትን ሁሉ ለማስነሣት ይመጣል።

ይህ ሁሉ በአዲሱ ኪዳን ሥር ተከናውኗል።

በብሉይ ኪዳን ተተንብዮ ነበር፡-

> «አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ... ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም ... የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ... ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ ... በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና» (ኤርምያስ 31፡31-34)።

ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ለኃጢአተኞች በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ አዲስ ኪዳን በመጽናቱ ለኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ ምሉዕና ክፍት ሆኖ ይሠራል። ይህም ኢየሱስ የፍርድን ብያኔ ለመስጠት እስኪመለስ ድረስ ይቅርታ የሚገኝበት የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

ያን ጊዜ የምስራቹ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለተቃወሙት፥ ወይም ስው-ሠራሽ ሃይማኖት ለመረጡት ዋጋ አይኖረውም።

ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያው ከመቅጽበት አይመጣም። ምንም አንኳ ኢየሱስ ለስው ልጅ ሁሉ ቢሞትም፥ የሚቀበሉት ብቻ ናቸው የይቅርታውን ስጦታ የሚያገኙት። ስለ ሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ማድረግ የአንተ ኃላፊነት ነው። ይህንንም እንድታደርግ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ጥሪውን ያቀርብልሃል፡-

> «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቈጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ

> ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19-20)።

እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ ታዝዘናል፡-

> «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ስውን ሁሉ ያዛል ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ስው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው» (የሐዋርያት ሥራ 17፡30-31)።

ስለ ሆነም ለእዚህ ጥሪና ትእዛዝ ምላሽ መስጠት አለብን።

ይህም የሚሆነው ሕይወትህን ገምግመህ ኃጢአትን በውስጡ ስታገኝና ተጸጽተህ ለመመለስ ስትወስን ነው።

> «ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን። ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት፡- እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማ በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት። ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1፡4-10)።

ለዚህ ምላሽ እንዲሆን፥ እግዚአብሔር ራሱም አስተማማኝ ቃል ገብቶልናል፡-

> «በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና» (ኤርምያስ 31፡34)።

ከኃጢአታችን የሚያነጻን የኢየሱስ መሥዋዕት ብቻ ስለ ሆነ፥ እርሱን እንደ ደኅንነታችን (ደኅንነት = ኢየሱስ) እንቀበለዋለን። ይህ

ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ኅብረት ላለው ሕይወት ጅማሬው ነው። አሁን ጸድተሃል። የሕይወትህና የልብህ አድፍ ተወግዶልሃል። አሁን ልብህ በአዳዲስ ነገሮች መሞላት አለበት፥ ከሁሉም በፊት ግን በእግዚአብሔር። አሁን እርሱ በልብህና በሕይወትህ ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ሊፈቀድለትና ሊጋበዝ (በጸሎት) ይገባዋል። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አሁን ሕይወትህን ያድስዋል። ፈቃድህም ሰፈቃዱ ይገዛል።

> «በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ስሞተውና ስተነሣው አንጂ ወደ ፊት ስራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።
>
> «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡15፥ 17-18)።

ይህን ያደረገ ሰው አሁን የእግዚአብሔር ንብረት ነው። በእግዚአብሔር በራሱ መመዘኛ መሠረት ተቀባይነትን አግኝቷል። ይቅርም ተብሏል። አሁን ያንን አዲስ ሕይወት ስመኖር፥ ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አዲስ ኃይልንና ምሪትን ይቀበላል። ያም ስእግዚአብሔር ክብርና በምድር ላይ መንግሥቱን ለመመሥረት ነው። ይህ ደግሞ የተወላገደ ወይም የተዛባ ነገር ላይኖርበት፥ ወደ ሕይወት ውበትና ቅድስና ይመራል። አሁን ወደ መጀመሪያው የሕይወት ትርጉም ተመልሰናል። በዚህም ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ ብቻ ላይሆን፥ በፍጥረት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሙላት ቀን በቀን መለማመድ የሚቻልበት ነው። ከሁሉም የሚበልጠው ዕጣ-ፈንታዬን ማወቄ ነው። ኃጢአቶቼ ከእግዚአብሔር አአምሮ ስለ ተፋቁ፥ ስለ ወደፊት በተስይም ስለ ሞት መፍራት አያስፈልገኝም። አርሱም አንደዚሁ ነው የሚል!

> «አንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8፡1)።

ልከ ኖኅና ቤተሰቡ በመርከብ ውስጥ ሆነው ከጥፋት ውኃ እንደ ዳኑ፥ እንዲሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ያሉትም ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ነጻ ናቸው።

ይህ አዲስ ሕይወት ዳግም በተወለደ አማኝ ውስጥ አዳዲስ ፍላጎቶችን ያሳድራል፡-

በመጀመሪያ ደረጃ፥ በአምልኮ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ኑሮና በፍቅር የሚገለጽ የአከብሮት ሕይወት፥ ሁለተኛ፥ ተመሳሳይ እመለካከት ካላቸው ጋር ኅብረት የማድረግ መሻት፥ ሦስተኛ፥ ይህን አዲስ ሕይወትና ተስፋ ከሌሎች ጋር ስመካፈል መፈለግ። በነገራችን ላይ የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ይኸው ነው።

ስለዚህም ከዚህ ነገር ወደ ኋላ እንዳትልና፥ ስሌላ ጊዜ ወደ ጎን እንዳትተው፥ ይልቁንም ከምትፈልገው በላይ ዘልቀህ ስመግባት በስሜትህ ምንም ጫና ሳያድርብህ፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ በማናቸውም ርዕሶች ላይ ነጻና ግልጽ ውይይት ስማድረግ ከእኛ ጋር ግንኙነት እንድታደርግ እንጋብዝሃለን። በጠንቃቃነታችንም ላይ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ።

ዳሩ ግን የማንንም እርዳታ ባትፈልግ እንኳ፥ ቢያንስ የቅርብ ጊዜ ትርጉም የሆነ አዲስ ኪዳን በመፈለግ፥ በእነዚህ ማስታወሻዎች እየተረዳህ ራስህ አጥናው። ከቁርዓንም ጋር አወዳድረው።

ሙስሊሞች ስክርስቲያኖች ከሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መካከል ዐበይቱን ከመለስን በኋላ እኛ ክርስቲያኖች ሙስሊም ጓደኞቻችንን ስለ እምነታቸው ተአማኒነትና መረጃዎችን ስመጠየቅ እንፈልጋለን። ከዚህ በታች ያሉትን መጻሕፍት ቅጂዎች ስማግኘትም ሆነ ከእኛ ጋር ስመገናኘት ብትሻ እባክህ በሚከተለው አድራሻ ጻፍልን፡-

የሕይወት ቦር
የ.መ.ሣ.ቁ 4937
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

<u>ጎትመታችን የሚከተሉትን ያጠቃልላል</u>፡-

- ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች

<u>ለሙስሊም አንባቢዎች የሚጠቅሙ እነስተኛ መጻሕፍት</u>፡-

- «አል-ኪታብ» (ለሙስሊሞች የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት)
- ውድ ዐብደላ
- ላለመደናገር ማወዳደር
- ዓላማና ግብ
- የውኃ ላይ ኩበት
- የናቢ ዒሣ መልእክት
- ስለ መሢሑ ልንገራችሁ
- እንድ እምላክ እንድ መንገድ
- ለእነዚህ አይገድህምን?

<u>ሙስሊሞችን በወንጌል ለመድረስ የሚጠቅሙ ትራክቶች</u>፡-

-ደኅንነት በሥራ ወይስ በእምነት?
- የደግ ሥራ መብዛት እንደ እምነት አይሆንም